ሕዝባዊ ኢድማ ላይ በደብረ ታቦር አካባቢ ጣልቃ ሲገቡ ሲሞክሩ ሕይወታቸውን በማጣቸው የዘመቻ አብዮተኞች እና ቆስቋሾች በክልሉ ለተነሡ ለእነዚህ ያልተረጋጉ ሁኔታዎች ተጠያቂ ተደረጉ።

የአካባቢው ፖሊስ ለእኛ የወገኑትን አቦሃየ አለማየሁ የተባሉትን ቄስ ስላሰራቸው፣ ሁኔታው በቆላ ድባ የነበረንን ተቃውሞ ያቀጣጠለ አንድ ክስተት ሆነ። ጉዳያችንን ካስተናገዱ እና የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን ቄስ ሆነው ሳሉ በአመዛኙ ማርክሲዝምን ከተቀበሉ ሰዎች አንደኛው እርሳቸው ነበሩ። እንዲለቀቁ መጠየቃችንን ብንቀጥልበትም፣ ግትሮቹ የአካባቢው ሹማምንት የዙሪያ-ገባውን ዐመፅ በማነሣሣት ከሰሷቸውና ሊለቋቸው ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ያ ሁኔታ ተስፋ ስላስቆረጠን፣ በከተማው ውስጥ ተከታታይ ሠልፎችን እንድናደርግ አስገደዱን።

በጭሃይት አስረናቸው የነበሩት ገበሬዎች እንዲሁም የአካባቢው የደህንነት መኮንኖች ጭምር ሊገድሉኝ እያሤሩ እንደ ሆነ ስለ ሰማሁ፣ ጊዜ እየገፋ በሄደ ቍጥር ስለ ሕይወቴ የበለጠ ዋስትና እንዳጣሁ ተሰማኝና የማምለጫ ሤራዎችን አዘጋጀሁ። የዘመቻ መኮንኖቼን ለማሳመን በአእምሮ ሕክምና ተቋም ውስጥ የሕክምና እርዳታ እንደሚያስፈልገኝ አስመስዬ ያልተለመዱ ነገሮችን ሳደርግ ጊዜ ወደ ጎንደር ሆስፒታል ተወሰድኩ። የገጠመኝ የሕክምና ሰው ዶ/ር አደም ከትውልድ አካባቢዬ ከሐረር የተገኘ አደሬ ስለ ነበር፣ ስለ ሁኔታዬ የእውነቴን ነግሬው ብቸኛው የሥነ-ልቡና ተቋም ወደ ሆነውና አዲስ አበባ ወደሚገኘው አማኑኤል ሆስፒታል መተላለፊያ (ሪፈር) እንዲጽፍልኝ ጠየቅሁት። ግልጥልጥ ያለውን እውነት ከነገርኩት በኋላ፣ ይህን ማድረጉ ከሙያው ሥነ-ምግባር ጋር የሚጻረር በመሆኑ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ፍርጥ አድርጎ ከነገረኝ በኋላ፣ አንዳች የእንቅልፍ ኪኒን ሰጠኝና ወደ ጣቢያዬ መለሰኝ። የመጀመሪያው ዕቅዴ ሲከሽፍብኝ ከችግሩ ለመውጣት እንደ ብቸኛ መንገድ ያንኑ ማድረግ ነበረብኝና የምር እያበድኩ እንደ ሆን ለዘመቻ መኮንኑ ለማሳመን በድጋሚ የወፈፌነት ባሕርያትን ማሳየት ጀመርኩ።

አንድ ቀን፣ ከጣቢያው በተመደቡ የሚረዱኝ ሰዎች ጋር ሆኜ በድጋሚ ወደዚያው ዶክተር ተወሰድኩ። በዚህ ጊዜ በአንዳች ዓይነት የአእምሮ ችግር ውስጥ እንደ ሆንኩ አመነና በመንገዴ ላይ የሚያጅበኝ እና የሚንከባከበኝ ፖሊስ መኮንን ተመድቦልኝ አዲስ አበባ ወደሚገኘው አማኑኤል ሆስፒታል አስተላለፈኝ።





## ከዘመቻው መልስ

ዶክተር እንዲያየኝ ወደ ሆስፒታል ተወስጄ ከታየሁ በኋላ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እያስመሰልኩ እንደ ሆነ ማንም ባላወቀበት ሁኔታ፣ ወዲያውኑ አልጋ ይዤ እንድታከም አስገቡኝ። በተቋም ውስጥ የሚረዱ የአእምሮ ችግር ያለባቸው እብዶችን ያየሁበት የመጀመሪያው ጊዜ ይሄ ስለ ነበረ፣ ሆስፒታሉ ውስጥ በነበርኩበት የመጀመሪያው ሌሊት የምሬን ፈራሁ። ከተለያዩ ዘመቻ ጣቢያዎች ከባድ የአእምሮ ችግር ኖሮባቸው በዚያ የሚታከሙ በርካታ ተማሪዎች ሲኖሩ፣ አብዛኞቹ የሥነ-ልቦና ችግር ኖሮባቸው በሆስፒታል የተገኙት ጫት በከፍተኛ መጠን ከሚቃምባቸው ከሐረር እና ጉራጌ ክልል የመጡ እንደ ሆኑ ማስተዋል ጀመርኩ። ከእኔ መንደር ከጉርሱም የመጣውን የባለጠጋው ነጋዴ የሼክ አደም ልጅ የሆነውና ፈጽሞ ያበደውን ሶማሌው ሐሰንን ለይቼ አወቅሁት። ቀን ላይ በዚያ ሲዞር ቆይቶ፣ ሌሊት ላይ የአካባቢውን ጋዜጣ ዘቅዝቆ የሚያነበው ሐሰን ምንም እንኳን የአንድ ሰፈር ልጆች ብንሆንም፣ እኔ ማን እንደ ሆንኩ ለይቶ አላወቀኝም ነበር። ከእኔ ጎን አልጋ የነበረው አንድ በጺም የተሞላ እና ከምሥራቅ አውሮጳውያን አገሮች በአንደኛው የትምህርት ቆይታ የነበረው የሚመስል በከፍተኛ ደረጃ የተማረ ሰው የነበር ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ጤነኛ ይመስልና ሌላ ጊዜ ደግሞ መስመሩን ይለቃል። ለማውራት በሚችልበት ስሜት ውስጥ ሲሆን ከእኔ ጋር አንዳንድ ውይይቶችን በመለዋወጣችን ጠልቆ የሚያስብ ሰው እንደ ሆነና አንዳንድ ጊዜም ሐሳቦቹን ለመከተል ከባድ ሆኖ የማገኘው መሆኑን ብዙም ሳልቆይ አስተዋልኩ። ላርጋክቲል የሚባለውን እንክብል ልትሰጠኝ ነርሷ በመጣች ቍጥር በአፌ ውስጥ አስገብቼ በምላሴ ሥር በማቆየት እንደ ዋጥኩት አስመስዬ ወዲያውኑ አወጣውና ነርሷ ስትሄድ እንክብሉን በእጄ አውጥቼ ወደ ሽንት ቤት እወረውረዋለሁ።

ለሁለት ሳምንት ገደማ በቆየሁበት በዚያ ሆስፒታል ሁሉም ዓይነት የአእምሮ በሽተኞች ዘግናኝ ባሕርያትን በሚያሳዩበት ቦታ ሕይወትን የመምራት ፈጽሞ ያልተለመደ ገጠመኝ ስላሳለፍኩ፣ ልምምዶቼን በዕለት ውሎ መመዝገቢያዬ ላይ እጽፋቸው ነበር። ትኩረቴን የሳቡትን የተረጋገጠ የአእምሮ በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ያልተለመዱ ባሕርያት በአትኩሮት መዝግቤያለሁ። ስለሚጽፈው ነገር ምንም ነገር አይግለጥልኝ እንጂ፤ ደግሞም መልከት እንኳን እንዳደርገው ዕድሉን አይሰጠኝ እንጂ፣ ከጎኔ የነበረውም ሰው እንዲሁ በብዛት

ይጽፍ ነበር። ሁለተኛው ሳምንት ላይ የተሳካ የሥነ-ልቦና በሽታዬ የታከመበት ሁኔታ ውስጥ እንዳለፍኩ እና የተለመደውን መደበኛ ሕይወቴን መቀጠል እንደምችል በሚገልጽ ወረቀት ከሆስፒታል ተለቀቅኩ። ያን ጊዜ ከመንግሥት ማስገደጃዎች ነጻነት ማግኘት ብለን የምንጠራውን ነገር ለመጨበጥ ስል ያንን ሠነድ ለመጠቀም ፈልግሁና የሚያመጣው አደጋ ቢገባኝም፣ እንደ ሰበብ ልጠቀምበት እንደማያስፈልገኝ ሆኜ በምትኩ ሳልተወሰነ ጊዜ አዲስ አበባ ልቆይ ወሰንኩ።


እኔና ጓደኞቼ በአብዮቱ ዘመን

አዲስ አበባ ውስጥ ጓደኞቼን በተደጋጋሚ ማግኘት ስጀምር ከሁሉ በላይ የዘመቻ ልምምዴን እና በአእምሮ ሕክምና ጣቢያ የሠራሁትን ጀብድ ከነገርኩት ከአሠልጣኜ ተከ ጋር መቀራረቡን አጠናከርኩ። እርሱም ከቅን ልቦናው የቆመ ማርክሲሳዊ አድርጎ በማየት በትንሹም በትልቁም ከእኔ ጋር ስለ ቆመ፣ በዋናነት ለበርጫዬ እና ለሲጋራ የምጠቀምበትን አንዳንድ የገንዘብ እገዛዎችን ያደርግልኛል። ከእርሱ በተጨማሪ ከመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም (ቲቲአይ) የመጣው ጌሪ እና ከወታደራዊ አካዳሚ የመጣው ተከሉ አንዳንድ ጊዜ የገንዘብ እገዛ ያደርጉልኛል። ምንም እንኳን ተራማጅ ሰው ባይሆንም፣ እኔን ጨምሮ አንዳንድ ተራማጅ ሰላማዊ ጓደኞቹ ለሆንነው የሆነ ዓይነት ኀዘኔታን ያሳየን የነበረው እና ሐረር ውስጥ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ የቅርብ ጓደኛዬ የነበረውን ወታደራዊ መኮንን ተከን አንድ ጊዜ አገኘሁት። የተበጫጨቀ የልብስ ሁኔታዬን አይቶ ወደ መርካቶ ወሰደኝና አዲስ ልብሶችን ገዝቶልኝ ለሌላ ማንኛውም ፍላጎቴ ተጨማሪ ገንዘብ ሰጠኝ።

እንደ ሰሎ ባር/ኔቪ እና ጆሊ ባር ባሉት የአብዮተኞች መገናኛ ቦታ ከጓደኞቼ ጋር ለመገናኘት ወደ አራት ኪሎ እየሄድኩ በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ በዋናነትም የኢትዮጵያ አብዮት ወደ የት እየሄደ እንደ ሆነ እና የቀረው ሚና በጥቅሉ ምን እንደ ሆነ ማብቂያ የሌላቸው ውይይቶችን እናደርግ ጀመር። በአራት ኪሎ ዙሪያ የሚገኙት ቡና ቤቶች እውነተኛ እና የሚያንቀሳቅስ ንግግር





ያላቸው አብዮተኞች ያነበቧቸውን የቅርብ ጊዜ መጻሕፍት እና ያገኟቸውን የቅርብ ጊዜ ሐሳቦች ለመወያየት የሚገናኙባቸው ቦታዎች ሲሆኑ፣ በእነዚህ ቦታዎች ላይ ብሩህ የፊዚክስ ተማሪ የነበረውን አፈወርቅን፣ የሕግ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆነውን ተክለአብን እና ሌሎችን ያገኘሁበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። በዚህ ጊዜ የዘመቻ ተማሪዎች ተስፋ መቁረጥ ወደሚንተከተከበት ደረጃ ላይ ደርሶ ስለ ነበር፣ አንዳንዶቹ ጣቢያዎቻቸውን በመተው ወደ አዲስ አበባ መመለስ ጀምረዋል። በቆላ ድባ በነበርኩ ጊዜ እንኳን እንቅስቃሴውን ወደ ስፍራ ማስለቀቅ እንዲቀየር ጥረት ማድረግ ጀምረን ነበር። ስፍራ ማስለቀቅ ሲባል ዘመቻው እንዲቆም ማስደረግ ማለት በመሆኑ፣ ዘመቻው ፈጽሞ እርባና-ቢስ እንደ ሆነ የእውነት ተሰምቶኝ ተማሪዎቹ ስፍራቸውን እንዲለቅቁ ብርቱ ተሟግቼያለሁ። መንግሥት እየበዘበዘንና ሆነ ብሎ ተስፋ እያስቆረጠን እንደ ሆነ ጠቅለል ያለ ስሜት በተፈጠረብን ወቅት፣ በመንግሥት ሳይጠበቁ በቀደሙት ፖሊሶች ዘመቻ ጣቢያዎቻቸው ውስጥ የተገደሉ በርካታ ጓደኞቻችን እንዳሉ ዜና ሰማን። ከእነርሱም መካከል በመጠኑ እውቃት የነበረችው መሲ አንዷ ስትሆን፣ እርሷም በከፋ ክፍለ-ሐገር ውስጥ ሕይወቷን ያጣች የሳይንስ ተማሪ የነበረች የድሬዳዋ ልጅ ነበረች።

ከዘመቻ ጣቢያዎች በርከት ያሉ ተማሪዎች እየተመለሱ በመጡ ቍጥር አራት ኪሎ አካባቢ ወቅታዊ አዝማሚያዎች ለውይይት የሚቀርቡበት እና አዳዲስ ሐሳቦች የሚፈለፈሉበት የተማሪዎች ፖለቲካ መናኸሪያ ሆነ። እሁን ምንም የፀተነ ወይም የትኛውም ዓይነት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን የሚሰበስብ የተማሪዎች ኅብረት ባለመኖሩ፣ እዚህ እና እዚያ መዋለላችን ቀጠለ። ተማሪዎች ስፍራቸውን የሚለቅቁበትን ሂደት ወዲያውኑ ተግባራዊ እንዲደረግ ብዙዎቻችን እየገፋንበት ሄድን። የሙግታችን መሠረት ዘመቻዎቹ በትክክል ያልታቀዱ፣ በመጥፎ ሁኔታ የተቀናጁ እና ከሁሉ በላይ ደግሞ በአብዮቱ ሂደት ላይ ተማሪዎችን ንቁ ሆነው ከሚሳተፉበት ፖለቲካ ለማሰናከል የተነደፈ ነው የሚል ነበር። አደጋ ያለበትንም ነገር ስናነሣ ተማሪዎቹ ጥበቃ የማይደረግላቸው እና ያልታጠቁ በመሆኑ ለበርካታ አደገኛ ሁኔታዎች የተጋለጡ መሆናቸውን ጠቆምን። በዘመቻው የሚሳተፉት ተማሪዎች በቀደመው አገዛዝ የማኅበራዊና ምጣኔ-ሐብታዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸውን ማስከበር በሚፈልጉት ሰዎች ጥቃት ሊፈጸምባቸው የሚችልበት ሁኔታ ውስጥ እንደ ሆኑ ሪፖርቶች ደረሱን።

በድንገት፣ አራት ኪሎ አካባቢ ያለው ውይይት ጎልቶ ወደሚጠናከርበት ሁኔታ መቀየር ሲጀምር፣ ከሐረር የመጣውና የሕግ ትምህርት ቤት ተማሪ የነበረው ሮብ እንደዚህ የሚል የሙግት ነጥብ ይዞ መጣ። "የሰፊውን ሕዝብ ጉዳይ በአሸናፊነት አጠናቅቀናል። የዘመቻው ተሞክሯችን የመደብ ጦርነቱ እየተስፋፋ ወዳለበት ወደ ሕዝቡ መካከል አምጥቶናል፣ ስለዚህም ተማሪዎቹን ከስፍራቸው ማስለቀቁ ክህደት እና አሳልፎ መስጠት ነው።" ሁኔታው መጀመሪያ ላይ እኔ ያላስተዋልኩት አዲስ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ምሥረታ እየተካሄደ የነበረበት ሲሆን፣ ሮብ ተማሪዎችን ስፍራ ከማስለቀቅ ተቃራኒ የሆነውን ሐሳቦች "ስሕተቶችን የማስተካከል" ሂደት በማለት ሲያብራራቸው፣ ለእኔና ለብዙ ሌሎች ኋላ ላይ ግልጽ እየሆነልን መጣ። ስሕተቱን የማስተካከሉ እንቅስቃሴን የሚያራግቡት አንዳች ዓይነት ውስጥ ለውስጥ የሚንቀሳቀስና ኋላ ላይ ስም ይዞ በግልጽ የሚታወቅ የፖለቲካ አጀንዳ ይዘው የወጡ ነበሩ። የተማሪዎቹን ስፍራ የማስለቀቅ ተቃራኒ ዘመቻ ወደ ፊት እየገፉበት መሄድ ጀመሩ። ለየት ያሉት ንድፈ-ሐሳቦች የዳበረውን አቋሜን በፍጥነት እየተካ የሚቀለብስ በመሆኑ፣ ለእኔ ይህ እንግዳ እና ያልተለመደ እድገት ሆኖ ነበር የታየኝ። ግራ ተጋባሁ ደግሞም ትንሹን እንኳን ለመናገር ምንም ፍንጭ የሌለኝ ሆንኩ። በአዲሱ አሻሚ ሁኔታ መንታ መንገድ ላይ ላለነው ግራ አጋቢው ጥያቄ ምን ማድረግ እንዳለብን ሲሆን - እየተካሄደ ያለው ተማሪዎቹን ካሉበት ስፍራ ማስለቀቅ ወይስ ተማሪዎቹን ወደየነበሩበት ጣቢያዎቻቸው ለመመለስ እየገፋ ባለው የስሕተትን መመለስ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ? የሚል ሆነ።

በአንዳንድ ሊብራሩ ባልቻሉ ምክንያቶች፣ ከብዙዎች በአብዮት ውስጥ ቢመደቡ ከሚመጥኑት አኳያ አቋሙን በፍጥነት ከአንደኛው ጎን ወደ ሌላኛው እንደሚቀያይር አውቅ ስለ ነበር፣ ሮብ የምሩን አብዮተኛ እንደ ሆነ አንዳንድ ጥርጣሬዎችን ለራሴ መያዝ ጀመርኩ። ተማሪ ሆነን ከሐረር ስንመጣ ጀምሮ ሆን ብሎ ሰው በሚሸሽበት ሹልክሉክ የሕይወት ዘይቤው ስለማውቀው፣ ለነበረኝ ጥርጣሬ ያ ራሱ አስተዋጽዖ አደረገ። በሕይወት ውስጥ ማንም ሰው ባለበት ቆሞ አይቀርም፣ ነገር ግን ዘና ማለት የሚወደው እና ተጫዋችነት ያለበት የሮብ ሕይወት ዘይቤ ግን እንደ ፖለቲከኛ ሆኖ አዲስ ከያዘው ሚና ጋር አብሮ አይሄድም ነበር። ያን ጊዜ እንዳየሁት ከሆነ ግን፣ ሽግግሩ በጣም ፈጣን ሆነብኝ።

ሮብ መሟገት የሚችል እና ጉዳዩን በየትኛውም ሁኔታ ማሸነፍ የሚሞክር





ሰው እንደ ሆነ እዚህ ጋ ጨምሮ ሊታከል ይገባል። እርሱ ከዊንጌት ትምህርት ቤት መጥቶ የሕግ ትምህርት ቤትን የተቀላቀለ ሲሆን፣ በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ይልቅ የተዋጣለት እንግሊዘኛ ይናገር ነበር። በጣም አሳማኝ እና ተፎካካሪ ተማሪ እንደ መሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜ የሚንሸራተቱ ሙግቶችን የሚያመጣ ቢሆንም እንኳን፣ አወዛጋቢ በሆኑ ክርክሮች ላይ ጥሩ የሚንቀሳቀስ ሰው እንደ ነበረ አስታውሳለሁ።

ስፍራውን ለቅቆ የመጣው እና ስፍራ የማስለቀቁ ዘመቻ ደጋፊ የሆነው ሌላኛው የሕግ ትምህርት ቤት ተማሪ ተክለአብ ጭምር ከአቋሙ መንሸራተት ጀመረ። በዚያን ጊዜ ሁለቱም እውነተኛ የእኔ አብዮተኞች እና አርአያዎቼ ስላልነበሩ፣ ከእነ ግርማቸው፣ አባ እና ጌታቸው ያሉ በጥቂቱ ከምጠቅሳቸው ሰዎች ጎራ እንኳን አላስቀምጣቸውም። ኋላ ላይ ተክለአብ እንደ ሮብ ያሉ ተማሪዎች እየገፉበት ላሉት አዲስ ሐሳቦች ክፍት እንደ ሆነ ሲነግረኝ፣ ምን እየሆነ እንደ ነበረ እርግጠኛ ባለመሆኔ ያ ሁኔታ የበለጠ ግራ አጋባኝ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ተክለአብ እርሱን ደግፌ ዘመቻ እንዳደርግለት እኔን የጠየቀበት አንዳች ዓይነት ስም የማጥፋት ጥቃት እየተለማመደ እንደ ሆነ ነግሮኝ ከዚያ ብዙም ሳይቆይ በፖለቲካ ማጭበርበር እየተከሰሰ እንደ ሆነ ተረዳሁ።

ብዙም ሳይቆይ፣ ለብዙዎቻችን የማይታይ ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ እየተካሄደ ያለ አዲስ የፖለቲካ መስመር እንዳለ ስላስተዋልኩ ሮብን አገኘሁትና ተማሪዎቹን ስፍራ በማስለቀቅ ጉዳይ ላይ ኮስታራ ውይይት ከፈትኩ። በዚያን ጊዜ አንዳች ዓይነት ንድፈ-ሐሳባዊ ማዕቀፍን በመስጠት በጉዳዩ ላይ አቋሙን በብርቱ ማቀናጀት ጀምሮ የተወሰነ ሄዶበታል። በወቅቱ ግልጽ የሆነ የውስጥ ለውስጥ ግንኙነቶች እንደ ነበሩት ባላውቅም፣ ከተካ ጋር የነበረኝን መገናኘት እንደ ጠበቅሁ በብርቱ ይደግፈው የነበረውን አቋሜን አነግረው ነበር።

ጊዜ በገፋ ቁጥር፣ ስፍራቸውን ለቅቀው የወጡ እንደ ምህድ ያሉ አንዳንድ የቀድሞ ጓደኞቼን አገኘኋቸውና የአልፎ አልፎ በርጫ ጊዜያትን ማሳለፍ ጀመርን። ምህድ ዱራሜ በነበረው የዘመቻ ጣቢያው ቁልፍ መሪ ሆኖ ካገለገለ በኋላ ጠፍቶ የመጣ ሲሆን፣ ወላጆቹ በእርሱ መጥፋት በጣም ተጨንቀው ነበር። አንድ ወቅት ላይ እናቱ ወደ ዱራሜ ሄጄ እንድፈልገው ጠይቀውኝ ለጉዞው እያቀድኩ ሳለ በወንድሜ ድንገተኛ ሞት ምክንያት ሳልሄድ ቀረሁ።[28]

ታሪኩን ቀደም ብዬ በአጭሩ የገለጽኩት፣ በቅጽል ስሙ ጥርኝ የሚባለው

ወንድሜ መላኩ ከዓመታት በፊት ከተጋባበት የሣንባ ነቀርሳ በሽታ የተነሣ በልብ ተዛማጅ ችግር ሲሠቃይ ቆይቶ፣ በዘመዶች እና ጓደኞች፣ በተለይም በአትቴ አበበ የገንዘብ መዋጮ ለተጨማሪ ሕክምና ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣና በጳውሎስ ሆስፒታል ውስጥ እንዲተኛ ተደርጎ ነበር። እንደ ወንድም የሚገባውን ያክል ባይሆንም፣ አልፎ አልፎ አገበኘው ስለ ነበር ብዙ ድጋፍ ይፈልግ የነበረውን እና ከትውልድ አገሩ ሐረር አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ ሆስፒታል የተኛውን ወንድሜን መጠበቅ ሲገባኝ ለፖለቲካ የበለጠ ትኩረት በመስጠቴ ኋላ ላይ ራሴን ወቀስኩ። ለሕዝቡ የጤና ሁኔታ ከመገኘት ይልቅ የሚበልጥ ትልቅ ጉዳይ እንደሌለ አድርጌ አስብ የነበረ ቢሆንም፣ በመደበኛ ሁኔታ አገበኘው ዘንድ ለነበረኝ ብቸኛ ወንድሜ ጊዜ ያልነበረኝ በመሆኔ አሁን ድረስ እጸጸታለሁ። አንድ ቀን ልጎበኘው ሄጄ መሞቱን ስሰማ፣ ነገሩ እውነት እንደ ሆነ ለማረጋገጥ በድኑን እንዲያሳዩኝ ጠየቅኋቸውና እውነትነቱን ሳረጋግጥ ያለማቋረጥ አለቀስኩ። ምንም እንኳን የእርሱ ሁኔታ ተስፋ ቢስ መሆኑን ሐኪሞቹ ነግረውኝ የነበረ ቢሆንም፣ የእውነት ይሆናል ብዬ በፍጹም አላሰብኩም ነበር።

ሐረር ውስጥ በሞራቲ ሆስፒታል ሕክምና ላይ በነበረ ጊዜ ለቤተሰቡ የእርሱ ሕመም የመጨረሻው ደረጃ ላይ የደረሰ እንደ ሆነና ሕይወቱን ማዳን የሚቻልበት ምንም ዕድል እንደሌለ ዶክተሩ ለቤተሰባችን ሲያሳውቅ፣ አለቀስኩና አቅራቢያ ወዳለው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሄጄ እግዚአብሔርን እንዲያድነው ጠየቅሁ። ይህ የእምነት ጉዳይ ሳይሆን፣ ቀደም ብዬ ገልጬው እንደ ነበረው በ1956 ዓ.ም የደረሰው የመኪና አደጋ ትርዒት ገጥሞኝ በነበረ ጊዜ እንደ ተሳልኩት ስዕለት የተስፋ-ቢስነት ነበር። ያኔስ ምንም ቢሆን ትንሽ እምነት ነበረኝ። በዚህ ወቅት ግን ባዶ ነበርኩ ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ፣ ከልቤ ሆኜ ያደረግሁት ነገር ስለ መሆኑ የማውቀው ነገር አልነበረም።

የልጅነቴን አምላክ መከተሌን መቼ እና እንዴት እንዳቆምኩ በትክክል ባላውቅም፣ ዩኒቨርስቲ ከገባሁ በኋላ ያጣሁት ይመስለኛል። ወደ ቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት የሄድኩ ጊዜ ኦርቶዶክስ ክርስትና ውስጥ ባደግሁበት መንገድ በመጠኑ እጾምና እጸልይ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። በእያንዳንዱ ሌሊት 'የለመኑህን የማትነሣ፣ የነገሩህን የማትረሳ አምላክ እርዳኝ' በማለት እጸልይ ነበር። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር እንዲሆን እና በትምህርቴም ስኬትን እንዲሰጠኝ ነበር ጸሎቴ።





ልጅ በነበርኩ ጊዜ ከሞላ ጎደል ለሁሉም እላላክላቸው ስለ ነበር፣ ከብዙ ሰዎች ‹‹እግዚአብሔር ይባርክህ›› የሚለው ምርቃት ደርሶኛል። ምንም እንኳን ከእርሱ ጋር የነበረኝ መያያዝ በምንም ዓይነት ዘላቂ እውነት ላይ የተመሠረተ ባይሆንም፣ እግዚአብሔርን ለመካድ ምንም ዕቅድ አድርጌ አላውቅም። የቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት ስገባ የክርስትናን ሦስቱ የተለያዩ እምነቶች ከምረቃ በኋላ በጥንቃቄ መርምሬ አሳማኝ ወይም ትክክለኛ የነበረውን እንደምመርጥና በዚያም ላይ ለዘላለም ጸንቼ እንደምኖር ራሴን አሳምኜ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል።

ወንድሜ ከፉኛ ታምሞ በነበረበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር እንዲያድነው የቀድሞ የልጅነቴን እምነት ለማምጣት ሞከሬ የወንድሜ ሕመም እየባሰበት በመሄዱ ጸሎቴ እንዳልተሰማ አስተዋልኩ። በውጤቱም፣ ያን ጊዜ ለእኔ የነበረው ትርጉም ምንም ቢሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ የነበረኝ ቅያሜ ጨምሮ በመሄድ ላይ ሳለ የወንድሜ ድንገተኛ ሞት ጥልቅ የሆነ እጦት እና ኀዘን ጣለብኝ። ቤተሰቡ ከተፋታ በኋላ በተለያዩ ቤተሰቦች እንኖር ስለ ነበር፣ ፍቅሬን ለወንድሜ ለመግለጥ ዕድል አግኝቼ እንደማላውቅ ሁልጊዜ ይሰማኝ ነበር። ከእናቴ ጋር ለመሆን ከወሰነው ውሳኔ እንጻር እኔ ከአባቴ ጋር ለመቆየት በመወሰኔ የበለጠ ዕድለኛ ነበርኩ። የወንድሜን የውሳኔውን መሠረት የማላውቅ ብሆንም፣ በውሳኔው ውጤት ግን ተሠቃየ። በመካከላችን ምንም የቀረ ፍቅር ባይኖርም፣ አባቴን ለማየት እና ከእኛ ጋር ምግብ ለመጋራት የሚመጣባቸው ጊዜያት ነበሩ። በአንጻሩ የተሻለ የነበረውን ምግብ እና የአባቴን ትኩረት ይሻማብኝ ስለ ነበረ፣ ለእርሱ ምን ያክል የማያስተናግድ አመለካከት እንደ ነበረኝ አስታውሳለሁ። በቂ ፍቅር ስላላሳየሁትና ወይም ደግሞ ደደር ላይ እስተምር በነበረ ጊዜ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት እንዲያመጣ ስላላበረታታሁት፣ በጸጸት ተሞልቼ ሰነበትሁ። የእኔ ግዴታ እናቴን መርዳት እንደ ሆነ አስብ ስለ ነበረና ደግሞም እናቴን እስከ ረዳሁ ድረስ ያ የሚደነቅ ሥራ ነበር ብዬ ስላሰብኩ፣ እንደ ወንድም እርሱንም መውደዴን ላሳየው ራሴን ባለመዘርጋቴ ተሳስቼ ነበር። ለእልኮል ገንዘብ እያባከንኩ ከፍተኛ የሆነ የሚስማማን ነገር እንደምከተልና ለሰፊው ሕዝብ ጉዳይ እንደ ቆምኩ በእብሪተኝነት እቈጥር በነበረበት ጊዜ ላይ አንዳንድ ርካሽ የሆኑ ልብሶችን በተወሰኑ ጊዜያት እንዴ ገዝቼለት ሊሆን ይችላል እንጂ፣ ገንዘብ ሰጥቼው እንደሆን በጭራሽ አላስታውስም። የታናሽ ወንድሜ ሞት በእያንዳንዱ

የሕይወቴ ገጽታ ላይ የሚደቁስ ውጤት እስኪያመጣ ድረስ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ማስታወሱ ብዙ ጸጸት እና ጭንቀት በነፍሴ ላይ ፈጠረብኝ።

ከወንድሜ ሞት በኋላ "ከዚህ በኋላ ለገዛ ራሴ ሕይወት እና ለወንድሜ ሕይወት እኖራለሁ፤ ሕይወቴ ጥንድ ኃላፊነትን እየተወጣ መሆኑን እርግጠኛ አደርጋለሁ፤" በማለት የምሬ የነበረውን መሐላ ለራሴ አደረግሁ። ጥልቅ በሆነው የውስጥ ማንነቴ ለእርሱ በመኖር እና በኖርኩት ሕይወት ውስጥ ለእርሱ ሐውልትን በማቆም ሞቶ እንዳይቀር አደርጋለሁ ብዬ ሳላስብ አልቀረሁም። ነገር ግን ያንን ቃል ኪዳኔን እንድኖረው የሚያስፈልገኝን ፍልስፍና እና ዘዴዎች ገና አላዳበርኩም ነበር። በተግባራዊው እውነታ ስመዘን ግን፣ መሐላዬ እንዲያው ዝም ብሎ አብዮታዊ ትኩሳቴን ደግሞም ለድሆች ጉዳይ ያለኝን መሰጠት አባባሰው እንጂ፣ ለወንድሜ ቃል የገባሁትን እንድፈጽም አልረዳኝም። ምናልባት ውስጥ ውስጤን በአብዮታዊ ቅናቴ ውስጥ ወንድሜን ማካተት በመፈለጌ ፈጽሞ የተግባር ሰው አልሆንኩም፣ ለመሐላዬም አልኖርኩም።

ይህ በዚህ እንዳለ የገንዘብ ችግሮቼን ለማስተካከል በድጋሚ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ለመሄድ እና በሥራዬ ላይ መቀጠል እንድችል ለመጠየቅ ፀቀድኩኝ። መጀመሪያ ላይ ይህ ምክንያታዊ አይመስልም ነበር፤ ነገር ግን ያንን ለማድረግ መፈለጌን ገፋሁበት። ለሥራ ለመመለሴ ያቀረብኩት ሰበብ ቀደም ብዬ የጠቀስኩት የኢትሳው ታሪክ ነበር። አዲስ አበባ በሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት ውስጥ በሚሠራ አንድ መኮንን ለምን ለማመልከት እንደ ዘገየሁ ማብራሪያ እንዳቀርብ ተጠየቅሁና እኔም ስመልስ ውጣ ውረድ በሚያበዛው አሠራር ተበሳጭቼና ተስፋ ቆርጬ እንደ ሆነ ነገርኳቸው። የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ የአስተማሪዎች ፍላጎት ላይ ስለ ነበሩ፣ ደመወዜ ተቀንሶ በሐረርጌ ክፍለ-ሐገር ውስጥ እንዳስተምር መደቡኝ። የክፍለ-ሐገሩ የትምህርት ጽ/ቤት ሁለት አማራጮችን ሰጠኝ፣ አንደኛው ጂጂጋ አቅራቢያ በምትገኘው ትንሽ ከተማ ጭናክሰን እንዳስተምር ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ በገለምሶ ወረዳ ባለችው በዴሳ ነበር። እኔም ዋናው ጉዳይ የአብዮቱን ጉዳይ የበለጠ ለማራመድ የበለጠ ጠቃሚ የምትሆነው የትኛዋ ከተማ ነች ከሚለው እይታ አንጻር መወሰን ስለ ፈለግሁ፣ ከአብዮት ጓደኞቼ ጋር፣ በተለይም ከአሠልጣኜ፣ ከተክ፣ ጋር ከተማከርኩኝ በኋላ ሁለተኛውን መረጥኩኝ።

ቢዴሳን ለመምረጤ ከፊሉ ምክንያት አካባቢው ያን ጊዜ በዋለልኝ እና





በግብረ-አበሮቹ እየተመራ የነበረና በማርክሲስት አስተሳሰብ ላይ ተመሥርቶ እንደ ተራማጅ ብሔራዊ እንቅስቃሴ ይታይ የነበረው የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር መቀመጫ በመሆኑ ነበር። ግንባሩ ደግሞ በወጣቶች እና በሰፊው የተማረ ኃይል ላይ ፈጥኖ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያደርግ በሚችልበት መልኩ የፖለቲካ ድርጅቶች ድጋፍ ነበረው። እዚህ ጋ ሊጠቀስ የሚገባው ነገር የቀሩት ኢትዮጵያውያን በሚያሳዝንና ባልታደለ መልኩ ወደ ሁለት የፖለቲካ መስመሮች በግልጽ ሲከፈሉ ገና በሚገባ አለመረዳታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ቆየት ብለን እንደምናየው፣ ተሰልቶ የማያበቃ አሳዛኝ ውጤቶችን ጭምር ያመጣባቸው መሆኑ ነው።

## በግጭት ውስጥ መኖር

አዲስ አበባ እያለሁ አንዳንድ የስም ማጥፋት ጥቃቶች በተለያዩ ጥጐች በቆሙት መካከል መካሄድ ሲጀምር፣ የዚህን መከፋፈል አመጣጥ ማየት ቻልኩኝ። ከላይ በ1961 ዓ.ም ገደማ ስም የማጥፋት ዘመቻ አድርጎ የነበረውን የተክለአብን ሁኔታ ገልጬዋለሁ። በሶሎ ባር በነበረን በአንደኛው ውይይት ላይ የእርሱን ታዋቂነት ጭቃ እየቀቡ ያሉ አንዳንዶች እንዳሉ እንድረዳው በማድረግ ስለ እርሱ ሐቀኝነት አዎንታዊ የሆነ መረጃ እንዳሰራጭለት ለመነኝ። ተክለአብ በሌሎች ዘንድ ይታይ የነበረው ሠፈራዎችን ወይም የፖለቲካ አጥናፎችን በተመለከተ ወታደራዊውን መንግሥት በሚደግፍ የግራ ክንፍ በመሄድ አቋሙን እንደሚለዋውጥ ሰው ተደርጎ ነበር። ያን ጊዜ ከተበላሸ ስሙ በስተጀርባ ያጨቃጨቃቸው የፖለቲካ ጉዳይ ምን እንደ ሆነ ሙሉ ሥዕሉ ስላልነበረኝ፣ እንዴት አድርጌ ለእርሱ እንደምቆም ምንም ነገር ማወቅ ሳልችል ቀረሁ።

ቀደም ብዬ መስከረም 1960 ዓ.ም ላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)ን የፖለቲካ መግለጫ አንብቤው ስለ ነበር፣ ጎንደር ውስጥ ሳለሁ በምሥጢር ለቅርብ ጓደኞቼ አሰራጭቼው ነበር። ከውጭ ሆኖ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ይመስለኝ ነበር እንጂ፣ ያን ጊዜ የአገር ውስጥ ሕልውና እና ሕገ-መንግሥት የነበረው ፓርቲ እንደ ሆነ ምንም ፍንጭ አልነበረኝም። ምንም እንኳን ስለዚያ የማውቀው በጣም ጥቂት ቢሆንም፣ ኢሕአፓን ሊቃወም የተነሣ ሌላ ድርጅት እየተፈጠረ እንደ ሆነ ደብዛዛም ቢሆን መረዳቱ ነበረኝ።

በዚያን ጊዜ እስከማስታውሰው ድረስ በሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ከየትኛውም ደጋፊዎች ጋር የመገናኘቱ ፍላጎት አልነበረኝም ነበረና ከዚህ የተነሣ ወደ ኢትዮጵያ አብዮት እየመራቸው ባለው የሚያለያዩዋቸው አቋሞቻቸው ላይ እርግጠኛ የሆንኩበትን ግንዛቤ እና መረዳት አልነበረኝም።

ኢሕአፓ ሐረር ውስጥ ተጽዕኖ ፈጥሮ ተቀባይነት እያገኘ ስለ ነበር፣ የወጣቶችን ልብ እና ነፍስ ድራማዊ በሆነ እና ሊብራራ በማይችል መልኩ አሸነፈ። ቀጣይነት ባለው አብዮት ውስጥ ሚናቸው ምን እንደሚሆን ለመወያየት ግልጽ በሆነ ስብሰባ በይፋ ይገናኙ የነበሩት ወጣቶች በአብዛኛው ከዩኒቨርስቲ የመጡትን ወጣቶች በቀላሉ ፖለቲካውያን ያደርጓቸዋል። የኢሕአፓን አጀንዳ ለማስተዋወቅ እንዳች ዓይነት የውስጥ ለውስጥ ተልዕኮን የሚያካሂዱ ተማሪዎች እንደ ነበሩ በግልጽ ሊስተዋል የሚችል ሲሆን፣ በአንዳንዶቹ በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ እኔም ተሳትፌ ነበር። ደግሞም ከመንደሬ ከጉርሱም የመጡ ወጣቶች በማርክሲሳዊ አሳማኝ ሐሳብ የጋለ ስሜት ኖሯቸው ስለ አብዮቱ ሲናገሩ ማየቴ እያስደነቀኝ፣ እንዴት በአጭር ጊዜ እንደ ተቀየሩ እና በአንድ ሌሊት እንዴት አብዮተኞች ሊሆኑ እንደ ቻሉ በመገረም አስባለሁ። ያ ማለት ለእኔ ምንም ማለት ቢሆን እንኳን፣ ማርክሲሳዊ ሆኖ ለመገኘት ለእኔ ሕመም ያለበት የማንበብ ዓመታትን ወስዶብኝ ነበር።

ረጅም እና ቀጭን ስለ ነበረ በቅጽል ስሙ ወባ እያልን የምንጠራውና በጉርሱም ባለው ሠፈሬ ያደገው ሚሊ ከልጅነት ጀምሮ ዝምተኛ እና ጭምት ልጅ መሆኑን አውቅ ስለ ነበር በእነዚያ ውይይቶች ላይ እንዴት ሆኖ በድፍረት፣ በብቃት እና በነውጠኝነት ሊናገር እንደ በቃ እስከማይገባኝ ድረስ አስደንቆኛል። በአእምሮዬ ጥልቀት ውስጥ አንድ የሚወተውተኝ እና ያልተመለሰ ጥያቄ ነበረኝ፡- "ወደ አንድ ለዐመፅ የሚነሣሣ ቡድንነት እየተቀየርን ነው ወይስ ሥርዓት እንዲይዙ የሚደረጉ አብዮተኞች?" በተገኘሁባቸው ስብሰባዎች ሁሉ ተመሳሳይ ነገር አይቼ ነበር ደግሞም ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቄ ነበር - "ከዚህ ወደየት እየሄድን ነው? ይህ የሐሳባዊነት ጋጋታ ወጣቱን እየተቆጣጠረው ያለው ለምንድን ነው?" በሳምንታት ውስጥ ማርክሲሳዊ አልሆንኩም፣ ይልቅ ማርክሲሳዊ ለመሆን ከ'ክላሲካል ማርክሲዝም' ጀምሮ እስከ አይዛክ ደቼር ትሮትስኪ ላይ፣ እና ከፍራንትዝ ፋኖን ጀምሮ እስከ እንደ ኤድጋር ስኖው ያሉ ኢዩሮ-ማርክሲስትስ ድረስ አንብቤያለሁ። ሰዎች ከሞላ ጎደል በአንድ ሌሊት





በሚያስብል ሁኔታ ማርክሲሳዊ ሆነው ሲቀየሩ ማየት በመቻሌ በእንዲህ ያለ አጭር ጊዜ ሰዎቹ መቀየራቸው የመፍጫ መሣሪያው በፍጥነት እንደሚፈጭ እንዲመስለኝ አደረገ።

## ያልታሰቡ ቀውሶች

ታሪክን ለማስተማር ወደ በዴሳ የሄድኩት በእንዲህ ዓይነት የአእምሮ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ሲሆን፣ በሆቴል ገንዘቤን ከማጠፋ ይልቅ ከትውልድ መንደሬ ጉርሱም ከሆነው ጓደኛዬ ታም ጋር ለተወሰነ ጊዜ በዚያ መቆየቱን መረጥኩ። ከሙስሊም ባለቤቱ ጋር በማያቋርጥ ውጥረት ውስጥ የሚኖሩ በመሆኑ፣ ማቆሚያ የሌለው ግጭት በሁለቱ መካከል የሚካሄድበትን ድራማ እንዲሁም ከሚስቱ ጋጠ ወጥ አያያዝ የተነሣ የሚሰማውን እፍረት ማየት ስላልፈለግሁ፣ ብዙ በመቆየቴ ምቾት አጣሁ። በበዴሳ የነበረኝ አዲስ ሕይወት መጪውን ጊዜዬን ከፉኛ የሚያጠቃ እና ያልተጠበቁ ችግሮችን የማስተናግድበትን የተበረገደ በር ከፈተብኝ።

ከትምህርት ሚኒስቴር በቅድሚያ ክፍያነት የተሰጠኝን ግማሽ ያክል ደመወዝ አራት ኪሎ ሳይንስ ፋከሊቲ አቅራቢያ፣ ከዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ብዙም ሳይርቅ ካለው ታዋቂ መጻሕፍት መደብር መጻሕፍትን ለመግዛት ስለ ተጠቀምኩበት፣ ወደ በዴሳ ስመጣ ከአዲስ አበባ የገዛኋቸውን በርካታ የማርክሲስት መጻሕፍትን አብሬ ማምጣት ቻልኩ። በእርግጥ፣ ከቦርሳዎቼ አንዱ የተሞላው በመጻሕፍት ክምር ሲሆን፣ የአንዳንዶቹን መጽሐፍት ርእሶች፡- *የሌኒን ቱ ታክቲክስ ኦቭ ሶሻል ዴሞክራሲ፣ ዋን ስቴፕ ፎርዎርድ ኤንድ ቱ ስቴፕስ ባክዋርድ፣ ሌፍት ዊንግ ኮሚዩኒዝም አን ኢንፋንታይል ዲስኦርደር፣ የማዎ ፎር ኢሴይስ ኦን ፊሎሶፊ፣ የኤንግል ዘ ኦሪጂን ኦቭ ዘ ፋሚሊ ኤንድ ፕራይቬት ፕሮፐርቲ ኤንድ ዘ ስቴት፣* የሚባሉት ከጥቂቶቹ መካከል የሚጠቀሱት ናቸው።

ታሚን፣ የዩኒቨርስቲው ምሕንድስና ተማሪ ዮኒን፣ ተሼን፣ እኔን እና ሌሎች ብቅ ጥልቅ እያሉ ከእኛ ጋር የሚገናኙ አንዳንድ ተማሪዎችን ያካተተ የጥናት ቡድን በታሚ ቤት ውስጥ ለማዋቀር ብዙ ጊዜ አልወሰደብኝም።

በዴሳ በደረስኩ ጊዜ ከተማሪዎች ኢድማ የተነሣ ትምህርት አልነበረም።

ነገር ግን አስተማሪዎች በየዕለቱ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱና እንዲፈርሙ መመሪያ ተሰጥቷቸው ስለ ነበር፣ እዚያ ሄደን ቀኑን ምንም ሳንሠራበት እናሳልፋለን። አንዳንድ ነጥብ ላይ መንግሥት ፖለቲካዊ አስተሳሰቡን በሌላው ላይ የሚጭንበትን የውይይት ክበብ የተባለ አሠራር ይዞ በመምጣት የጥናት መጻሕፍትን አዘጋጅቶ እያንዳንዱ የመንግሥት ቅጥረኛ አርብ ላይ ይህንን የጥናት መጽሐፍ ለማጥናት ጊዜ መመደብ እንዳለበት ደነገገ። ይህም ስልት ቅጥረኞችን በማርክሲሳዊ አስተሳሰብ ለመሙላት እና ሁሉንም ሰው ወደ አብዮቱ ለመሜን የተነደፈ መሆኑ እየገባኝ የውይይት ቡድኑን ተቀላቅዬ ሳይ፣ አብዛኞቹ አስተማሪዎች ማርክሲዝም እና ሌኒንዝም ምን እንደ ሆነ ፍንጩም እንኳን እንደሌላቸው ደረስኩበት።

ጣልቃ ገብቼ ንቁ የሆነ ሚና መጫወቱን መጀመሪያ ላይ አቅማምቼበት የነበረ ቢሆንም፣ ኋላ ላይ ግን ማቅማማቴን ትቼ ዘው ብዬ መግባት ስጀምር፣ ተሳትፎዬ በሠራተኞቹ መካከል ቅይጥ የሆነ ስሜቶችን አመጣ። በእርግጥም፣ በአስተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ የነበረው ጥያቄ፣ "የምንወያየውን መጽሐፍ አብዝቶ የሚያውቀው ይህ እንግዳ ማን ነው?" የሚል ቢሆንም፣ እኔ ግን ከፊት ያለውን አደጋ ሳስተውል አልቻልኩም። የሕይወቴ ተልዕኮ ብዬ ያልኩትን ማርክሲዝምን የማስፋፋትን እና ሰዎችን ወደ አብዮተኝነት የመለወጥን ሚና ብቻ እየተጫወትኩ እንደ ነበር ስላሰብኩኝ፣ በውይይት ክበቡ ንቁ ድርሻን እንድወጣ ያደፋፈረኝ ዋናው ነገር በኃላፊው ጊዜ ውስጥ በእኩዮቼ ዘንድ አግኝቼው የነበረው ተቀባይነት ነበር። በእኔ የማርክሲስት ፍልስፍና እና የሐሳባዊነት እይታ በሰፊው ተጽዕኖ ያደረግሁባቸው በተለይ ከትውልድ አገሬ የሆኑ በርካታ ጓደኞች ሲኖሩኝ፣ ከእነርሱም ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል ካሱ (ፋሎ)፣ ሚሊ፣ ቴንስ፣ እና ግርማ ናቸው። ይህ ቦታ ግን እንግዳ እና ማንም ሰው በጥሩ ሁኔታ እኔን የማያውቅበት፣ ስለ እኔም የሚታወቅ አንድ ነገር ቢኖር፣ በጊዜው የኩራት መታወቂያ ከሆነው ከዩኒቨርስቲ የመጣሁ አስተማሪ መሆኔን ብቻ ነበር።

የጥናት ክበቡ መጀመሪያ ላይ በታሜ ቤት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ እያለ፣ ብዙም ሳልቆይ የደረስኩበት ነገር ታሜ ራሱን ማርክሲስት ብሎ ለመጥራት የለየ እና ከሃዲ እንደ ሆነ ነበር። የኒ ልክ እንደ ሁሉም በየመንደሮቻቸው እንዳሉ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሁሉ በማርክሲዝም ርእሰ





ጉዳይ ላይ ሥልጣን እንዳለው ሰው ተደርጎ የሚታይ የከተማዋ መሪ ተደርጎ የሚቆጠር ሰው ሆኗል። ጥናታችንን እያደረግን እያለ፣ ለእያንዳንዱ እኔ ለማቀርበው ሙግት ሐሳብ፣ አቋሜን እውነት እንደ ሆነ ለማስረገጥ ከነበሩኝ መጻሕፍት ማስረጃን ማምጣት ስለ ነበረብኝ፣ ለበርካታ ጊዜ እርስ በርስ አንስማማም ደግሞም አንዳንዴ ወደ ተቀጣጠለ የሐሳባዊ ጭቅጭቆች ውስጥ እንገባለን። በዚህ መልኩ መወያየቱ ደግሞ ጥቂት ገጾችን ማገላበጥን እና ከሌኒን ወይም ማዎ መጻሕፍት ተገቢውን ማጣቀሻ ማግኘትን ይጠይቃል። ታሜ ነጥቦቹን በማስረጃ ማስደገፍም ሆነ ስሕተቶቹን አምኖ ለመቀበል የሚችል ሰው ባይሆንም፣ እኔ ግን አብዛኛውን ጊዜ ባልኩት ነገር ላይ ትክክል ነበርኩ። እርሱ አሳማኝ የሆነውን ወደ ጠረጴዛ ያመጣሁትን ማስረጃ ሰምቶም እንኳን ወደ መስከን የማይመጣውና በግትርነቱ የሚጸናው ምናልባት የበዴሳ ከተማ አብዮት መሪ አድርጎ ራሱን ከማየቱ የተነሣ ሊሆን ይችላል። በዘመኑ  ምናልባት ከእውነታው ጋር ተስማምቶ መሄድ አልቻልኩኝም፣ ወይም ከየት እንደ መጣ ማየት እስከማልችል ድረስ እብሪተኛ ሆኜ ሊሆን ይችላል፣ አሊያም ኋላ ላይ ልከፍለው ያለውን ዋጋ ከግምት በሚያስገባ መልኩ የአካባቢውን ኃይላት ለማስተዋል ብልህ አልነበርኩም ይሆናል።

ብዙም ሳይቆይ፣ የመንግሥት ደጋፊ ከሆነ የፖለቲካ ድርጅት በአንደኛው የተመደብኩ እንደ ሆነ ተደርጎ አንዳች ዓይነት ወሬ በከተማዋ ውስጥ እየተዘዋወረ እኔ በማላውቀው መልኩ ከጀርባዬ አንዳች ነገር መካሄድ ጀመረ። እንዲህ ዓይነት መንግሥትን የመደገፍ ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች ባንዳ ወይም ከ መኤሶን (የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ) መሪዎች አንዱ በነበሩት ኃይሌ ፊዳ በተገኘው ስም ፊዳሰት ተብለው ይጠራሉ።[29] በተለይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዘንድ አንድ ወገን መያዝ በተማሪዎች ፖለቲካ ድባብ ውስጥ አዲስ ነገር ባይሆንም፣ እውነተኛ ተከታይ አይደለም ተብሎ ለሚታሰብ ለየትኛውም ሰው የሚፈጠሩና የሚለጠፉበት "ፃፊዎች፣ ሰውር አክሻፊዎች፣ አመናፋሾች፣ ትውፊተኞች፣ በመጠኑ የቡርዦዋ ቡቡዎች፣ ጀብደኞች፣ ወግ አጥባቂዎች›› እና የመሳሰሉት ዓይነት ስሞች ይዘጋጁለታል። ይህ ሁኔታ የማግለል ፖለቲካ ክፉል ገጽታ ቢሆንም፣ ያኔ ግን እየጨመረ የሄደ የሚመስለው የአንድን ሰው ስም በመጠቀም ማግለሉ እና ማስፈራራቱ በሁላችንም ዘንድ እንግዳ ክስተት ሆኖ ነበር።

ለልፋቴ ይገባኛል ብዬ ያሰብሁት ይህንን ነው ብዬ ባላምንም፣ አዲሱን የተለጠፈብኝን ስም ከብዙ ግራ መጋባት እና ብስጭት ጋር ስቀበል፣ በፖለቲካዊ እምነቶቼ ጫፍ ድረስ የተሰጠሁ ታማኝ አብዮታዊ ሆኛለሁ በሚለው ግምት ውስጥ ነበርኩኝ። ከዚህ የተነሣ ያለማወላወል ትክክል ነው ብዬ እምን ለነበረው ጉዳይ ከትምህርት ቤት መታገድን ጨምሮ ዋጋ ከፈልኩ፣ በበርካታ አጋጣሚዎች ሕይወቴን አደጋ ላይ ጣልኩኝ፣ ወደ አእምሮ ሕክምና ጣቢያ እስከገባ ድረስ የሥነ-ልቦና ችግር የደረሰበት ሰው መስዬ ለመታከም ራሴን እስከሰጥ እና ስሜን አደጋ ላይ እስከጥል ድረስ ሄድኩኝ። ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ ግን፣ አሁን ላይ ራሴን እየቀጠለ ባለው አብዮት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መስጠት አለብኝ ብዬ በማስብበት ከፍተኛና ወሳኝ ጊዜ ላይ ሕይወቴ ያልተጠበቀ የአቅጣጫ ለውጥ ሲያደርግ ማየት በጣም የሚያስደንቅ ነበር። ልክ እንደ እኔ ጀግና ቼ ጉቬራ መሥዋዕትነት የከፈሉትን ለመምሰል ሞት እስከመኝ ድረስ የአብዮቱን ጉዳይ ወደ ተሳካ ድምዳሜ ለመውሰድ የሚነድድ መሻት ነበረኝ።

በሂደት ላይ ስላለው እና ምንም ነገር ስሜት ስለማይሰጠው፣ ስላልተገነዘብኩት በማበብ ላይ ያለው የፖለቲካ አዝማሚያ ባሕርይ እና ድባብ በመጨነቅና ተስፋ በመቁረጥ ሆኜ በጥልቀት ማሰብና ማመዛዘን ጀመርኩ። በአካባቢዬ እየሆነ ባለው ግራ የሚያጋባና ጭጋጋማ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ቢያንስ በዚህ አዲስ ድባብ በስተጀርባ ያለው ማን እንደ ሆነ የእውነት ላገኘው አልቻልኩም። ያ ብቻ አይደለም፣ እንደ ከስተትም እንቆቅልሽም የሆነብኝን የጉዳዩን መነሻ ሥር የምችለውን ያክል ፈልፍዬ ለማውጣት ጣርኩኝ፣ ግን ከንቱ ጥረት ነበር። ያን ጊዜ የቅድመ-ሕክምና ትምህርት ክፍል ተማሪ የነበረውና አዲስ አበባ ውስጥ ከተከ ጋር በጥብቅ ይገናኙ ወደ ነበረው ሺም ደብዳቤዎችን ከጻፍኩለት በኋላ ለደብዳቤዬ በሰጠኝ ምላሽ በእነዚያ ዘመናት እየተጋፈጥኩ ላለኋቸው ችግሮች በባሕርዬ ቆፍጣና ላልሆንኩበት ተራ ምክንያት በከፊል ተጠያቂ እንደ ሆንኩ አስታወቀኝ። ከእርሱ እይታ አንጻር፣ ሰዎች በጣም በቀላሉ ያላግባብ እንዲወነጅሉኝ ሰበብ የነበረው ያ ሁኔታዬ ሲሆን፣ አሁን ባለሁበት ሁኔታ ውስጥ ሆኜ የአተያዩን ዐወድ ለመተንተን እንድችል ደብዳቤው በኖረኝ ብዬ እመኛለሁ። በማስበውና በምናገረው በጣም ቀና ሰው እንደ ነበርኩኝ ብቻ ሳይሆን፣ እምነቴን ሳልፈራ ለሌሎች ለማካፈል በጣም ክፍት እንደ ነበርኩ እውቃለሁ። በሌሎች በቀላሉ እንደማልወሰድ ወይም ያስቀመጡትን





እውነታቸውን ለእኔ እስከማምንበት ድረስ አቋም እንደማልወስድ ጭምር እውቃለሁ።

በአብዮቱ የጅማሬ ዘመን ላይ እንደ ኤፍሬም እና መኮንን ካሉ ሰዎች ጋር ሐረር ውስጥ በነበረው የበርጫ ቆይታ ላይ ሆነን ስንወያይ፣ በግራ በኩል እየተነሣ ያለው የፓርቲዎች ክፍፍል ገና በጣም ያልበሰሉ መሆናቸውን እንደሚጠቁም በግልጽ ማካፈሌን አስታውሳለሁ። ይህም ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያን አብዮት አቅጣጫ በተመለከተ እንደ ሌሎቹ ጥንታዊ አብዮቶች ያለውን አካሄድ መስመር የያዘ ባለመሆኑ፣ በጣም እርግጠኛ እንዳልሆንኩበትም አብራርቼላቸዋለሁ። ያነሣሁት ጥያቄ፣ "ኢትዮጵያ በከፍተኛና ዝቅተኛ የመደብ ልዩነት ዴሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ ሳታልፍ ወደ ማኅበረሰባዊ አብዮት እንዴት ልትሸጋገር ትችላለች?" ግራው በንድፈ-ሐሳባዊው ክርክር ደግሞም በ20ኛው ምእተ-ዓመት የመጀመሪያዎች አሥርት ዓመታት የተከሰተውን በቦልሸቪኮች እና በሜንሸቪኮች መካከል የነበረውን ክፍፍል እንኳን አላሳለፈም። በጉዳዮ ላይ ኢታገል ስለ ነበረ፣ በከፍተኛ ሁኔታ እያሰብኩበት የእውነታችንን ተወያየንበት፣ ነገር ግን የምር ነገሩን ፈትተን ስለ መለያየታችን ምንም ትዝ አይለኝም። ሁለቱም ኤፍሬም እና መኮንን ጥርጣሬዬን ላካፍላቸው ምቾት የሚሰጡኝ ኮስታራ አእምሮ የነበራቸው ምሁራን እና ገለልተኛ የአስተሳሰብ ሰዎች ስለ ነበሩ፣ ያንኑ ጥያቄ ለሽሜ ጠየቅሁት። ምላሹን የእውነት ባላስታውስም፣ የማስታውሰው አንድ ነገር ራሴን ገትሬ እንድጋፈጠው "ቆፍጣና ሁን!" የሚለውን ምክሩን ብቻ ነበር።

በበዴሳ የነበረው መጥፎ ስም የመስጠት ሁኔታ በተለይ የተሜን ቤት ትቼ ከወጣሁ በኋላ የበለጠ ሕዝብ ዘንድ የደረሰ ሆነ። የእርሱ ስብእና፣ ከባለቤቱ ጋር ያለው ግንኙነት እና የማርክሲሳዊ ሕይወት ያለው ለማስመሰል መሞከሩ እኔን ያፈነኝ ነገር ሆኖ በመስንበቱ፣ አንድ ሌሊት ላይ ሻንጣዬን ይዤ ክፍል ወደ ተከራየሁበት ሆቴል ሄድኩ። ይህ ውሳኔዬ፣ ያን ጊዜ በቀን 2 ብር ብቻ የነበረውን ሆቴል የምከራየው ከማስተምርበት የሥራ ገቢ በተጨማሪ ሌላ ገንዘብ ስለማገኝ እንደ ሆነ አድርገው ሐሜት እንዲያሰራጩብኝ ስላስቻላቸው፣ የነበርኩበትን ሁኔታ ጭራሽ አባባሰው። ቀጥሎም፣ እነዚያን ሁሉ መጻሕፍት በራሴ ልገዛ እንደማልችል፣ ነገር ግን አንድ ሰው ወይም አንዳች የፖለቲካ

ድርጅት እነዚያን ለእኔ እንዳዘጋጀልኝ የተወራበት ሌላ አሉባልታ ስለ መጸሕፍቴ መጣ። ከዚያም የእውነትም ያን ጊዜ የማይቻል የነበረውን፣ የዘመቻ ሰፍራዬን ከለቀቅሁ በኋላ እንዴት በድጋሚ የአስተማሪነትን ሥራ ላገኝ እንደ ቻልኩ አወዛጋቢው ጉዳይ ተከትሎ መጣ። ያንን የግሌ ምሥጢር አድርጌ ይዤው ስለ ነበረ፣ እንደ ካሱ እና ጢቆ ያሉ ቅርብ የሐረር ጓደኞቼ ብቻ በቀር ማንም ሰው ሥራ ያገኘሁበትን ምሥጢር አያውቅም ነበር። የበዴሳ ሐሰተኛ አብዮተኞች እነዚህን ሁሉ ጫፎች አገናኝተው በአካባቢው ላይ ለመንግሥት ደጋፊ ድርጅቶች ለማገልገል ተልኬ የመጣሁ እንደ ሆንኩ አድርገው በመደምደማቸው፣ ለእኔ ተሰጥተውኝ የማያውቁትን ልብ የሚሰብሩ እንደ *"ፊዳሊስት"* ወይም *"ባንዳ"* ዓይነት ስሞች በዚያን ጊዜ ሰጥተውኝ ነበር።[30]

ሁኔታውን ለማብራራት እና አሉባልታውን ለማስተባበል አንዳንድ ጥብቅ ዘመቻ ማድረግ ብፈልግም፣ ታሪኬን ለመስማት እዚያ የሚገኝልኝ ሰው ጠፋ። አሉባልታዎች ከአንደኛው *የበርሜ* ክበብ ወደ ሌላኛው በፍጥነት የሚዘዋወሩ በመሆናቸው፣ አንድን ሰው መጥፎ ስም ለመስጠት እና ስሙንም በወጣቶች መካከል አበላሽቶ ለማሰራጨት አንድ ቀን ይወስዳል። ገና ልጆች ለሆኑት ወጣቶች ነገሩን በጥንቃቄ ለመተንተን እና የፍርዳቸውንም ውጤት ለመገምገም ምንም ጊዜ ያልነበረ ሲሆን፣ በእነርሱ በኩል ሁኔታውን ሊያስቡበት ፈቃደኞች የነበሩ ቢሆንም፣ ከሚፈለገው የትንታኔ መሣሪያ አኳያ ነገሩን በጥልቀት ለመመርመር እንዴት ይችላሉ?

አንድ ቀን ተማሪዎቼ ሜይዴይን (ዓለም አቀፍ የላባደሮችን ቀን) ለማክበር ሰልፍ ሲወጡ እኔም በሙሉ ልብ ሆኜ ሰልፉን ተቀላቀልኩ። በቀደመው አብዮት የጅማሬ ዘመናት ላይ አዲስ አበባ ውስጥ የተካሄደውን የሙስሊሞች ሰልፍ ማስታወቂያዎችን በመጻፍ እና እንደ ማሃ ካሉ ጓደኞች ጋር መፈክሮችን በማሰማት መካፈሌ ሊታወስ የሚገባው ነገር ሆኖ ሳለ፣ የዚህኛውን ሕዝባዊ ሰልፍ ሲያደራጁ ልረዳቸው በዚያ ባለመገኘቴ ግን ከፋኝ ተሰምቶኛል። በቀደመው አብዮት ወቅት፣ በሴቶች ሰልፍ ላይ እንኳን መፈክሮችን በማዘጋጀት እና ማስታወቂያዎችን በመጻፉ በኩል የበኩሌን እስከወጣ ድረስ በአውራ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁልጊዜም ግንባር ላይ ሆኖ መቅረብ የምፈልግ ሰው ነበርኩ። በበዴሳ የተከሰተው ያልተጠበቀ ሁኔታ በየትኛውም ዓይነት ከአብዮቱ ጋር የተያያዘ ሕዝባዊ ክስተት ላይ የምሳተፍበትን ዕድል ገደበብኝ።





በዚያ ቀን መፈክሮችን እያሰማሁ እና ራሱን የሾመውን ወታደራዊ መንግሥት እየተቃወምኩ እና የሽግግር ሕዝባዊ መንግሥት (እርሱም የኢሕአፓ ተቃዋሚ ቡድኖች የነበሩት) እንዲመሠረት እየጠየቅሁ ስሰለፍ፣ አንድ ሰው ከዳተኛ እና የሕዝቡ ጠላት እንደ ሆንኩ በማውገዝ ከኋላዬ ግዙፍ ቡጢ አሳረፈብኝና መሬት ላይ ዘረረኝ። በሁኔታው በአካል ተጎድቼ የነበረ ሲሆን፣ በስሜቴ ደግሞ ከዚያ በላይ ቆስዬ እያለቀስኩኝ ወደ ሆቴል ክፍሌ ሄድኩ። በአጋጣሚው ብቻ ሳይሆን፣ ያዘነልኝ እና ከቁብም ያስገባኝ አንድም ሰው ባለመኖሩ ጭምር ደንግጬ ለብቻዬ በዋልኩበት ሁኔታ ውስጥ አንዲት ወጣት ልጃገረድ ብቻ ማምሻው ላይ ጎበኘችኝ። ይህች ልጅ እኔን እና ጥቂት ሌሎች የዘመቻ አስተማሪዎችን በኮንትራት ውል የምትመግበን ሴትዮ ልጅ ነበረች።[31] በእያንዳንዱ ምግብ የሚቀርብበት ሰዓት ላይ ከሚያስተናግዱን አንደኛዋ ልጅቷ ስትሆን፣ በሌሊት መጥታ ሁኔታዬን አጣራችና በሚያባብለው የአይዞህ ንግግሯ ማዘኗን ገለጸችልኝ። ባለሁበት ግራ መጋባት ውስጥ የእርሷ ጉብኝት ለእኔ ብዙ ነገር ማለት ስለ ሆነ፣ የሕዝቡ ጠላት ተደርጎ ስም የወጣለትን ሰው ለማጽናናት ራሷን አደጋ ላይ ለጣለችው ለዚያች ወጣት እና ብርቱ ልጃገረድ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ደደር ላይ አስተማሪ ከሆንኩ ጊዜ ጀምሮ፣ በቆላ ድባ የዘመቻ ጣቢያ ከነበረኝ የጠጪነት ሁኔታ በላይ ከሞላ ጎደል በየቀኑ እስኪባል ድረስ የምጠጣ ሰው ሆንኩ። በበዴሳ ከተሰጠኝ መጥፎ ስም በኋላ የአልኮል ፍጆታዬ አሳሳቢ በሚሆን መልኩ መጨመሩ ሳያንስ፣ ለዓመታት ያክል በታሰርኩበት አጫሽነቴም ገፋሁበት። መጥፎ ስም ስለ ተሰጠኝ፣ በጥልቀት ተቀይሜ ነበርና የበለጠ ከመጠጣት እና የበለጠ ከማጨስ በስተቀረ ጭንቀቴን የማሸንፍበት ሌላ መንገድ አልነበረኝም። ከብዙ ጊዜ አንድ ጊዜ እየመጣች የምትጎበኘኝ ፍሬዝ የምትባልና በአለማያ ዩኒቨርስቲ የምትሠራ የሴት ጓደኛ ነበረችኝ። ፍሬዝ በፍጥነት እንዳገባት ያለማቋረጥ ትለምነኝ የነበረች ኮስታራ ልጃገረድ ስትሆን፣ እኔ ደግሞ ከእርሷ ፍላጎት በተቃራኒ አብልጬ እፈልግ የነበረው ራሴን በአብዮቱ ማዕከል ላይ ለማኖር እና ከማግባትም ይልቅ በራስ ላይ ያላተኮረ ሕይወት መኖር ብቻ ነበር። አልፎ አልፎ ታደርገው የነበረው ጉብኝቷ የተጨነቀውን ልቤን ያሳረፈልኝ፣ ደግሞም በበዴሳ እንድኖረው በተገደድኩት የብቸኝነት ሕይወት ውስጥ ለነፍሴ ደስታን ያመጣልኝ ቢሆንም፣ ለጋብቻው ዝግጁ ባለመሆኔ

እርሷን ማራቁን ቀጠልኩበት። እርሷ ሳትመጣ የቀረች ጊዜ ግን የጂን እና ብራንዲ ጥሩ ወዳጅ በመሆን ከሆቴሌ ውጪ የትም መሄድ ስለምፈራ፣ በእያንዳንዱ ሌሊት እዚያው ሆቴል ወደሚገኘው አንድ ጥግ እሄዳለሁ። በዚያም ጨርሶ እስከሰክር ድረስ ብራንዲ ከኮካ ጋር እየቀላቀልኩ እጠጣለሁ፤ ስሰክርም ለመተኛት ወደ ክፍሌ እሄዳለሁ።

በላብ አደሮች ቀን ገና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ በሆነ ወጣት ተማሪ ከተመታሁ በኋላ፣ በሕይወቴ ላይ በርከት ያሉ ዛቻዎችን ማስተናገድ ጀመርኩ። ይህ ተማሪ በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ይኖር የነበረውና የምሕንድስና ተማሪ የነበረው የጓደኛዬ የጊብ ታናሽ ወንድም መሆኑ ተደረሰበት። እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከግምት በማስገባት፣ በዴሳን ትቶ ለመሄድ ጊዜው እንደ ሆነልኝ ወሰንኩና በሐረርጌ ውስጥ ወደምትገኝ ሌላ ከተማ እንዲያዘዋውሩኝ ለንዑስ-ወረዳው የትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ጠየቅሁኝ። እርሳቸውም የዝውውር ውሳኔዬን የሚያስረዳ ማመልከቻ እንድጽፍ እና ጉዳዩን የሚያረጋግጥ ደጋፊ ሰነድ እንደ ማስረጃ አብሬ እንዳቀርብ ስለ መከሩኝ፣ ከአካባቢው የፖሊስ ቢሮ ሪፖርት ወሰድኩኝ። በላብ አደሮች ቀን የተፈጸመውን ነገር ፖሊስ መዝግቦ ይዞት ስለ ነበረ፣ ሐተታውን ከቢሯቸው መውሰዱ አስቸጋሪ አልሆነብኝም። ስለዚህም ሠነዱን ከማመልከቻዬ ጋር አያይዤ በትምህርት ሚኒስቴር ላሉት ኃላፊዎች አስገባሁና ዝውውሩ ተፈቅዶልኝ ወደ ጅጅጋ ተመደብኩ።

ወደ ጅጅጋ ከመሄዴ በፊት ከካሱ ጋር ጥቂት ጊዜ ከቆየሁ በኋላ፣ በዴሳ ከተማን በደስታ፣ ነገር ግን ስሜ እንዲጠፋ ምክንያት በሆኑት ሁኔታዎች ደግሞ በእጅጉ በማዘን ለቅቄ ወጣሁ። ካሱ ከጉርሱም የሆነ የእኔ ጥሩ ጓደኛዬ ሲሆን፣ ከመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም (ቲቲአይ) ተመርቆ በሐረር ዙሪያ የተመደበና ለበርካታ ዓመታት ያስተማረ ሰው ነው። ከእርሱ ጋር የነበረኝ ጓደኝነት በ1964 ዓ.ም ከዩኒቨርስቲ አቋርጬ ከወጣሁ እና ደደር ላይ አስተማሪ ከሆንኩበት ጊዜ ጀምሮ እየጠበቀ የመጣ ግንኙነት ነበር። እንደ አባቶቻችን ጥንታዊ ትውፊት መሠረት ጓደኝነታችንን የበለጠ ለማጠንከር የመጀመሪያ ልጁን ሲወልድ የክርስትና አባቱ እንድሆንለት ፈቅዶልኛል። እርሱ ብሩህ አእምሮ የነበረው ንጣሚ በመሆኑ፣ ተሰጥዖውን አስተውዬ ወደ ዩኒቨርስቲ እንዲገባ ሁልጊዜ አበረታታው ነበር። ይህንን ለማድረግ ቢወስን ኖሮ ታዋቂ የሥነ-ጽሑፍ ሰው ይሆን ነበር። ነገር ግን፣ እርሱ ለዚህ ነገር ጥረት ያደረገው በከፊል ልብ ስለ ነበረ ታዋቂ ሰው አልሆነም። ከዚያ ይልቅ፣ የእኔን ተራማጅ አይታዎች በመቀበል ደደር ላይ እንደ ተዋወቅሁት ጓደኛዬ ልክ እንደ ሽሜ የአብዮት ጓደኛዬ ሆነ።

በኢትዮጵያውያን ፖርቲዎች ግራ ክንፍ በኩል የተፈጠረው የፖለቲካ መከፋፈል የተለየ ቅርጽ ይዞ ስለ ነበር ወደ ሐረር በተመለስኩበት ሰዓት የፖለቲካ ድባቡ በከፍተኛ ሁኔታ ተቀይሮ ጠበቀኝ። በጊዜው፣ ኢሕአፓ ሐረር ውስጥ ባሉት ወጣቶች ላይ ግልጽ የሆነ እንቅስቃሴ እንደ ያዘ ምንም አያጠራጥርም ነበር። ዩኒቨርስቲ የነበሩት አብዛኞቹ ጓደኞቼ ጉዳዩን በታማኝነት እያገለገሉለት ከቅን ልቦና በመነጨ ፓርቲውን የሚደግፉ ሲሆኑ፣ ካሱም እንዲሁ በኢሕአፓ የውስጥ ለውስጥ ሥርዓት ተመልምሎ ሲያገለግል ቆይቷል። ሁልጊዜም ቢሆን ራሴን የማየው ሐረር ውስጥ ላለው የፖለቲካ መዳበሮች ተከራካሪ አድርጌ በመሆኑ፣ በከተማዋ ውስጥ እየታየ በነበረው ነገር ላይ አለመገኘቱ በፖለቲካ ሒደቱ ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎን ላጣ እንደ ሆነ ያክል እንዲሰማኝ አደረገ። በበቂ መጠን ያነበብኩ፣ ደግሞም በማርክሲዝም ጉዳይ ላይ ጥሩ መወያየት የምችል፣ ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ለአብዮት እና በኃላፊው ጊዜ ላይ በነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ ጠንከሬ በመቆም ረገድ ጥሩ ዝና ያለኝ ሰው ነኝ ብዬ አስብ ነበር። አሁን ግን፣ የቅርብ ጊዜ የአብዮት ተቀባዮች የሆኑትን ጨምሮ ሁሉም ሰው የዝማሬ ቡድኑን በተቀላቀለበት ሰዓት ላይ አንድ ጥግ ላይ የተጣልኩ እና የተተውኩኝ መስሎ ተሰማኝ። እስከዚህ ደረጃ ድረስ የበርሜ ከባቢዎቼን ይዤ እንደ ቆየሁ ስሆን፣ እንደ ቲቶ፣ ጳግሽ፣ ታሜ እና ሽሜ ያሉ የጥንት ጓደኞቼንም አግቼያቸዋለሁ። ነገር ግን፣ ከኃላፊው ጊዜ በተለየ የተገደበ ተጽዕኖ እንደ ነበረኝ ብዙም ሳይቆይ እየገባኝ መጣ።

ያለመታደል ሆኖ፣ በበዴሳ የተለጠፈብኝ መጥፎ ስም ሐረር ውስጥም ይከተለኝ ጀመር። ሆኖም ግን ሐረር እንደ በዴሳ ሳይሆን፣ ሐቀኝነቴን የሚያውቁና የትኛውንም ማስፈራራት እና ስም ማጥፋት በቀላሉ የማይቀበሉ በርካታ ጓደኞች ያገኘሁባት ከተማ ሆነችልኝ። የትስስር ሥርዓቱ የበለጸገ እና ሰፊ ቢሆንም፣ የምንኖረው ባልተመጣጠነና በተዘበራረቀ ዓለም ላይ ስለ ነበረ፣ ይህ ትክክለኛው ሰዓት አልነበረም። እርሱም ነገሮች ሊተነበዩ በማይችሉበት ሁኔታ በፍጥነት በሚተካኩበት እና ማንም ሰው ሙሉ ለሙሉ ተጠያቂ ሊሆን የማይችልበት በመሆኑ ነበር። አንዳንድ ሰዎች እኔን በቡና ቤቶች እና ደርግ ለቅስቀሳ ብሎ ባመጣቸው ኪነቶች ላይ እያገለሉኝ እንደ ሆነ ማስተዋል

ጀመርኩ።[32] በተፈጥሮዬ በስሜቱ ስስ ሰው በመሆኔ ሰዎች ስለ እኔ ምን እየተሰማቸው እንደ ሆነ በቀላሉ መናገር እችል ነበርና በርቀት አውቃቸው የነበሩ ሰዎች በጥርጣሬ ዓይን ሲመለከቱኝ ማስተዋል ጀመርኩ። ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ በቀላሉ ለለይ እስከማልችል ድረስ ያስቸገረኝ ነገር የተወሳሰበው ሕይወቴ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በእነዚያ ዘመናት ፖለቲካ እየተካሄደ በነበረበት በመላው ሁኔታ መታደኔ ጭምር ነበር። ስለ አመራር ጉዳይ የበለጠ ግልጽ ጥያቄዎችን በማንሣት፣ ስለ አብዮቱ አቅጣጫ የበለጠ መመራመር ጀመርኩ። በነፍሴ የውስጥ ጥልቀት ውስጥ ራሴን እጠይቅ የነበረው በብዙ ገጽታዎች እየተገለጠ የነበረውን አብዮት እየመራ ያለው ማን እንደ ሆነ ነበር? በሐረር ውስጥ የነበረውን የፖለቲካ ምስቅልቅሎሽ በግልጽ ያየሁ ሲሆን፣ ፈጽሞ ልወደው አልቻልኩም። በድጋሚ፣ "ከዚህ ሁሉ ግራ መጋባት በስተጀርባ የሚገኙት ሰዎች እነማን ናቸው?" ብዬ መጠየቅም ነበረብኝ።

በቀደሙት ጊዜያት ውስጥ ፖለቲካ በብዙ ምሥጢራዊነት ስለማይሸፋፈን አብዮተኞች እርስ በርስ እንተዋወቃለን፣ ደግሞም ልዩነቶች ቢኖሩን እንኳን ግልጽ የሆኑ ውይይቶችን እናደርጋለን፣ ከዚያም የተነሣ የፖለቲካ እድገቶችን ለመያዝ ችግር አልነበረብንም። ሐረር ውስጥ ከቆላድ አምባ እስከ ቦቱ፣ በጆጎል አካባቢ ከሸንኮር እስከ ፈሴና ባር ድረስ በእያንዳንዱ የመኖሪያ ክፍል ውስጥ ጓደኛ ነበረኝ። በዚህም ምክንያት ወደ የትኛውም የበርጫ ታዳሚዎች ዘንድ መሄድ እና ከነበራቸው ፍሰት ጋር መቀላቀል እችል ነበር። በተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም የመካድ ሁኔታ ሳይገጥመኝ አብዮታዊ በሚለው መልካም ስሜ ስደሰት ቆይቻለሁ። አዲሶቹ ወጀቦች ቢያንስ ሐረር ላይ እንደ ተገለጡት በቀደሙት ጊዜያት ላይ እመላለስበት እንደ ነበረው ፖለቲካ በልዝብነት ሰስልሰው ስላልሄዱልኝ አንዳች ነገር ተሳልፌ ልሆን እንደምችል አሰብኩ። ወይም ምናልባት በአዲሶቹ ፖለቲከኞች እየተመራ ካለው አዲስ ፖለቲካ ፍሰት ወጥቼያለሁ ማለት ይሆን ስል መጠራጠርም ጀመርኩ።

ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ፣ የድሮ ጓዴ ሽሜ ልክ እንደ እኔ ፊዲስት ወይም ባንዳ ተብሎ በመጥፎ ስም እንደ ተጠቆረ ስሰማ፣ በመላው ሕይወቴ ከማውቃቸው ሰዎች ሁሉ የመጨረሻ የዋህ ሰው ስለ ነበረ፣ ይሄኛው እንከብል እውጠው ዘንድ አስቸጋሪው ሆነብኝ። ሽሜን የማውቀው ደደር ላይ እንዳስተምር ከተመደብኩበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን፣ እርሱ የእውነት ጓደኛዬ፣ የእውነት





ማርክሲስት እና አብላልቶ የሚያስብ ሰው፣ ባጭሩ በርካታ የሚደነቁለት ነገሮች ያሉት ሰው ነበር። የእርሱን ጓደኝነት የምደሰትበት በበርካታ ግንባሮች ላይ እየተገጣጠምን፣ እንደ ጸሐፊ፣ ገጣሚ፣ አርቲስት እና ግሩም ተጫዋች ጭምር ሆኖልኝ ነው። ምንም እንኳን እርሱ በአብላጫው ከተግባራዊ ማንነት ይልቅ ንድፈ-ሐሳባዊ የመሆን አዝማሚያ ይኑረው እንጂ፣ ጥልቅ እውቀት የነበረው የዘመኑ አብዮተኛ ነበር። ከእርሱ ጋር መሆን ያስደስት ስለ ነበር፣ በሁሉም ሰው ዘንድ የሚወደድና ሰው ሁሉ ከእርሱ ጋር በርጫ ማድረግን የሚመኝበት ሰው ነበር። አብዛኞቹን ከሰዓት በኋላዎች ከሽሜ ጋር መጻሕፍትን በማንበብ እና "ዲሞክራሲያ" የተባለውን የኢሕአፓ የምሥጢር ሥነ-ጽሑፍ፣ ደግሞም ሌሎችን ድብቅ ሰነዶች በጋራ እያነበብን እናሳልፋለን። ሽሜ ደደር ላይ በነበረን ትውውቅ ላይ እንደ ነበረው እንደ ዛው እንደ ሆነ ዘልቋል እንጂ፣ ተለውጦብኝ አያውቅም።

የኢሕአፓ መሪ ነን በሚሉት የጊዜው ሰዎች ከሽሜ ጋር የነበረኝ ጓደኝነት እንድተው መመሪያዎች፣ እንዲያውም ማስጠንቀቂያዎች ጭምር ይደርሱኝ ጀመር። እኔ ግን አሳማኝ ሁኔታን መሠረት ባላደረገና በሌሎች ማስረጃዎች ባልተደገፈ መነሻ ውድ ጓደኛዬን መተው አልፈለግሁም ነበርና፣ ያሉትን ለመፈጸም አሻፈረኝ በማለት ከሁሉም በላይ የጓደኝነት ግብረ-ገባዊ ገዢ እውነታዎች ላይ የሙጥኝ አልኩኝ። ሽሜ ለሌላ ለመወገን ፖለቲካዊ ጎራውን ቀይሮ ቢሆን ኖሮ ምሥጢር አድርጎ እንደማይደብቀኝ እርግጠኛ ነበርኩ። ሰፋ ያለ ምርመራን በኢሕአፓ ታሪክ እና ተፈጥሮ ላይ አድርገን ባናውቅም፣ እንዲሁም እውነተኛ የኢሕአፓ አባላት ባንሆንም፣ ፓርቲው ለኢትዮጵያ አብዮት እውነተኛው ተከራካሪ ነው ብለን ሁለታችንም የምራችንን ለማመን በቅተናል። ነገር ግን፣ የኢሕአፓን መርሐ-ግብር አንብበን ነበርና በኢትዮጵያውያን አብዮት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የያዛቸው አቋሞች የሚያሳምኑን ሆነው ስላገኘናቸው፣ የአብዮቱ ፈጠራ ያለው ፓርቲው ነው ብለን ልባችን እና ድጋፋችን ሰጥተነዋል። ስለዚህም ከእንዲህ ዓይነቱ ጓደኛዬ ራሴን ለማራቅ ምንም ሕጋዊ ምክንያት አልነበረኝም። ለጥያቄያቸው የማይሸነፈውን አቋሜን በመረዳት የአካባቢው የፓርቲ መሪዎች ከእነርሱ ጋር ኮስታራ የሆነ ስብሰባ እንዳደርግ ጠየቁኝ። ያን ጊዜ ሉቶሮሬ ተብሎ በሚጠራ የምሽት የበርጫ በዓል ላይ እንደ ቲቶ፣ ጸጋሽ፣ ታሜ፣ እና በፓርቲው የአመራር ቦታ ላይ ያሉ

በሚመስሉት ሌሎች አደሬ ጓደኞቼ ጋር የሦስት ሌሊት ተከታታይ ስብሰባዎችን አደረግን። በአጀንዳው ላይ ዋናው ርእስ ከሽሜ ጋር የነበረኝን ግንኙነት የተመለከተ ነበር።

በስብሰባዎቹ ላይ የሽሜን የፖለቲካ አቋም እና እኔም ከዚያ አቋም ጋር እንዴት የተያያዝኩ እንደ ሆንኩ ያለውን ሁኔታ በሰፊው ተወያየን። በዚህ ውይይት ውስጥ መረጃን መሠረት ያደረጉ አሉባልታዎች ሳይሆን ተጨባጭ የሆኑ ማረጋገጫዎችን እፈልግ ስለ ነበር፣ ሽሜ ወደ ሌላኛው ሰፈር ለመሄዱ እኔን የሚያሳምኑበት ምን ማስረጃ እንዳላቸው በመጠየቅ መሪዎቹን አፋጠጥኳቸው። በእነርሱ በኩል ግን፣ ሁሉም ክሶች መሬት ባልረገጡ መሠረቶች ላይ የተመሠረቱ ስለ ነበሩ ውንጀላቸውን እውነተኛ ለማድረግ አንዴም እንኳን የሚጠቅሱት ነገር በማጣታቸው፣ ይህ ስም ማጥፋት ብቻ ነው ብዬ ክሳቸውን ውድቅ አደረግሁት። ማስረጃ ተብለው በእርሱ ላይ መሪዎቹ የጠቆሙት ነገር ሽሜ በየዕለቱ ይጠጣል፣ ደግሞም ወደ ምሽት ጭፈራ ቤቶች ይሄዳል፣ ስለዚህ ተጨማሪ የገንዘብ ምንጭ አለው ማለት ነው የሚል በመደበኛ ሁኔታ አልኮል ከመጠጣቱ ጋር የተያያዙ ክሶች ነበሩ። ለዚህም ቢሆን፣ የአለማያ ከተማ ከንቲባ የሆነ የአጎት ልጅ እንዳለውና በቸርነት ገንዘብ እንደሚሰጠው ነግሬ ዝም ባሰኘቸው፣ ከአንዳንድ የመንግሥት ሹማምንት እና የግብርና ሚኒስቴር ውስጥ መምሪያ የሆነው የኢፒኢዲ ሠራተኞች ጋር ግንኙነት አለው የሚል ሌላ ክስ ቀረበበት።[33] ለዚህኛውም ክሳቸው ያቀረብኩላቸው ማፋጠጫ ከመንግሥት ሹማምንት ወይም የኢፒኢዲ ሠራተኞች ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑ ችግሩ ምኑ ላይ ነው? የሚል ነበር። ስለዚህ በዚህ ዓይነት የምልልስ ሁኔታ ልንተማመን ባለመቻላችን፣ ከሦስት አድካሚ የሌሊት ስብሰባዎች በኋላ ስብሰባው እርባና-ቢስ ብቻ መሆኑ ተረጋግጦ ያለ ምንም መቋጫ ተጠናቀቀ። ከሽሜ ጋር ያለኝን ግንኙነት ካላቆምኩ የፖለቲካ ዝናዬ ላይ ሊደርስብኝ ለሚችል ለየትኛውም ነገር ተጠያቂዎች እንደማይሆኑ የሚገልጽ አንዳች ዓይነት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሲሰጡኝ፣ እኔም በበኩሌ፣ አሉባልታን መሠረት አድርጌ ጓደኛዬን ከምተው ይልቅ የሚመጣውን አደጋ ሁሉ ለመቀበል እንደምመርጥ ነግርኳቸውና ተለያየን።

ምንም እንኳን የራሱ የሆነ የባሕርይ ደካማ ጎን እና እንደ ሥርዓት አልበኝነት፣ እልከኝነት፣ እና በመጠጥ ተጽዕኖ ሥር በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ





የችግር ፈጣሪነት ዓይነት የግል ችግሮች የነበሩበት ቢሆንም፣ በእጅጉ እምነት ሊጥሉበት የሚችሉት ሰው በመሆኑ ሽሜን አምነው ነበር። በትንሹ ለሚያከብራቸው ሰዎችም ትሕትና የጎደለው ሰው ሲሆን፣ እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ምንም ሳያፍር በአሽሙር ሊወጋቸው ሁሉ ይችላል።

ብዙም ሳይቆይ እንደ ባንዳዎች ተፈረጅንና የእኔ ስም ከሽሜ ጋር በተያያዘ መጥፋት ጀመረ። ይህ ሲሆን አስጨናቂ ሆኖ የመጣው ሌላው ነገር መጥፎ ስም የመሰጠቱ ሁኔታ በገዛ ቤተሰቦቼ አባላት ላይ እንኳን ሊፈጸም መቻሉ ነበር። “ሙሉ ቂሎ” በመባል በቅጽል ስሟ እንጠራት የነበረችው የአክስቴ ልጅ ሙሉ እና ታናሽ ወንድሟ ጌትም ጭምር ባንዳ ተብለው በመጠራታቸው ጉዳዩ ወደ ቤት እየመጣ ነበርና ብዙ ጎዳን። ሙሉ እና ጌት የቤተሰባችን አባላት እንደ መሆናቸው አብረን ስላደግን ሁለቱንም አውቃቸዋለሁ። ሙሉ ዘናጭ ሴት ነበረች እንጂ፣ ለፖለቲካ ጨርሶ ዝንባሌውም አልነበራት፤ ጌት ደግሞ ሽቅርቅር የሆነ የ11ኛ ክፍል ተማሪና ለፖለቲካ ጥቂት ፍላጎት የነበረው ልጅ እንደ ሆነ ይታወቃል። ታዲያ ለክሱ ምክንያት የነበረው ምንድን ነው? ቢባል ውድ የነበሩ ልብሶችን ይለብሱ ስለ ነበረና ከመካከለኛ ገቢ ያለው ቤተሰብ የመጡ ስለ ሆኑ ገንዘባቸውን አባካኝ ለሆነ የሕይወት ዘይቤ በማዋላቸው ነበር። የገቢ ምንጫቸው ለአካባቢው ጠጅ ቤት ጌሾን የሚያቀርበው አነስተኛ ንግድ ሥራን ከሞተችው እናታቸው መውረሳቸው ለሕዝቡ ግልጽ ያልነበረ ምሥጢር ነበር። ባለኝ ተጽዕኖ ሁሉ ለአጎቴ እና አክስቴ ልጆች ልከላከልላቸው ሞክሬ ስላልተሳካልኝ በከንቱ ደከምሁ። በእነዚያ ዘመናት፣ የተሰጠውን ስም እውነተኝነት ለማጣራት የሚሞከርበት ምንም ዘዴ እስከማይኖር ድረስ አንድ ጊዜ ባንዳ ተብላችሁ ከተጠራችሁ፣ ያንን ስም ያገኘው ማንም ይሁን ማን፣ ያንን ቅጽል ማስወገዱ ከባድ ይሆናል። ስሙ ለተሰጣቸው ሰዎች ነገሩ ሊያመጣ የሚችለውን የግል ጉዳት በተመለከተ ግድ የሚለው ማንም ሰው አልነበረም። እንደ ሐረር ባሉ ከተሞች የሚሰጠው ስም በተለያዩ የበርሜል ሞገዶች አማካኝነት መላውን ከተማ ሊደርስ ይችላል፤ ከዚያም የምታስተውሉት ብቸኛ ነገር ስለ እናንተ ምንም ባያውቁም እንኳን፣ ሁሉም ሰው ስለ እናንተ የሚያወራ መሆኑን ብቻ ነው። በጣም ተስፋ የሚያስቆርጠው እና የሚያሳምመው ነገር ሰዎች የአብዮቱ ጠላት አድርገው ሲገምቷችሁ ወዲያውኑ የምታጡት የከበሩ ጓደኝነቶቻችሁን መሆኑ ነው። ማረጋገጫ የማምጣቱ ሸክም በእናንተ ላይ

የተጣለ ቢሆንም፣ ደግሞም ራሳችሁን እውነተኛ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ብታደርጉም፣ የሚያሳዝነው ነገር ማንም የማይሰማችሁ መሆኑ ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ በአንዳንዶቹ የቀድሞ አብዮተኛ ከባቢዎቼ ዘንድ ጠንካራ የሆነ ጓደኝነት እስከዚያ ጊዜ ድረስ የያዝኩ ሰው ስለ ነበርኩኝ ነገሩ አስጨነቀኝ። ነገሩ የሚያስጨንቀው ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ ለዘመዶቼ ለሙሉ እና ለጌት ጭምር ሆነ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ 1968 ዓ.ም ላይ ሙሉ ስታገባ የተከሰተውን ነገር አስታውሳለሁ። ኢሕአፓ የጠነሰሰውና የበላይነቱን የተቀዳጀበት የላባደሮች ቀን እና የሠርጉ ዕለት አንድ ቀን ላይ ዋለ። የአክስቴን ልጅ ሠርግ በዓል ትቼ የሕዝብ ሰልፍ ለማየት ወደ ስታዲየም ከሄድኩ በኋላ የቀረው የሠርጉ ክብረ-በዓል ላይ ለመገኘት ወደ ሠርጉ ሄድኩ። እዚያ ስደርስ፣ ትኖርበት ከነበረበት ከሸንኮር አካባቢ ያሉ አንድም ወጣት በባህላችን የተለመደ በሆነው መሠረት የሠርጉን ዝግጅት ለመርዳት አለመምጣታቸውን ለመታዘብ ቻልኩ። በጣም በሚያስጨንቅ መልኩ የትኛቸውም የጎረቤት የልጅነት ጓደኞቿ ከሠርጓ ጋር በተያያዘ ላለው ክብረ-በዓል እንዲሁም በዋዜማውና በማግስቱ ላለው ባህላዊ የሌሊት ክብረ-በዓል ሳይገኙ ቀሩ።

በዘመኑ ከመጣ የፖለቲካ እብደት ይልቅ የቆየ ወዳጃዊ ትስስር የበለጠ ጠቃሚ ለሆነላቸው በማኅበረሰቡ ለነበሩት በእድሜ የገፉ አባላት ይህ ተግባር የሚጻረር መሆኑ አያጠያይቅም። ስለዚህም፣ እነርሱ ሙሉ ለሙሉ በዝግጅቱም ሆነ በዋናው የሠርግ ክብረ-በዓል ላይ ተሳተፉ። በነገራችን ላይ፣ የአክስቴ ልጅ ለማግባት የወሰነችው ሐረርን ለመልቀቅና በለጋ እድሜዋ የምትጋፈጠውን ጫና ለመሸሽ ነጻ ወደ ሆነ አካባቢ እንደ መሄጃ ዘዴ አድርጋ ለመጠቀም እንደ ሆነ ጠቀስ አድርጌ ለማለፍ እፈልጋለሁ።

አብዛኛውን ጊዜ ጥበብ እና ዘዴ የጎደለው የሚመስለው ደግሞም በእነዚያ ዘመናት ያስፈልግ የነበረውን ነገሮችን የመመርመርን ነገር እና በሕይወቱ የገጠመውን ችግሮች የሚወጣበትን ሥነ-ሥርዓት ያላዳበረው ሌላኛው ጓደኛዬ፣ ጌት፣ ችግር ውስጥ ገባ። በርከት ያሉ ጓደኞቹ ከእርሱ ጋር ያላቸውን ጓደኝነት ማቋረጥ ሲጀምሩ፣ ከመንግሥት ዘንድ ጥበቃ ማግኘት እንደሚያስፈልገውና ከማኅበረሰቡ እንዲገለል ምክንያት የሆኑትን ሰዎች ስለ መበቀልም ጭምር ማሰብ ጀመረ። ይህንንም ያሰበው የመገለሉን ሁኔታ፣ በዋናነትም በክፍል ውስጥ





ይደርስበት የነበረውን ጫና መቋቋም ስላልቻለ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ የምኖርበት ድረስ እያለቀሰ መጥቶ የእርሱ የክፍል ጓደኞች እንዴት እንዳገለሉት እና እንዳዋረዱት ይነግረኝ ነበር። ሁሉም ተማሪዎች ከእርሱ ርቀው ስለሚቀመጡና እንዲናገርም ስለማይፈቅዱለት፣ የእርሱ ተስፋ መቁረጥ ከሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እያለፉ ካሉ ተማሪዎች ጋር እንዲሆን አደረገው። ከእነዚህም አንደኛው ገና ልጅ የነበረ ኋላ ላይ ለኢሕአፓ እንደሚሠራ ተጋልጦ መንግሥት በዚያው ምክንያት የገደለው ብሩህ ጭንቅላት ያለው ተማሪ፣ ዳዊት ነበር።

አንድ ቀን ከአንዳንድ በኢሕአፓ ውስጥ ቁልፍ ቦታ ከነበራቸው ጓደኞቼ ጋር በነበረኝ ግንኙነት ጌት እና በከሳቴ ብርሃን ይኖር የነበረው የጎረቤታችን ታዋቂው የሕግ ሰው ልጅ ሽቤ ሊገደሉ እንደ ሆነ ምሥጢር ተነገረኝ። ጊዜ ሳልወስድ መረጃውን ለጌት አስተላልፌ ጩርቁን ማቁን ሳይል ከተማይቱን ወዲያውኑ ጥሎ እንዲወጣ መከርኩት። ሊያምነኝ ሲያቅማማ በፍጥነት እርምጃ ወስዶ ከተማይቱን በመልቀቅ ካልወጣ ሕይወቱን እንደሚያጣ አበክሬ ስላስጠነቀቅሁት መጨረሻ ላይ መረጃውን አምኖ በመውሰድ በምሥጢር ከሐረር ወደ ድሬዳዋ ታክሲ ያዘና ወጣ። ከድሬዳዋም በባቡር አድርጎ ከሙሉ ጋር ለመኖር ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። ሙሉ ያገባችው የአየር ኃይል ፓይለት በመሆኑ ዩኒቨርስቲ እስኪገባ ድረስ መጠለያና ምግብ ሰጥተውት በዚያ ቆየ።

የጌትን ሕይወት እንዳተረፍ ምክንያት የሆነውን ያንን ጓደኛዬን ከልቤ እንዳመሰግነው ያደረገኝ ነገር የጌት ጓደኛ ሽቤ በዛው ቀን መገደሉ ነበር። ከግብረ ገባዊ እሴቶቻችን እና የፍልስፍናዊ አተያየቶቻችን በሚመነጩ የሕይወት ጉዳዮች ላይ አንዳንድ ጊዜ መራራ አለመግባባቶች ስላሉን፣ በጌት አንዳንድ ባሕርያት በአብዛኛው ደስተኛ ሆኜ አላውቅም። ለምሳሌ፣ በጥቅሉ ከሴቶች ጋር ስላለው ግንኙነት እና በግብረ-ገባዊ ልልነቱ ላይ ችግር አለብኝ። ይሁን እንጂ፣ እንዲሁ ከመጣ የሐሰት ክሶች የተነሣ በዚህ ወጣትነት እድሜው በከንቱ እንዲሞት አልፈለግሁም ነበር።

ሐረር ውስጥ ወደ ነበረኝ የእኔ ሁኔታ ስመጣ፣ ጓደኛዬ የሆነውን የሽሜን ሐቀኝነት የምሟገትለት ነጥብ አንድ ጫፍ ላይ ደረሰ። ከእርሱ ጋር ያለኝን ግንኙነት እንዳቆም ብዙ ጊዜ ማስጠንቀቂያ የደረሰኝ ብሆንም፣ በሕሊናዬ ላይ ምንም ማድረግ ስላልፈለግሁ የትኛውም መጠን ያለው ማሳመኛ አቋሜን

ሳያስለውጠኝ ቀረ። ከእርሱ ጋር የገፋሁበት የጓደኝነት ትስስር ስሜ እየጠፋ መሄዱ ቀጥሎ *ፊዲስት* እንደ ሆንኩ አድርገው የሰጡኝ ስም ላይ የሚጨመር የበለጠ የፈጠራ ወሬዎች ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንዲጨመሩ አደረገ። በዚያን ጊዜ ራሱን በግልጽ ከመኢሶን ጋር አድርጎ የነበረው የቅርብ ጓደኛዬ ሮብ ጋር አንድ ላይ እንደ ሆንኩ ተደርጎ አዳዲስ አሉባልታዎች መወራት ጀመሩ። ሮብ በመኢሶን *ሠፈራ* ውስጥ የቤት ስም ሆኖ የሚጠራበት ስሙ ሲሆን፣ ምናልባት የእርሱ በከፊል ጣልያናዊ መሆን የተጋነነ ውጤት ሳያመጣ አልቀረም። ስለዚህ፣ ስሜን ማጽዳት ከነበረብኝ ማረጋገጫ የማቅረቡ ሸክም በእኔ ላይ የጸና ይሆናል ማለት ነው። ምንም እንኳን እንደ ተካ እና ጸግሽ እንዲሁም ሌሎች የዩኒቨርስቲ የቀድሞ ጓደኞቼ ጋር ሞቅ ያለ፣ ሆኖም ውስብስብ ግንኙነት የነበረኝ ብሆንም፣ የማያውቀኝ የሐረሪ ወጣት ጭምር *ፊዲስት* እንደ ሆንኩ በአመዛኙ የሚያውቅ መሰለ። በተቻለኝ መጠን ከአንደኛው *በርጫ* ወደ ሌላኛው *በርጫ* በመሄድ ስሜን እና ሐቀኝነቴን ለሚያደምጡኝ ሁሉና እነርሱ ለታመኑለት ፓርቲ የምወግን መሆኔን ለማሳመን፣ አንዳንዴም በእውርነት ሌላም እየጨመርኩ የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ሞከርኩ። አሉባልታዎች ከእውነታው በላይ ብርቱ ስለ ነበሩ እና በዙሪያዬ ያሉት አብዛኞቹ ጓደኞቼ እኔ በጣም እፈልገው የነበረውን አጸፋዊ ዘመቻ ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት በጥቂቱ ብቻ ስለ ነበር፣ ጥረቴ ምንም ጥሩ ውጤት ሳያመጣ ቀርቶ በከንቱ ደከምሁ። እነዚህ ጓደኞቼ ምናልባት ለገዛ ራሳቸው ስም ፈርተው፣ ወይም ከሸሜ ጋር ያለኝን ግንኙነት ላለማቋረጥ በያዝኩት ግትር ቁርጠኝነት ተበሳጭተውም ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ሳስበው፣ ምናልባት ምክራቸውን ልሰማ እና ራስን እንደ ማስተረፊያ ጊዜያዊ ውሳኔ ከሸሜ ጓደኝነት በዘዴ መተው ነበረብኝ፤ ወይም በሕይወቴ ጉዞ በዚያኛው ደረጃ ላይ አንዳች ዓይነት ጠቃሚ የሕይወት ትምህርቶችን በመማር ላልፍ ይገባኝ ነበር። ከዚህ የተነሣ ተስፋ መቁረጡ ራሴን በማጠፋበት ዓይነት መልኩ የበለጠ ብዙ እንድጠጣ አደረገኝ።





## የጅጅጋው ውስብስብ ሕይወትና ቀጣዩ ሁኔታ

ማስተማር ለመጀመር ወደ ጅጅጋ የተዛወርኩት በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ሲሆን፣ በቶጋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳይንስ እንዳስተምር ተመደብኩ። እኔ የታሪክ ተማሪ የነበርኩ ብሆንም፣ መስኬ ያልሆነውን የትምህርት ዓይነት የማስተማሩን ተግዳሮቱን ተቀብዬ፣ በዚህም ይሁን በዚያ፣ ሥራውን ተወጣሁት። በጅጅጋ ያሉት ወጣቶች በበዴሳ ሳለሁ ወደ ጅጅጋ እንደ ተዛወርኩ ሰምተው ነበርና በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ያንን የጠላሁትን '*ፊዲስት*' የሚለውን ስም በድጋሚ መስማት ጀመርኩ። በመጀመሪያ ደረጃ፣ ትምህርት ቤት የነበሩት ተማሪዎች በመተላለፊያዎች እና ጎዳናዎች ሳልፍ '*ፊዲስት*' እያሉ ይጮኹ ስለ ነበረ፣ ወጣት ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይመጡና አቋሜን ለማጣራት ሲሉ ከእኔ ጋር ውይይት ይከፍታሉ። አብዛኞቹ የሚያነሡዋቸው ጥያቄዎች ተጨባጭ ወይም እውነተኛ ስላልነበሩ እነዚያን አጋጣሚዎች እየጠላኋቸው፣ ነገር ግን ያልተፈለገ መጋፈጥን ለማስወገድ ስል ብቻ ስሜቶቼን አረጋጋሁ። በጣም ያበሳጨኝ ጉዳይ እንዲህ የሚያደርጉት ወጣት ታዳጊዎች ስለ ማርክሲዝም የሚያውቁት በጣም ጥቂት ሆኖ ሳለ፣ 'ልክ እንደ ሶቭየት ተሞክሮ 'ከአብዮት መለየት'፣ እና 'የተራው ሰው አብዮት' የሚሉ የማኦ ዓይነት ሐሳቦችን ሲያወሩ ተደማጭነት ማግኘታቸው ነበር። በባህላችን ውስጥ እንዲህ ያለ መጥፎ አጋጣሚዎች በተማሪዎች እና በአስተማሪዎች መካከል ይሆናል ተብሎ በጭራሽ ስለማይገመት፣ ብስለት በጎደለው የልጅነት እብሪተኝነታቸው ብቻ ሳይሆን፣ የትምህርት ቤት አስተማሪ ለሆነ ሰው አክብሮት መስጠት ባለመቻላቸው ጭምር በእጅጉ አዘንኩ። አንዳንድ ጊዜ በትሕትና እመልስላቸዋለሁ፣ ነገር ግን በፖለቲካ ውይይት ውስጥ ስላሉት ደንቦች በጣም ጥቂት ነገር በሚያውቁ ሕጻናት ስለምጠየቅ ንዴት ተሰምቶኝ ተገቢ ባልሆነ መልኩ እመልስላቸው ነበር።

አዳዲሶቹ የሥራ ባልደረቦቼ ጉራማይሌ ስሜቶችን የሚያንጸባርቁ መስለው ይታያሉ። ይህም የሆነው በማርክሲዝም ላይ በጥሩ ሁኔታ እውቀት ያለው እና ኢሕአፓን ሙሉ ለሙሉ የሚደግፍ ተራማጅ ፖለቲከኛ፣ ነገር ግን '*ፊዲስት*' ተብሎ የተጠራን አዲስ ሰውን አይተዋልና ነው። በዩኒቨርስቲ ግቢዎች ውስጥ እየተካሄዱ ከነበሩት አደገኛ የፖለቲካ መዳበሮች የተነሣ፣ በዋናነት ትምህርታቸውን ከዩኒቨርስቲ በማቋረጥ የማስተማር ሥራን ከያዙት

ሰዎች መካከል ጥቂት ጥሩ ጓደኞች ነበሩኝ። የትምህርት ሚኒስቴር ከፈጠረው የሥራ ዕድሎች የተነሣ አያሌ ተራማጆች ሊሠራጩና በቀላሉ በማይታወቁባቸው አካባቢዎች መጠለያ ስለሚያገኙ፣ ያ ሁኔታ 'የኖኅ መርከብ' ተብሎ የተጠራበት ጊዜ ነበር። እንደ ደሜ፣ ባሕሩ፣ ጌቾ እና ብርሽ የተሰኙ አዳዲስ ጓደኞቼ ጋር ታዋቂ በነበረው ገነት ሆቴል አብረን ስንሆን *ለበርጫ* በአንድነት ተቀምጠን ተመሳሳይና የተከለከሉ የምሥጢር ሥነ-ጽሑፎችን ካነበብን በኋላ፣ ምሽቶች ላይ ቢራ እንጠጣለን። ቡና ቤቶቹ ድብቅ ቀጣችንን ለማስተንፈስ የቻልንባቸው ቦታዎች ሆነውልን ስለ ነበር፣ ከማይመቸው ዓለም ማምለጫ የተደላደሉ ቦታዎች ሆነው አገለገሉን። ነገር ግን ያኔም ቢሆን፣ ከእነዚህ ጓደኞቼ ጋር አሳልፍ የነበረው ሌሎች *'ፊዲስት'* ብለው የሰጡኝን ስም እውነት እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ከባድ የሆነ ሸክም በትከሻዬ ላይ በመጫኔ ነበር። ቋሚ በሆነ መልኩ ያንን ማድረጉ ለእኔ ከባድ ሲሆን፣ ከዚያም በላይ በአእምሮዬ ያለውን በሐቀኝነት እና በእውነት ዘና ብዬ የምናገርበትን ነጻነቴን ሰረቀኝ።

በእድሜዬ 20ዎቹ መጀመሪያ ላይ ስለ ነበርኩ፣ በስሜ ላይ የተለጠፈው መጥፎ መግለጫ እንደ ወጣት ልደሰትበት የተገባኝ ሕይወቴ ላይ አንዳንድ ገደቦችን አኖረብኝ። በዚህ ረገድ ከልጃገረዶች ጋር በሚኖረው የፍቅር ግንኙነቶች መደሰትን ጨምሮ፣ በዚያ እድሜ ላይ ያሉ ብዙዎቹ ሰዎች የሚኖራቸውን ዓይነት ፍላጎት ሳላገኝ ቀረሁ። ማስፈራሪያ ውስጥ ስትገቡ ምንም እንኳን፣ እንደ ጥሩ እና አሳማኝ ሰው፣ ደግሞም የሚስብ ነገር ያለው ሰው ሆናችሁ ብትታወቁም እንኳን፣ የሴት ጓደኞችን ማግኘት ግን አብዛኛውን ጊዜ ከባድ ይሆናል። እዚህ ጋ ልክ እንደ ትረካ መረጃ በማድረግ ላካፍለው የምሻው አንድ አጋጣሚ አለኝ። በእነዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች መካከል አንዲት የሴት ጓደኛ ለመያዝ ተሳክቶልኝ በጋራ *በርጫ* ለማድረግ እና ለመደሰት አንድ ወቅት ላይ ለመምጣት ደፈረች። የመጣችው ከኢሕአፓ የሚሰራጨውን የተከለከለ የምሥጢር ሥነ-ጽሑፍ ይዛ ስለ ነበር፣ እኛ ደግሞ አንድ ላይ የሆንነው የፖለቲካ ግንኙነት ለመመሥረት ስላልነበረ "ይህ የፖለቲካ ጥናት ክበብ አይደለም፤ ከእኔ ጋር ሳይሆን፣ ከፈለግሽ ከገዛ ራስሽ እኩዮች ጋር ይህንን ልታደርጊ ትችያለሽ" በማለት በግልጽ ነገርኳትና ተስፋ አስቆረጥኳት። በንግግሬ ብትቀየመኝም፣ አቋሜን ተቀበለችና ለዕለቱ እንዲሁም ጅጅጋ ለቆየሁባቸው አብዛኞቹ ጊዜያት ጥሩ የሚባል የደስታ ጊዜን በጋራ አሳለፍን።

ጅጅጋ በነበርኩበት በዚያን ጊዜ አንዳች የሚያስጨንቅ ነገር ተከሰተ። እናቴ





ከሐረር ልትጎበኘኝ መጣችና ሕይወቴን የከበበ አንዳች ዓይነት አደጋ እየመጣ እንደ ሆነ እንደ ተሰማት ገልጻ፣ "ምቀኛ ሊያጠፋህ ተነሥቶብሃል" ብላ ነገረችኝ። ተልዕኮዋ እኔን ማዳን ነበረና ስሜቷ ስላስፈራት በአካባቢዋ የነበረውን ጠንቋይ ምክር ልትጠይቅ ከሄደች በኋላ፣ ጠንቋዩ ፍርሃቷን አረጋግጦላት 'ክታብ' ተብሎ የሚታወቀውን የክላላ መድኃኒት እንዳደርገው የሰጣት መሆኑን አስታውቃኝ፣ በክንዴ ዙሪያ እንዳደርገው መከረችኝ። መጀመሪያ ላይ ክታቡን ለመቀበል አሻፈረኝ ብልም የማትርነት ተፈጥሮዬን የምታውቀው እናቴ እያለቀሰች እና ቅርብ በሆነ እና በማላመልጠው አደጋ ውስጥ እንደ ሆንኩ በመንገር እንድወስደው ስለ ጎተጎተችኝ፣ እርሷን ደስ ለማሰኘት ስል ልወስደው እና ኋላ ላይም በሆቴሌ ሽንት ቤት ውስጥ ልጥለው ወሰንኩኝ። በሚቀጥለው ቀን እናቴ ተሰናብታኝ ስትሄድ፣ ከሳምንት በኋላ ግን አንዳች አስቸጋሪ ነገር በእኔ ላይ ደረሰብኝ። ሐረር ውስጥ ካለው የፖሊስ ዋና መሥሪያ ቤት የመጡ የደህንነት መኮንኖች ቡድን በማስተምርበት ትምህርት ቤት ያስሩኝ ጀመር። በዚያ ቀን ታምሜ ስለ ነበር በሆቴሉ ክፍሌ ውስጥ ተኝቼ ከቆየሁ በኋላ ቀኑ የክፍያ ቀን ስለ ነበር፣ ከሰዓት በኋላ ላይ ከአልጋዬ ተነሥቼ ደመወዜን ለመውሰድ ወደ አውራጃው ጽሕፈት ቤት አመራሁ። በቦታው ስደርስ፣ ተራቸውን የሚጠብቁ ረጅም የአስተማሪዎች ሰልፍ ነበረና ተራዬን እየጠበቅሁ ሰልፌ ላይ ቆሜ ሳለሁ፣ በአካባቢው በጥሩ ሁኔታ ከማውቃቸው የደህንነት መኮንኖች አንደኛው ምልክት ሰጥቶ ከሰልፉ ካወጣኝ በኋላ ይጠብቅ ወደ ነበረው ላንድሮቨር መኪና እንድገባ ገፋኝ። ሁኔታው በጭራሽ ይሆናል ብዬ ያልጠበቅሁት ስለ ነበረ፣ ፈጽሞ ያስደነገጠኝ እና ያስደነቀኝ ነገር ነበር። እኔን መርገም እና ያለማቋረጥ መምታት የጀመሩት የደህንነት መኮንኖቹ ወደ መኖሪያዬ እንድወስዳቸው ጠየቁኝ። ወደ ገነት ሆቴል አስቀድሜ ከመውሰዴ በፊት ቀድሞ እኖርበት ወደ ነበረው ወንዴ ብዬ ወደምጠራው ጓደኛዬ ቤት ወሰድኳቸው። ክፍሉን በጥልቀት መርምረው ምንም ሊያገኙ ባልቻሉ ጊዜ፣ ቀጥሎ ወደ ሆቴሌ ክፍል ወሰድኳቸው። ከተፈጠረው ነገር የተነሣ በትክክል እያሰብኩ እንደ ነበረ ወይም እንዳልነበረ በእውነት አላስታውስም። ያልተጠበቀው ነገር በእናንተ ላይ በሚደርስባችሁ እንዲህ ባለው ጊዜ ላይ፣ ራስን ተቆጣጥሮ ለማሰብ ጊዜ ስለማይኖር፣ ማድረግ ያለባችሁን ነገር ነው የምታደርጉት። በደረስን ጊዜ በር ሲከፈት የደህንነት ሠራተኞች እና ጓደኞቼ መካከል የተፈጠረውን እሰጥ-አገባ አሁን ድረስ በግልጽ አስታውሳለሁ። ታዲያ፣

የደህንነት ቡድኑ ወደ ክፍሉ ሲገባ ሦስት ጸጉራቸውን በአፍሮ ያበጠሩ ሰዎችን በማየታቸው ማንም ሰው በዚያ ይኖራል ብለው አልጠበቁም ነበርና ቀልባቸው በመጠኑ ተሰበ ወዲያውኑ "እጅ ወደ ላይ!" ሲሉ ጮኹ። ጓደኞቼም ወዲያውኑ እንደተባለው ሲያደርጉ፣ ደህንነቶቹ በጣም አብጠርጥረው ክፍሉን መረመሩ፤ ነገር ግን በዘመኑ በኢሕአፓ ተራማጅ ምሁራን ዘንድ ታዋቂ የነበረው "ጎሕ" የተሰኘው መጽሔት በቀር ጥርጣሬያቸውን የሚያረጋግጥላቸው አንድም ነገር ሳያገኙ ቀሩ። ይህ ሊሆን የቻለው ባሕሩ፣ ጌቾ እና ዘርዬ ለደህንነት ቡድኑ የተሳሳተ ምልክት ሊሰጡ የሚችሉ ሁሉንም ዓይነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ጽሑፎች ስላስወገዱ ነበር። ስለዚህ ደህንነቶቹ አራታችንን (ጌቾ፣ ባሕሩ፣ ዘሩ፣ እና እኔን) ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወስደው እኔን የተነጠለ ክፍል ውስጥ በማድረግ እስር ቤት ጣሉን። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ጓደኞቼ ሲፈቱ፣ እኔ ግን ለቀናት ያክል እንደ ታሰርኩ ቆየሁ።

በተጣልኩበት የእስር ቤት ክፍል ውስጥ በርካታ ተማሪዎች የኢሕአፓ አባላት እንደ ሆኑ ስለ ተጠረጠሩ ብቻ እየማቀቁ አገኘኋቸው። 'ፊዲስት' በሚለው ስሜ የሚያውቁኝ አንዳንዶቹ በእነርሱ ሁኔታ እስር ቤት ውስጥ ተቀላቅያቸው ስላዩኝ የተደነቁ ሲሆን፣ ኀዘኔን ተጋርተው ያዘኑልኝም ነበሩ። በእስር ቤት ከተዋወቅኋቸው ውስጥ የማስታውሰው ብቸኛ ስም የምርጥ ጓደኛዬ የአሌክስ የአጎት ልጅ የሆነው ሰሎሞን ብቻ ነው። ያሰረኝ ያው የደህንነት መኮንን ምሽት ላይ ከታሰርኩበት ክፍል አውጥቶ ወደ ሌላ ክፍል ሊወስደኝ ሲመጣ፣ ከእኔ ቀደም ብለው ተመሳሳይ ሁኔታ ያጋጠማቸው ተማሪዎች ወደ ቶርቸ ግርፋት ክፍል እየወሰዱኝ እንደ ሆነ አወቁ። በሕይወቴ አይቼው ከማውቀው ሁሉ የከፋ ቅዠት በዚያች ጨለማ ክፍል ውስጥ እያየሁ እንዳለሁ እስኪሰማኝ ድረስ መጀመሪያ ላይ በጭካኔ ገረፉኝና ምንም ፍንጭ እንኳን የሌለኝን የምሥጢር መረጃ እንድነግራቸው ጠየቁኝ። እንደ ኢሕአፓ አባል የእኔ ሚና ምን እንደ ሆነ መረጃ እንድሰጣቸው ሲጠይቁኝ፣ የውስጥ ለውስጥ መጠሪያ ስሜን እና የመሳሰሉትንም ጨምሮ እንድነግራቸው ጠብቀው ነበር። እየጠየቁ ያሉት የተሳሳተ ሰውን እንደ ሆነና የትኛውንም መልስ ልነግራቸው እንደማልችል በመቀባጠር ስነግራቸው፣ ከፉኛ መምታቸውን ቀጠሉበትና አፌን ለጉመው በከንዴ ዙሪያ ገመድ በማድረግ ገመዱን ኮርኒሱ ላይ በተያያዘ ነገር ላይ ሲያስሩት ሰውነቴ ተንጠለጠለ። በዚህን ጊዜ ጫማዬ ወልቆ የውስጥ እግሬን በተደጋጋሚ ይመቱ ጀመር። የትኛውንም መረጃ ለእነርሱ ልነግራቸው ከፈለግሁ





ማድረግ ያለብኝ ነገር ከጣቶቼ አንደኛውን ማውጣት እንደ ሆነ ተነገረኝ። ምቱ ልሸከመው የማልችለው ሲሆንብኝ፣ ጣቴን አወጣና ዝቅ አድርገውኝ ጠረጴዛ ላይ እንድቀመጥ፣ ከዚያም የሚፈልጉትን የምሥጢር መረጃ እንዳወጣ ይጠይቁኛል። ይህን ዕድል ሳገኝ አሁንም፣ የተሳሳተ ሰው እንደ ያዙ እውነቱን እነግራቸውና ልክ እንደ ልጅ በፊታቸው ሳለቅስ ስለማያምኑኝ እንደ ገና ወደ ነበርኩበት ሁኔታ ይመልሱኛል። በጅጅጋ የነበረው አበሳ ለተወሰኑ ቀናት ቀጠለና በላንድሮቨር መኪና ዋናው የፖሊስ መሥሪያ ቤት ወደሚገኝበት ሐረር ለተጨማሪ ምርመራ ተወሰድኩ።

ወደ ሐረር ከመወሰዴ በፊት፣ የእኔ ጉዳይ በጅጅጋ ፖሊስ እንደ ሪፖርት መቅረብ ነበረበት። ኃይለኛ የሆነ የጥያቄ ምርመራ ተደርጎብኝ በውይይታችን ውስጥ በኢሕአፓ ደጋፊዎች "ባንዳ" የሚል የስም ማጥፋት ደርሶብኝ እንደ ነበረ ስነግራቸው መረጃው ቅንድባቸውን አነሣው። ፖሊሱ ቃሉን ጨምሬ እንዳብራራው ሲጠይቀኝ፣ ታሪካዊ የቃሉን መገኛ ካብራራሁላቸው በኋላ፣ በአምስቱ ዓመት የጣልያን ወረራ ወቅት ከኢጣልያ ጋር የወገኑትን ኢትዮጵያውያን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል እንደ ሆነ ገለጽሁኝ። በዚህ መጥሪያ ቃል የተገለጸውን ሰው አገሩን እና ሕዝቡን አሳልፎ እንደ ሰጠ ተቆጥሮ ማኅበራዊ መገለል የሚደርስበትን ትርጉም ቃሉ እንደ ተሸከመ ተገለጠልኝ። ቃሉ ኢትዮጵያ ውስጥ በታሪክ ጥቅም ላይ ከዋለበት ዐውድ አኳያ ለምን እና እንዴት ያው ቃል ለእኔ ሊሰጥ እንደ ቻለ እኔ ራሴ ግራ የተጋባሁና ያላወቅሁ እንደ ሆንኩ ለፖሊስ መኮንኖቹ አስረዳሁ። ፖሊሱ የመረጃውን እውነትነት ለማረጋገጥ ማስረጃ ከፈለገ ለማረጋገጫ እንዲሆነው የትምህርት ቤቱን ርእሰ-መምህር ጋሽ ጥላሁንን እንዲያገኛቸው ጠየቅሁት። የትምህርት ቤቱ ርእሰ-መምህር ወደ ጣቢያው መጥተው መሰከሩ፣ ደግሞም መረጃው እውነት እንደ ሆነ አረጋገጡና ያቺ ቁራጭ መረጃ በኦፊሲያላዊው የፖሊስ ሪፖርት ውስጥ ተጨመረች። መረጃዋ መጨረሻ ላይ እንድለቀቅ አስተዋጽዖ ያደረገች ነገር እንደ ሆነች ወይም እንዳልሆነች እርግጠኛ አይደለሁም።

ጅጅጋ ውስጥ ሳለን ከፉኛ ሲመታኝ የነበረው የአካባቢው ፖሊስ አብሮን ያልነበረበት፣ ከደህንነት ቡድኑ ጋር ወደ ሐረር ያደረግሁት ጉዞ እንዳሰብኩት መጥፎ አልነበረም። ኋላ ላይ በኢሕአፓ የተገደለው የመርማሪ ቡድኑ ዋና ፖሊስ በጉዞው ውስጥ እንደ ጓደኛ ሆነልኝና የሚፈልጉት ሰው እኔ

እንዳልሆንኩኝ በተደጋጋሚ ነገርኩት። ሊሕሳሊ የሚባለው የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ መሪ የሆንኩት እኔ እንደ ሆንኩ እና የኮድ ስሜም መሐመድ የምባልበት መስሏቸው ስለ ነበር፣ ሁኔታዬን በሐቀኝነት ነገርኳቸውና እየዋሸኋቸው እንዳልሆነ ወተወትኩኝ። በእኔ ላይ ምን ሊያደርጉ እንደ ሆነ ምንም ፍንጭ ስላልነበረኝ፣ በጉዞው ወቅት ሁሉ እያለቀስኩ ከድሃ ቤተሰብ እንደ መጣሁ፣ እናቴም ወንድ ልጇን እንዳጣች፣ የእርሷ ብቸኛ መጦሪያ እኔ እንደ ሆንኩ እና የመሳሰሉትን የገዛ ራሴን የግል ታሪኮች እነግራቸው ጀመር። በታሪኬ አንደኛው ቦታ ላይ ዋናው መኮንን ስለ ቤተሰቤ ጠየቀኝና የእናቴንና የአባቴን ስም ነገርኩት። የሚያስደንቀው፣ ፖሊስ መኮንኑ እናቴን እና ሁለቱን አጎቶቼ በቀለ ዋቅቶላን እና ነጋዴውን አበበ ዋቅቶላን ወዲያውኑ አወቃቸው። ምንም እንኳን በጉዟችን ውስጥ የነበረን ውይይት የተሟሟቀ ወዳጃዊ ድባብ የነበረው ቢሆንም፣ ወደ እስር ቤት ከመወርወር ስላላስጣለኝ በዋናው የፖሊስ መሥሪያ ቤት እስረኛ ማቆያ ውስጥ ወጣቶች በሚበዙበትና ከሁሉም እድሜ የሆኑ የፖለቲካ እስረኞች በታሰሩበት ትንሽ ክፍል ውስጥ ተጨመርኩኝ። የድሬዳዋ ልጅ ተስፋዬን፣ ኋላ ላይ በአስመራ ዩኒቨርስቲ ጥሩ የሥራ ባልደረባዬ የሆነውን ዘነበን፣ የሐረር ወታደራዊ አካዳሚ ምሩቅ የሆነውን ሰለሞንን እና አሁን ስማቸውን የማላስታውሳቸውን ሌሎችን በዚያ ተዋውቄ አዲስ ጓደኛ አደረግኋቸው። ክፍሉ መጠቅጠቁ ብቻ ሳይሆን፣ በውስጥ ያለነው የታፈንን እና ብርሃን ማየት የምንችለው በተመደበው ጊዜ ላይ ብቻ ወደ ሽንት ቤት ስንሄድ ብቻ ስለ ሆነ፣ የእስር ቤቱ ሁኔታ ልክ እንደ ከፋ ቅዠት ነበር። በተጨማሪም፣ እንድንተኛ የሚደረገው በቀዝቃዛው ሲሚንቶ ላይ ያለ ፍራሽና ብርድ ልብስ በመሆኑ፣ በእነዚያ ሁኔታዎች ውስጥ ወደ ተራ እንስሳነት ደረጃችሁ የተቀነሳችሁ ያክል እንዲሰማችሁ ትገደዳላችሁ። አንድ ሰው ምሽት ላይ የተፈጥሯዊ ጥሪ ግፊት ቢደርስበት ምን ሊያደርግ እንደሚችል መገመት አያስቸግርም። ዝርዝሩ እየቀጠለ እና እየቀጠለ ይሄዳል፣ እኔም በእነዚያ አስጨናቂ ሁኔታዎች ውስጥ የተፈጠሩትን ክስተቶች ገለጻ ማቅረብ አልፈልግም። በእርግጥ ሌሎች በአስጨናቂ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈዋል፤ ደግሞም የእኔ ከእነርሱ ጋር ሲተያይ ከቁብም አይገባም።

እስር ቤት ከተጣልኩኝ ከቀናት በኋላ፣ በትንሽ ክፍል ውስጥ እንድጠየቅ ስጠራ ክስተቱን እንዲታዘቡ የደህንነት መኮንኖች ቡድን በዚያ እንዲገኙ






ተደረገ። ዋናው መኮንን ኋላ ላይ በኢሕአፓ የተገደለው ሻምበል ሰሎሞን ሲሆን፣ በምርመራው መካከል በጣም ረጅም እና ቆንጆ የሆነ ወጣት ሰው ይዘው ገቡና ከእርሱ ጋር ትውውቅ የኖረኝ እንደ ሆነ ጠየቁኝ። "የለንም" ስል በመለስኩላቸው ጊዜ፣ "እርግጠኛ ነህ፣ ይህንን ሰው አታውቀውም?" ሲሉ ደጋግመው ጠየቁኝ። ያንኑ መልሴን ሳጸናላቸው፣ የሰውየው ተራ ደረሰና ያንኑ ጥያቄ ለእርሱ ጠየቁት። ሲመልስም፣ "አዎን፣ ስሙ ጥበበ ነው" ማለቱን ተከትሎ ስለ እኔ የሚያውቀውን ሁሉ ዘርዝሮ እንዲናገር ዕድል ተሰጠው። ስለ እኔ ብዙ ያውቃል፣ ነገር ግን በመረጃዎቹ ውስጥ አንዳንድ እውነት ያልሆኑ ነገሮች ስለ ነበሩበት ጣልቃ ገብቼ ሰውዬውን ጥቂት ጥያቄዎች እንድጠይቀው ፈቃድ ጠየቅሁኝ። እርሱም ለጥያቄዎቼ እርስ በርስ የሚፋለሱ እና ልክ ያልሆኑ ምላሾችን ሰጠኝ። ከዚያ አጭር ገጠመኝ ምን ድምዳሜ እንደ ወሰዱ እርግጠኛ ባልሆንም፣ የማውቀው ነገር መልሰው ወደ እስር ቤት እንደ ወሰዱኝ ብቻ ነው። የእስር ጓደኞቼ ምን እንደ ተከናወነ ለማወቅ ጓጉተው ስለ ነበር ሁሉንም ዝርዝር ነገርኳቸው።

ኋላ ላይ ያ ወጣት ሰው በፖሊስ እንደ ተገደለ ስሰማ በእጅጉ አዘንኩለት። አጭር ቆይታ ቢሆንም እንኳን፣ እስከ ዛሬ ድረስ ያንን ገጠመኝ በግልጽ አስታውሳለሁ። ያን ጊዜ ከፖሊስ ጋር ከተታኮሱ በኋላ በቁጥጥር ሥር ሲውል ስሜን ለፖሊስ የሰጠው እርሱ ይሆን እንደሆን ምንም ፍንጭ የለኝም። አውቶቡስ መናኸሪያ ውስጥ ፖሊሱ ሲቀርበው እንዳይያዝ ለማምለጥ የመሮጥ ሙከራ አድርጎ ጥቂት ከተታኮሱ በኋላ ፈልገው ያዙት። በተያዘ ጊዜ ጥቂት የኢሕአፓ ሰነዶች ከእርሱ ጋር የተገኙ ሲሆን፣ ዕቅዱም እነዚያን ሰነዶች ከሐረር ወደ ጅጅጋ ይዞ ለመምጣት ነበር። በሚጠይቁት ጊዜ ሰነዶቹ የሚሰጡት ለእኔ እንደ ሆነ አድርጎ ስሜን ሰጣቸው። ስሜ ለምን እዚያ እንደ ገባና ለዚያ ሰው ስሜን ማን እንደ ሰጠው፣ እንዲሁም መላው ተልዕኮ ምን እንደ ሆነና ከእኔ ጋር ምን እንደሚያያይዘው ዛሬም ድረስ ምንም አላውቅም፤ የሕይወቴም አንደኛው እንቆቅልሽ እንደ ሆነ ይቀጥላል። የትኛውንም ቦርሳ ሳልሸከም በአንዳች ዓይነት አቋም የፓርቲው ከባድ ደጋፊ ሆኜ ነበር እንጂ፣ የኢሕአፓ አባል አልነበርኩም። ከፋም ለማ፣ በፓርቲው ውስጥ ከላይ ካስረዳኋቸው ሁኔታዎች የተነሣ በመዋቅር ደረጃ አልገባሁም ነበር።

ከተወሰኑ ሳምንታት በኋላ፣ በማላውቀው ምክንያት ከእስር ቤት

ተለቀቅሁ። የማውቀው አንድ ነገር የፖሊስ መኮንን የሆነው አጎቴ ዋናውን መርማሪ ሻምበል ሰሎሞንን ምንም የማላውቅ መሆኔን በመግለጽ ስለ እኔ ይለምነው እንደ ነበር ብቻ ነው። ለመለቀቄ ምክንያት የሆነው ምንም ቢሆን ምን፣ ትልቅ እፎይታ ግን ነበር። ያፈጠጠውን ሞት ወይም ከዚያም የከፋውን እንደ ተጋፈጥኩ ስለ ተሰማኝ 'ሞቼ ነበር ተነሣሁ!' ለማለት እችላለሁ።

ሞትን የተለማመድኩበት ጥግ ላይ እንድገኝ ያደረጉኝን ሁኔታዎች ባላውቅም፣ "እየሞትኩ የነበረው ለማን ነበር፣ የምሞተውስ ለማን ነው?" ስል ራሴን ጠየቅሁኝ። "በእንዲህ ያለ ደብዛዛ እና ግልጽ ያልሆነ ሁኔታዎች ውስጥ ሞቼ ቢሆን ኖሮ የሕይወቴ መሥዋዕትነት ይታወስ የነበረው እንዴት ነበር?" ስለዚህም፣ ለመሞትም እንኳን ቢሆን ይሄ ትክክለኛው ሰዓት አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ መምጣት ነበረብኝ። ጊዜው በብዙ ግራ መጋባት እና መደናበር የተሞላ ጊዜ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱ አሟሟቴ



ከሞት ማምለጥ

ምንም ትርጉም የሌለው ይሆን ነበር ብዬ ሳስብ አሳቤ አስፈራኝ። ሁላችንም በአንዳች የጋራ እብደት ውስጥ እንደ ሆንን ስላሰብኩኝ፣ የትኛውንም ዓይነት ፖለቲካዊ ትስስር ትቼ መውጣት እና የራሴን መደበኛ ሕይወት፣ በተለይም በሕይወት ለመቆየት የእኔ መኖር ከፉኛ ለሚያስፈልጋት ለእናቴ መኖር እንዳለብኝ ወሰንኩ። ከመታሰሬ በፊት 42 ኪሎ የምመዝን ቀጭን ሰው ስሆን፣ በእነዚያ ጥቂት የእስር ሳምንታት በጣም ስለ ከሳሁ፣ የሞት መንፈስ መስዬ ነበር። ከአልኮል፣ ሲጋራ እና ጫት የተነሣ ጤና የማይሰማው ሰው በመሆኔ፣ እናቴ እንደምሞት ትጠብቅ ነበር።





ከእስር ከተለቀቅሁ በኋላ፣ ለማስተማር ወደ ጅጅጋ ስመለስ በተቀየረ ድባብ ሰላምታ ተሰጠኝ። አግልለውኝ እና 'ወጣት መሸተኛ' ሲሉኝ የነበሩት ሁሉ ወዳጃዊነት እና ኀዘኔታን ያሳዩኝ ጀመር። እንደ ጀግና አድርገው ሊያዩኝ የጀመሩ ቢኖሩም፣ በውስጤ የሚሰማኝ ጀግናም ተንኮለኛም ሰው እንዳልሆንኩኝ፣ ይልቅ ግራ በተጋባ ዘመን የሚኖር ግራ የተጋባ ሰው እንደ ሆንኩ ብቻ ስለ ነበረ፣ በዚያን ጊዜ እፈልገው የነበረው ነገር ብቻዬን እንዲተዉኝ ነበር። ሁልጊዜ ቢራ ለመጠጣት ገንዘብ ስለማይኖረኝ፣ ቪኖ ወደ መጠጣት ቀየርኩና የአልኮል መጠጥ ፍጆታዬ ጨመረ። ይህ ሁኔታዬ በሌላ አገላለጽ ሲቀመጥ፣ ምናልባት ውድ ጓደኛዬ ሞገ አንድ ጊዜ እንደ ተናገረው ሂደታዊ ራስን የማጥፋት ሙከራ እያደረግሁ ነበር ለማለት ያስችላል።

1969 ዓ.ም ላይ የኦጋዴን ጦርነት ሲነሣ ታዋቂ የነበረው የምዕራብ ሶማሌ ነፃ-አውጪ ግንባር (ምሶነግ) ወጣቶችን ትኩረት አድርጎ በራሪ ወረቀቶችን ማሰራጨት ጀመረ። ግራ በመጋባቱ መካከል ላይ፣ አንዳንድ ወጣት ተማሪዎች የፋሺስታዊውን ወታደራዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚዋጋ ዴሞክራሲያዊና ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅት መስሏቸው ምሶነግን መቀላቀል ጀመሩ። በእንዲህ ያለው ግራ መጋባት ውስጥ ጅጅጋ ወይም ሐረር ውስጥ የነበሩት የኢሕአፓ አባላት ምን እያደረጉ እንደ ነበረ በእውነት አላውቅም። ሁኔታውን ለወጣት ተማሪዎች ግልጽ የማድረግን ኃላፊነት ሊወስዱ እና ከሶማሌ መንግሥት ጋር ተያይዞ ግልጽ ሳይሆንላቸው የተረዱትን የፖለቲካ ድርጅት የሚቀላቀሉትን ወጣት ወንድና ሴቶች ማስቆም ነበረባቸው።

አንዳንድ በስሕተት የተወሰዱ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን እየለቀቁ የኢትዮጵያን መንግሥት በኦጋዴን በኩል ለመዋጋት የሶማሌ ኃይሎችን ተቀላቀሉ። አንዳንድ ነገሩ ያሳሰባቸው ተማሪዎች ለተወሰኑ ሌሊቶች ጠሩኝና ስለ ኦጋዴን ጦርነት እና ስለ ተዋጊው ምሶነግ ግልጽ ውይይት እንድናደርግ፣ ደግሞም ጅጅጋ ውስጥ ላሉት ወጣቶች ሊኖር የሚገባው የፖለቲካ አቋም ምን ሊሆን እንደሚገባ እንድናስብ አማከሩኝ። እኔም በበኩሌ ስለ ድርጅቱ ይሄ ነው የሚባል ተጨባጭ መረጃ በሌለበት ምሶነግን መቀላቀል ለማንም ሰው ጠቢብ እርምጃ እንዳልሆነ አቋሜን ግልጽ አደረግሁላቸውና ምሶነግ ነኝ እያለ ያለውን ሊሆን እንደማይችል ያለኝንም የገዛ ራሴን ስጋት ነገርኳቸው። ለተልዕኮው ሕይወታችንን ከመስጠታችን በፊት ተፈጥሮውን እና ግቦቹን በጥንቃቄ

በመመርመር የየራሳችንን ትክክለኛ ፍርድ መጠቀም እንዳለብን አጸናሁላቸው። ውይይቱን አብሬያቸው ያደረግኋቸው ተማሪዎች ስም ፍቅሩ፣ ጌትነት፣ እና የመሳሰሉት እንደ ነበረ አሁን ድረስ የማስታውስ ሲሆን፣ ለምን በእኔ ላይ ብዙ እምነት እንደ ጣሉ አላውቅም። ምክንያቱም ምንም ቢሆን ምን፣ ያደረግሁት ነገር የገዛ ራሴን ግምገማ መስጠት እና ሕጻናቱ ልጆች ምሶነግን ከመቀላቀል እንዲያስቆሟቸው ምክር መስጠት ነበር።

አያሌ ወጣት ተማሪዎች ለዴሞክራሲያዊ ትግል መሰጠታቸውን ለማረጋገጥ ምሶነግን መቀላቀል እንደሚያስፈልግ አምነው የነበረው በዚህ ጨፍጋጋ ሁኔታ ውስጥ ነበር። የሚያሳዝነው፣ ለዚህ ገዳይ ውሳኔ ካደረጉት ውስጥ አንደኛዋ ሐረር ውስጥ *ባንዳ* ተብላ ስም የተሰጣት እና ከፖለቲካ ጫናው በመሸሽ መደበቂያ ፈልጋ ወደ ጅጅጋ መጥታ የነበረችው ወጣት የአደሬ ልጃገረድ ማሪያ ነበረችበት። እንዳለመታደል ሆኖ፣ መገለሉን ልታመልጠው ባለመቻሏ ምሶነግን እንድትቀላቀል ያሳሰባት የውስጥ መነሣሣቷ እርሷ እውነተኛ የአብዮቱ ሴት ልጅ እንደ ሆነች ለጓደኞቿ ለማረጋገጥ መፈለጓ ሆነ። ይህንን ውሳኔዋን ስታሳውቀኝ፣ ንጹሕነቷን ለማስመስከር ስትል ብቻ እንዲህ ያለ ትልቅ ውሳኔ ውስጥ ልትገባ እንደማያስፈልጋት ሐሳቧን እንድትቀይር በግሌ መከርኳት። በጊዜው ምክሬን የተቀበለችኝ ቢመስልም፣ አንድ ሌሊት ላይ ሙትት ብዬ እስከሰክር ከጠጣሁበት የተለምዶ መጠጥ ቤት ስመለስ በከፍሌ በር ላይ ቁራጭ ወረቀት ተያይዞ አገኘሁ። የጻፈችውን ማስታወሻ ሳነብበው፣ *"ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ታጋይም እንዲሁ ነው"* የሚል ሲሆን፣ ለግንባሩ ያላትን መስጠት አክብራ ምሶነግን ተዋጊዎችን ለመቀላቀል እንደ ሄደች ገባኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለ እርሷ ምንም አልሰማሁም።

የሶማሌ ጦር ሠራዊት እንደ ቱጉጫሌ ያሉትን ወታደር የሰፈረባቸውን የጠረፍ ምሽጎች እየጣሰ መሄድና ወደ ጅጅጋ መቃረብ ጀመረ። ከሁሉም የኦጋዴን ክልል ወደ ጅጅጋ የሚፈልሱ የተፈናቀሉ ሰላማዊ ሰዎች ይመጡ ስለ ነበር፣ ከተማይቱ የበለጠ በሕዝብ ተጨናነቀች። በተመሳሳይ መልኩ፣ ወደ ሐረር፣ ጉርሱም፣ ድሬዳዋ እና ሌሎች ራቅ ያሉ ቦታዎች ለደህንነት ሲሉ ጅጅጋን የሚለቅቁ ሰዎች ነበሩ። ሰዎች ለሕመም ወይም ለሌላ ድንገተኛ-ነክ የሆነ ችግር ከተማይቱን ለመልቀቅ አሳማኝ ምክንያት ሲኖራቸው፣ የሩስያ ወታደራዊ ዕቃ ጫኝ አውሮፕላን የነበረችውን አንቶኖቭን እንዲጠቀሙ ተደረገ። ያለችውን





ትንሽ አጋጣሚ በመጠቀም አየር ኃይሉ በሚሰጠው ዕድል ከተማይቱን ለቅቄ ለመውጣት ተከታታይ ጥረቶችን አደረግሁ። በመጨረሻ፣ ከተማይቱ በሶማሌዎች ከመያዟ ጥቂት ሳምንታት ቀደም ብዬ ለመውጣት ተሳካልኝ።[34]

እስር ቤት መቆየቴ በከፊል የራሱን አስተዋጽዖ ሳያደርግ አልቀረም ብዬ እስካስብ ድረስ ሐረር ውስጥ የቀድሞ ጓደኛዬ የሆነው ካስ ጋር ባረፍኩበት አጋጣሚ *ባንዳ* ተብሎ የተለጠፈብኝ ስም የጠፋ መሰለ። መገለሉን እስከዚህም ጊዜ ድረስ አጋፈጠው ስለ ነበር፣ ደግሞም በእነዚህ ቀናት በጥቅሉ ደስተኛ ሰው ስላልነበርኩ ይህ ሁኔታ ጥቂት የመተንፈሻ ዕድል እንጂ፣ የአእምሮ ሰላምን ግን አልሰጠኝም ነበር። በጥቅሉ፣ የተሰጠኝ መጥፎ ስም በሕይወቴ ላይ ጥቁር ጠባሳ ጥሎብኝ አለፈ። የአርጌው አብዮት መሪ ሆኜ በስፋት በመታወቄና ከመንግሥት ጋር የሚሠሩት ሌሎቹ የፖለቲካ ቡድኖች ይከታተሉኝ ስለ ነበር፣ እንዲህ ያለው ያለፍኩበት መከራ በቂ ያልሆነ ያክል አዳዲስ ተግዳሮቶችን መጋፈጥ ጀመርኩኝ። በእነዚያ ዘመናት፣ ወደ እኔ በሚጠቁሙ በሁለት የተሳሉ ሰይፎች መካከል የምኖር ስለሚመስል፣ በሁለቱም የፖለቲካ መስመሮች ውስጥ የማንም ወገንተኛ ሳልሆን መቅረቴ በጣም ግራ አጋቢ ነበር። ከዚህ የተነሣ በሁለት ጥላዎች መካከል መኖሩ ተስፋ መቁረጤን ያባባሰ እና የአልኮል መጠጥ ፍጆታዬን የጨመረ በጣም የሚያስቸግር ልምምድ ሆነ።

ጅጅጋ ለሶማሌዎች የ"ፍትሕ" ጥያቄ ተፋለምን በሚሉ የምሶነግ ሶማሌ ኃይላት በመያዟ፣ የከተማይቱ ነዋሪዎች የሚያሠቃየውን የሦስት ቀን መንገድ በእግራቸው ተጉዘው ወደ ሐረር እንዲሄዱ ተገደዱ። ከተፈናቀሉ በኋላ ስደተኞች የሆኑት አብዛኞቹ ሰዎች በሐረር ሰሜን ምዕራብ ክፍል ባለው ስታዲየም አካባቢ በመንግሥት በተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲሰፍሩ ተደረገ። በአንጻሩ ባለጠጋ ቤተሰብ አባላት ያሏቸው ሌሎች ደግሞ ሌላ የተሻለ ቦታ ሰፈሩ።

ከጅጅጋ የመጡት አስተማሪዎች በተለያዩ የሐረር ትምህርት ቤቶች እንዲያስተምሩ ድልደላ ሲደረግ፣ እኔ ተመርቄበት በነበረው በመድኃኔዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ታሪክ እንዳስተምር ተመደብኩ። ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ ከነበሩኝ አሳዛኝ ሁኔታዎች አኳያ መድኃኔዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን መቀላቀሌ ደስታን ሰጠኝ። እንደ ከበደ፣ ጥሌ እና ካሳሁን ያሉትን የጥንቶቹን ማግኘቴ እና እንደ ብሬ ያሉ አዳዲስ ጓደኞችን ማፍራቴ አስደሰተኝ። ይህ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያሉት ተማሪዎች ሁሉ

የኢሕአፓ ደጋፊዎች አሊያም ተመሳሳዮቻቸው ናቸው እስኪያስብል ድረስ ፖለቲካ ውስጥ ስለ ገቡ፣ "ትምህርት ቤቶች" ሊሆኑ የሚገባቸውን መሆን ጨርሶ ያቆሙበት ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል። በትምህርት ቤቱ ላይ ሥልጣን ያላቸው የሚመስሉት ተማሪዎቹ ሲሆኑ፣ እነርሱም በመንግሥት ላይ አድማ መትተው ስለ ነበር ትምህርት አይሰጥም። ልናስተምር ከገባንም ወደየክፍሎቻችን እንሄድና አብዛኛውን ጊዜ ከማርክሲዝም ወይም የኢትዮጵያ አብዮት፣ በዋናነትም የፓርቲ ፖለቲካን በማውራት እናበቃለን። አንድ ሰው የሚያስተምረው በማኅበረሰብ ሳይንስ የትምህርት ዓይነቶች መሆን አለመሆኑ ከግምትም አይገባም ነበር።

ታሪክን ማስተማር የእውነት ብፈልግም፣ ነገር ግን ተማሪዎች በኃላፊው ጊዜ ላይ ፍላጎት ስላልነበራቸው፣ ከአመራማሪው እና ታሪካዊው ቁስአካላዊነት ጋር በተያያዘ ያሉ አንዳንድ ፍልስፍናዊ ጉዳዮችን የማወያየት ስልት ነደፍኩ። አንዳንድ ጊዜ ከዓለም ታሪክ እና የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር የተያያዙ ርእሶችን ሳስተዋውቅ ምንም እንኳን ራሴን እንደ ቀድሞው፣ ሐቀኛው እና ተራማጁ አብዮተኛ ማውጣት ብፈልግም፣ በክፍል ውስጥ ግን በተቻለኝ መጠን ራሴን ከፖለቲካ ለማራቅ ሞከርኩ። ያ ዘመን አስተማሪዎች እንደ ጥንቱ ጊዜ የሚከበሩበት ጊዜ አልነበረም ለማለት እስኪያስችል ድረስ፣ ለመማር በማይፈልጉ፣ ይልቁንም በክፍል ውስጥ ፖለቲካን ለመወያየት በሚጓጉና በተመሰቃቀለባቸው ተማሪዎቻችው ድንገተኛ ፍላጎት ይታዘዙ ነበር ማለት ይቻላል። አብዛኞቹ በትምህርት መስክ ሳይሆን፣ በትግል መስክ ላይ እንዳሉ ይገምቱ ነበር።

ያለማቋረጥ የገነባሁት እና ሆን ብዬ እንደ ማንነቴ አንድ አካል ልይዘው እፈልገው የነበረው የአብዮተኝነት ምስሌ ያለ ምክንያት ወይቦ ስለ ጠፋ፣ በዚያ ላይ ደግሞ አባቴን ካጣሁ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወንድሜን በሞት ስላጣሁ፣ የ1970ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት በሕይወቴ የጨለማው ዘመናት ነበሩ። ለአባቴ መሞት ምላሽ የሰጠሁት እንዴት እንደ ነበር ማስታወሱ ያስደንቃል። አባቴ ለወራት ታምሞ ሆስፒታል ይማቅቅ በነበረ ጊዜ የሚሠቃየው የመጨረሻ ደረጃ በደረሰ የጉበት እብጠት እንደ ሆነ ሐኪሙ አንድ ወቅት ላይ ከነገረኝ ውጪ፣ በእብደቱ የፖለቲካ ሕይወቴ ውስጥ ሆኜ እርሱን በመደበኛ ሁኔታ ለመጎብኘት እንኳን ዕድል ሳላገኝ ቀረሁ። እንደሚሞት ባውቅም፣ ከሞተበት ቀን በፊት





ባለው ሌሊት፣ በአክስቴ ቤት ሌሊቱን እየጠጣሁ በማሳልፍበት ሁኔታ በጣም ሰክሬ ነበር እንጂ፣ ለእርሱ እንክብካቤ ለማድረግ ብዙም ግድ አልተሰኘሁም። እናቴ እና ሌሎች ዘመዶች ሁሉ እኔን ፈልገው መጥተው እናቴ በሩን ስታንኳኳ እና የአባቴን ሞት በጩኸት ስታረዳ፣ ከመጠጡ ኃይል የተነሣ ደንዝዤ ነበርና ለሚያሳዝነው ዜና ያን ያክል ቦታም አልሰጠሁትም። የማለፉን ዜና ሆስፒታል ሄጄ በይፋ ስቀበል፣ ቀጣዩ ተግባሬ ቀብር የሚከናወንበት ቦታ የት እንደሚሆን መወሰን ነበር። የተከበረ ኑሮን የመራበት ከተማ ጉርሱም ውስጥ እንዲቀበር ከወሰንን በኋላ፣ ቀጣዩ ጉዳይ ደግሞ አስከሬኑን ለመውሰድ የመጓጓዣ መኪና ከየት እናገኛለን የሚለው ሆነ። የመኪና ኪራይ ዋጋ ውድ ስለ ነበር ለዚያ የሚሆን በቂ ገንዘብ አልነበረኝም። ትንሽ ቆይቶ ግን ከትምህርት ሚኒስቴር እርዳታ መጠየቅ የሚል ሐሳብ መጣልኝና የክፍለ-ሐገሩን የትምህርት ጽ/ቤት (ፒኢኦ) መኮንኖች ቀረብኩና የአንዳቸውን መኪና እንድጠቀም እንዲፈቅዱልኝ ጠየቅሁ። ዋናው ተቆጣጣሪ ጋሽ ተድላ ለሹፌሩ የቀን አበል እስከ ከፈልኩ እና የነዳጅ ወጪውን እስከ ሸፈንኩ ድረስ ላንድሮቨሯን ለመጠቀም እንደምችል በመፍቀድ ትልቅ ውለታ ዋሉልኝ። ያንን ለማድረግ ተስማማሁና የአባቴን አስከሬን ወደ ጉርሱም ለመውሰድ ስነሣ፣ ወደ ጉርሱም በሚደረገው ጉዞ ላይ እናቴ እና የተወሰኑ ዘመዶች አጀቡኝ። የአባቴም ቀብር ሥነ-ሥርዓት አብዛኛውን ሕይወቱን እንደ ደብተራ እሸቴ ሆኖ በታማኝነት ባገለገለበት የራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ተከናወነ።

ጉርሱም ውስጥ በሕይወቴ በጣም ተስፋ አስቆራጭ ከነበሩት ልምምዶቼ አንደኛው የሆነውን ቀደም ብዬ መስከሬያለሁ። ከቀድሞ ጓደኞቼ እንደ ብሬ እና ጥቤ ያሉት የተወሰኑት ብቻ አባቴን በሞት በማጣቴ ሊያጽናኑኝ የመጡ ሲሆን፣ በሰፈሬ የነበሩ አንድ ወቅት ጀግና የነበርኩላቸው የቀሩት ወጣቶች ግን በአንዳች ባህሉን ያለመፈጸም አድማ ውስጥ ሆነው ብቅም ሳይሉ ቀሩ። እኔ ከእነርሱ እይታ አኳያ፣ አሁን ድረስ ኃዘኔታ ሊደረግልኝ የማይገባኝ ባንዳ ተደርጌ በመቆጠሬ የተሰፋ መቁረጥ ስሜት ማስተናገድ ብቻ ሳይሆን፣ ሁኔታው በጥልቀት ከነከነኝ ደግሞም አስቆጣኝ። ሰዎች እርስ በርስ በሚተዋወቁበትና በሚቀራረቡበት ትንሿ የጉርሱም ከተማ ውስጥ የገጠመኝ ሁኔታ ምን እየተከናወነ ስለ መሆኑ ትልቅ ጥያቄ አስነሣ። በሰፈሬ የሚኖሩት ወጣቶች እንደ ባህል አድማ አድርገው ችላ ያሉት እኔን ነው? ከሆነስ፣ በማን ላይ፣ አባቴ

እንደሆን በጣም የተከበረ ሰው ነበር። ወጣቶቹ ከእኔ ጋር ችግር ቢኖርባቸው እንኳን፣ ሰው የሞተበትን ቤተሰብ መጎብኘት እና ኃዘኔታቸውን መግለጥ ወይም ጥቂት የኃዘን መግለጫ ማድረግ ነበረባቸው። ፖለቲካ ባህላችንን ምን ያክል በጥልቀት እንዳበላሸውና እንደ በከለው በግልጽ የሚያሳየው አንደኛው ሁኔታ ይሄ ነው።

ነገሩ የሚረብሽ መጤ አካሄድ ስለ ሆነ እና በተለይ እርስ በርስ እንደ ትልቅ ቤተሰብ አካል በቅርበት በምንተያይበት ማኅበረሰብ እና በትንሿ የጉርሱም ከተማ ውስጥ ይህ ይሆን ዘንድ በጣም ያልተለመደ ነገር ስለ ሆነ፣ ይህንን ጉዳይ በግሌ ብዙ መረመርኩኝ። ይህንን ሁኔታ ከሌላኛው ትይዩ አጋጣሚ ጋር በተለያዩ እንቅስቃሴዎች አነጻጸርኩኝ። ጓደኛዬ ካሱ አባቱን ጉርሱም ውስጥ በሞት ሲነጠቅ ለአጭር ጊዜ ከሐረር ላየው መጥቼ አንድ ከሰዓት በኋላ ከእርሱ ጋር አሳልፌያለሁ። ወጣቶች የየራሳቸውን ጫት በየግል ይዘው መጥተው ያዘነውን ሰው ለማጽናናት በርጫ የሚቀመጡበት አዲስ ባህል ነበር። ካሱ በከተማዋ ውስጥ በሚኖሩ ደርዘን በሚሆኑ ጓደኞቹ ተከብቦ ያጽናኑት የነበረ ጊዜ፣ ምንም እንኳን ከአብዛኞቹ ጋር በቅርበት የምንተዋወቅ ቢሆንም፣ ማንም ሰው ግን ቀርቦ ሊያነጋግረኝ ፍላጎት አልነበረውም። "ይህ ቸልተኝነት ነው ወይስ ጥበብ? ይህ አብዮታዊ መሆን ነው ወይስ 'አጸፋዊ' መሆን ነው?" እያልኩ ራሴን ስጠይቅ ከረምኩ። የጊዜውን ሁኔታ እና የወጣቱን የሚያሸንፍ አስተሳሰብ መተንተን መሞከሩ ግራ የሚያጋባ ነገር እንዲሆንብኝ ያደረገው በእነርሱ እይታ ጠላታቸው ተደርጌ መቆጠሬ ጭምር ሲሆን፣ ጓደኛዬ ካሱ ግን ከእነርሱ ይልቅ አሸናፊ ጀግና ነበር። ካሱ እና እኔ ሐረር ውስጥ በአንድ ቤት ውስጥ አብረን ኖረናል ደግሞም ጥሩ ጓደኛሞች ነበርን። ያ ሁሉ ነገር ምንም ትርጉም አልፈጠረም ነበርና ሁኔታው የእውነት ልቤን ሰበረው፣ ደግሞም ሰዎች ስሜታቸውን እንዴት በእንዲህ ያለ ፍጥነት ያጣሉ፣ እንዴትስ የማያስቡ ይሆናሉ? ስል ራሴን ጠየቅሁ፤ ነገር ግን ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ አልነበረኝም። ይህ የማንም የተረጋጋ አሟሟት ሳይሆን፣ ይልቁንም የተወደደው ባህላችን የተፋጠነ አሟሟት ሁኔታን የሚያሳይ ነበር። በግልጽ ለመናገር፣ በሁኔታው ተስፋ መቁረጥ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በእነዚያ ዘመናት ሁላችንንም ከብበውን በነበሩት ከደረጃ ዝቅ የማለት እና የሕገ-ወጥነት ሁኔታችን ምክንያት በአስጨናቂ መልኩ አዝኜም ጭምር ነበር።





ከእነዚህ ነገሮች የተነሣ፣ ረዳት-አልባና ግራ የተጋባ ሆኜ፣ እንዲሁም የመጠጣት እና የማጨስ ልማዴ እየተባባሰ በሄደበት መልኩ በስሜታዊ፣ አእምሯዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዬ የእውነት የታፈንኩ መስሎ እየተሰማኝ ሕይወቴ ለወራት ያክል በከንቱነት ቀጠለ። በእርግጥ፣ ከጅጅጋ የሆኑት አንዳንድ ጓደኞቼ በ1969 ዓ.ም በኦጋዴን ጦርነት ከሆነው መፈናቀል በኋላ በካሱ ቦታ አብረውኝ ሆነው ስለ ነበር ያ በመጠኑ አጽናንቶኛል። በተለይ ከዩኒቨርስቲ ከሆኑት የድሮ ጓደኞቼ ጋር ጥሩ ግንኙነቶች ስለ ነበረኝ፣ ከቢራውና ከሲጋራው ጎን የእነርሱ ማጽናናት አብሮኝ ነበር ለማለት ያስችላል።

ሕዝባቸው እያለፈበት ባለው የከስተቶች መረብ ውስጥ ግለሰቦች እንዴት ተጠምደው እንደሚወድቁ ማስረዳት ከባድ ነገር ነው። በሌላ አነጋገር፣ ግለሰቦች ሕይወታቸው በሚፈልጉት መልኩ ለመግለጽ እና ሌሎችን ሳይጎዱ ወይም በሌሎች ሳይጎዱ በሰላም መዘዋወር የሚችሉበት ምርጫ ምን ያክል ነው የሚል ነው። በእነዚያ ቀናት የገዛ ራሴን አቋም እና ማንነት በመጠበቅ እና ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ሳይረዱኝ እንዴት አድርጌ ራሴን እንደ ቀድሞ ማውጣት እንደምችል በማሰብበት ጉዳይ ብዙ ታገልኩኝ። ሐረር አካባቢ ለነበሩትና ለማውቃቸው ለአንዳንዶቹ የኢሕአፓ መሪዎች ሰፈር እንዳልቀየርኩኝ ግልጽ ሆኖላቸው ነበር። በኾዋኾዌው ሌላኛው ጥግ ባለው በመኢሶን ላሉት ደግሞ ራሴን ምቹ በሆነው የሰካራምነት ከለላ ውስጥ የሸሸግሁኝ የተጋጋለ የኢሕአፓ አባል እንደ ሆንኩ አድርገው እንደሚያዩኝ ገምቻለሁ። ለሰፊው የሐረር ወጣት በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ የተለያየ ነገር ማለት ነበርኩኝ። ሁሉንም የተካተቱ ተግዳሮቶች ለማስተናገድ በመሞከር ውስጥ በሁሉም አቅጣጫ መጎሳቆል ሲገጥም ነገሮችን ትክክለኛ አድርጎ ማስኬድ ከባድ ነው።

በእነዚያ ዘመናት 'አቋም' የሚለው ቃል ብርቱ የሆነ ትርጉም የነበረው ሲሆን፣ የገዛ ራሴ የግል ባሕርይ ግልጽ የሆነ የፖለቲካዊ አቋሜን እንዳልይዝ የራሱን አስተዋጽዖ ያበረከተ መስሎ ተሰማኝ። ስለ ፖለቲካ ጉዳዮች በቡድን ታማኝነት ከመመራት ይልቅ እንደ ግምገማዬና እምነቴ ትርጉም ያለው ድምዳሜ ላይ በመድረስ በገለልተኝነት የማስብ ዓይነት ሰው ነበርኩኝ። ለግፊቶች አልሸነፍም ወይም ለድርጅቱ የትኛውም ዓይነት መሰጠት ራሴን በቀላሉ ለማንሸራተት እጅ አልሰጥም። ይህንን ስል ምን ማለቴ እንደ ሆነ ለማስረዳት እንደ ትረካ በማድረግ የተወሰኑ አጋጣሚዎችን እዚህ ላይ ላይይዝ።

ስሙ ሶል የሚባል የቀድሞ የዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበረ አንድ ወጣት የድርጅቱን አቋም እና የወታደራዊውን መንግሥት አቋም እያነጻጸረ በሚያሳይ የመኢሶን በራሪ ወረቀት ላይ እንድወያይ አንድ ወቅት ላይ ተጋበዝኩ። በራሪ ወረቀቷ ቅጽ 32 እንደ ነበረች እና ርእሷም 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ወይስ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት' የምትል እንደ ነበረች አስታውሳለሁ። ይህችን ወረቀት በጋራ አንብበን ደግሞም ከኢሕአፓ አቋም ጋር በማነጻጸር ይዘቱን በዝርዝር ስንወያይበት፣ በዚያ *በርጫ* ውይይት ላይ እውነተኛ የሆነውን ተሳትፎዬን አደረግሁኝና የገዛ ራሴን አይታዎች ገለጽኩኝ። ከመኢሶን ሰፈር የመጣ የመጀመሪያው ያነበብኩት ወረቀት ላይ ሐሳብ የሰጠሁ ቢሆንም፣ ወረቀቱ ያቀረባቸው ሐሳቦች ግን የምር እና በጥልቀት መወሰድ ነበረባቸው። በሌላ አነጋገር፣ ወረቀቱ ከሌላኛው ጥግ የመጣ ስለ ሆነ፣ በወረቀቱ ይዘቶች ላይ ውድቅ በሚያደርግ መልኩ መመልከት የለብንም የሚል አቋም ይዣለሁ ማለቴ ነው። እውነት ለመናገር የመሟገቻ ሐሳቡ ዝርዝር ላይ የሰፈረውን አላስታውስም፤ ነገር ግን ወረቀቱን በጥልቀት ለመመርመርና አዎንታዊ ጎኑን ዋጋ ለመስጠት እንከኑንም ደግሞ ለመጠቆም የዲያቢሎስ ተሟጋቾች የመሆንን ያክል አቋም ልንይዝ ይገባል የሚል ምልከታ ይዤ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። በሚቀጥለው ቀን፣ በድጋሚ የሐሜት መነጋገሪያ መሆን ስጀምር፣ ከመኢሶን አቋም ጋር ሙሉ ለሙሉ እንደምስማማ አድርጎ ውንጀላ ያቀረበውና *ፈዲስት* ልሆን እንደምችል ጥርጣሬውን ያቀረበው ሰው ለበርጫ በዓሉ የጋበዘኝ ያው ሰው፣ ሶል እንደ ሆነ ኋላ ላይ ደረስኩበት።[35]

ታሪኩን ከላይ የገለጽኩት አደሬው ጓደኛዬ ማህ ጋር በተያያዘ ያለውን ሌላኛውን አጋጣሚ ልተርክላችሁ። ለዚያ መጠሪያ የዳረገውን አጋጣሚ በተመለከተ ምንም ፍንጭ ባይኖረኝም፣ *ፈዲስት* ነው ተብሎ እንደ ተወራበት ሰምቼ ነበር። ምንም እንኳን ከሽሜ ጋር እኩል ባይሆንም ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው፣ ሌላው ቢቀር በ1966 ዓ.ም ከነበረው አብዮት ቀደም ብሎ ጀምሮ አብረን ማርክሲዝምን አጥንተናል። ከዘመቻ ጣቢያ 'ጠፋ' መባሉን ተከትሎ በወላጆቹ ጥያቄ ሄጄ እንዳፈላልገው ታስቦ የነበረው ሰው እርሱ ነበር። አንድ ቀን ሐረር ውስጥ ቡና ወይም ሻይ ለመጠጣት ወይም ከአካባቢው የአደሬ ሴት ነጋዴዎች የከሰዓት በኋላ *በርጫ* ለማድረግ ጫት የምንገዛበት የከተማ ማዕከል በሆነው በፈረስ መጋላ ነበርኩ። ሰዓቱ አብዛኞቹ የሐረሬ ወጣቶች ጫት





ለመግዛት እቦታው ላይ የተሰባሰቡበት የ7:00 ሰዓት ገደማ ሲሆን፣ ማህ ከፔጆ መኪና ሲወጣ አየሁት። በቀጥታ እርሱን ላገኘው ሄጄ ፍቅሬን ለመግለጽ አቀፍኩትና ወደዚያ ያመጣው ምን እንደ ሆነ፣ ደግሞም ከእኔ ጋር በርጫ ሊያደርግ ይፈልግ እንደ ሆነ ጠየቅሁት። የመጣው የዘመዱን ሞት ለቅሶ ለመድረስ እንደ ሆነና በዚሁ ቀን ወደ ድሬዳዋ እንደሚመለስ ነገረኝ። ዕቅዴ ከእርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍና ካሉት ፓርቲ ተሰላፊዎች አንጻር የእርሱ አቋም ምን እንደ ሆነ ልጠይቀው ነበር። ከአሉባልታ ይልቅ ከእርሱ አፍ በመስማት እውነት ላይ ቆሜ ስለ እውነት ልኖር የምሬን ፈልጌ ስለ ነበር ወደ ድሬዳዋ እንድመጣና እርሱን እዚያ እንዳገኘው ጋበዘኝ። ማድረግ በቻልኩ ብዬ የተመኘሁ ብሆንም፣ ሌሎች የተያዝኩባቸው ነገሮች ስለ ነበሩ ግብዣውን ሳልቀበል ቀረሁ።

ያስደነቀኝ ነገር ከዚያ ተከትሎ ያየሁት ነገር ሲሆን፣ እርሱም ከማህ ጋር በነበረኝ ውይይት በጥልቀት በተቆጡ በሚመስሉ ወጣት ሰዎች መከበቤ ነበር። አንዳንዶቹ በድፍረት ሆነው የአብዮቱ ጠላት እንደ ሆነ ከሚታሰበው ባንዳ ከሆነ ሰው ጋር ውይይት መክፈትም ጭራሽ እንዳልነበረብኝ ነገሩኝ። በምላሼም ተከታታይ የሆኑ ጥያቄዎችን እንደሚከተለው ጠየቅኋቸው፡ "ታውቁታላችሁ? *ባንዳ* እንደ ሆነ ለእኔ ለማረጋገጥ ምን ማስረጃ ታቀርባላችሁ? *ባንዳ* ቢሆን እንኳን፣ እርሱን ከመጨበጥና ከማነጋገር እኔን ልታግዱኝ ትፈልጋላችሁ?" ማንም ሰው ለጥያቄዎቼ ምላሽ መስጠት አልቻለም። እስኪደነቁ ድረስ፣ ከእርሱ ጋር በርጫ ለማድረግ ተዘጋጅቼ እንደ ነበረና ሁኔታው ፈቅዶ ቢሆን ኖሮ በየትኛው የፖለቲካ ፓርቲ የቆመ ሰው እንደ ሆነ እውነቱን ለራሴ ለማወቅ ፈልጌ እንደ ነበር ነገርኳቸው። የበለጠ ተቆጥተው ትተውኝ ሄዱ፣ እኔም ይሁንላቸው ብዬ ነገሩን ተውኩት።

ከቀድሞ ጓደኛዬ ከካስ ጋር መኖር ኃላፊነትም፣ ጥቅምም ነበረው። እርሱ በከበቡት አስተማሪዎች ዘንድ የአስተማሪዎች ኅብረት ሊቀ መንበር ስለ ነበረ እና ሐረር ውስጥ ያለው የኢሕአፓ አባላት መካከል ጥሩ ተቀባይነት የነበረው ሰው በመሆኑ፣ እንደ መሪ የሚታይ ግለሰብ ነበር። ከእርሱ ጋር መኖሬ እና መቀራረቤ አንዳች ዓይነት አመኔ መጠለያን ሰጥቶኝ ነገሮችን ከእርሱ ጋር በጣም በግልጽነት እነጋገራለሁ። እንደውም ስለ ኢሕአፓ አንዳንድ አቋሞች ያለኝን ተቃውሞዎች እና ጥርጣሬዎች እየገለጥኩለት የተለመዱ የውስጥ ለውስጥ ሥነ-ጽሑፎችን እናነብ እና የፓርቲውን የታቀዱ መልእክቶች እንሰማ

ነበር። *'ካልመረረ፣ ካልጎመራ ትግል ምኑን ትግል ሆነ?'* የሚል እና በኦሮምኛ ቋንቋ የተጻፈውን *'ከራን ብሊሱማ' (የነጻነት መንገድ)* የተሰኘውን አሰፋ በሚባል ወዳጄ የተገጠመውን ግጥም ዓይነት ሌሎችንም የሚያነሣሡ መልእክቶችን በግልጽ አስታውሳለሁ።

የተወገድሁ እና ያላግባብ ከተጣበቀብኝ ስም የተነሣ የተገለልኩ በመሆኔ ስለምሠቃይ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ መጽናናትን የማገኘው በጠጪነት ልማዴ ነበር። ከዚህ የተነሣ ራሴን በውኃ በይ ውስጥ ለመጣል የፈለግሁባቸው በኋላ ደግሞ ያቅማማሁባቸው ጊዜያት ነበሩ። ወደ ፊት እንድዘል ከውስጤ የሚመጣ የሚመከረኝ ግፊት ይሰማኝና ነገር ግን በድንገት ሐሳቤን ቀይሬ እየተንገዳገድኩኝ ወደ ቤቴ መሄዴን እቀጥላለሁ። የምሄደውም ወደ ብሩህ ጨረቃ እና ከዋክብት እየተመለከትኩ፣ ደግሞም ከጨረቃ፣ ከከዋክብቱና ከአሸዋዎች በምንም የማላንስ የአጥናፈ-ዓለም ልጅ እንደ ሆንኩ ለራሴ እያወጅኩኝ ነበር። ያን ጊዜ መንፈሳዊ ሰው የነበርኩ ባልሆንም፣ የአጥናፈ-ዓለሙ ልጅ ስለ መሆኔ ሐሳብ የመጣልኝ ለዚያ ቅጽበት ትልቅና ግዙፍ ከሆነ እንዲሁም አካል ከሆንኩበት ነገር ይልቅ፣ ከመረዳቴ በላይ በሆነ ሤራ ውስጥ አንደኛው አካል እንደ ሆንኩ የሚያስታውሰኝ ረቂቅ-ሥዕል (አብስትራክት) ነበር። በእነዚያ መስመሮች አንጻር ማሰቡ የፍንደቃ ስሜትን እና ከመሞት ይልቅ ለመኖር መመኘትን ይሰጠኝ ነበር።

እንደዚያ ሰክሬ ስገባ ካሱ ላይ ተሰፋ የቆረጥኩበትን ስሜቶቼን የምዘረግፍባቸውና ስለ ተወሳሰበው የሕይወቴ ሁኔታ ቅሬታዬን የማቀርብባቸው ጊዜያት በርካቶች ስለ ነበሩ፣ አንዳንድ ጊዜያት ላይ ካሱ "ጥበበ፣ ስለ ጉዳዩ ለምን ትጨነቃለህ? ረስተኸው ትክክለኛ ሕይወትህን ለምን አትመራም?" ይለኝ ነበር። ግትር በሆነ ሁኔታዬ "በምንኖርበት ዓለም ውስጥ ትክክለኛነት የምንለው ነገር የለም፤ በጥልቀት የተጎዳሁ ስለ ሆንኩ ችግሮቼን መርሳት አልችልም፤ ሁኔታዬ መቋጫ እንዳላገኘ በጥልቀት ሕሊናዬ ያውቀዋል፤" እለው ነበር። ለትውልዴ አባላት እኔ ንጹሕ ሰው እንደ ሆንኩ የማሳውቅበትን እና አብዮተኛ እንጂ፣ እንደ ተወነጀልኩበት ስም *ባንዳ* እንዳልሆንኩ አሳይቼ ለመሞት የምፈልግበት አንዳች ዓይነት የውይይት መድረክ ተዘጋጅቶ ዕድል በተሰጠኝ እያልኩ እመኘለሁ። ነገር ግን፣ ከተወነጀልኩበት ነገር ነጻ ያደረገኝ ፓርቲም ሆነ ቡድን አልነበረም። እንደ





ተቆለፈብኝ እና ለአብዮቱም፣ ደግሞም ትውልዱ እየከፈለው ላለው መሥዋዕትነት ምንም አስተዋጽዖን ትርጒም ባለው መልኩ ማድረግ እንዳልቻልኩም ተሰምቶኝ ነበር። ለዚህም ይመስለኛል ቅኔያዊ በሆነ መልኩ ስለ እኔ ሁኔታ አስተያየቱን ሲሰጥ፣ "ጥበበ ማለት በጭንቅላቱ ችግር ይዞ የሚዞር ሰው ነው" ሲል ካሱ ተናግሮ የነበረው።

ከካሱ ጋር የነበረኝ ጓደኝነት ሌላ ዓይነት ገጽታም ነበረው። እኔና ካሱ በአእምሯዊም ሆነ ማኅበራዊ ነገር ለረጅም ጊዜ ተጣጥመን መሄድ የምንችል ሰዎች ስለ ነበርን፣ እንደገናም ደግሞ እርሱ ልክ እንደ እኔ ጥሩ አንባቢ በመሆኑ ብዙ ነገሮችን አብረን ስለ ተካፈልን፣ ከእርሱ ጋር የሚኖሩኝ *የበርጫ* ጊዜዎች በፍቅር የምናፍቃቸው ነበሩ። ምንም እንኳን ካሱ ይፋዊ በሆነ መልኩ ከሚስቱ ጋር የተፋታ ሰው ባይሆንም፣ ልጃገረዶችን ወደ *በርጫ* ክፍለ-ጊዜዎቻችን እንጋብዝ ስለ ነበር፣ ልክ እንዳላገባ ሰው በነጻነት ይኖራል። አንድ ጊዜ በነበረው "ቀይ እና ነጭ ሽብር" ተብሎ በሚታወቀውና በመንግሥትና በሕዝብ መካከል በተፈጠረው ግብግብ ውስጥ፣ ሁለት ልጃገረዶች ሊጎበኙን የመጡበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ። አንደኛዋ በሩን እንዳለፈች 'እግራችን እርጥብ ነው፣ ሶላቶውን አነጠፉት' በማለት እኔን በጣም የሚረብሽ ነገር ተናገረች። ልጃገረዶቹ እየተናገሩ የነበረው ስለ ሬናልቶ ሲሆን፣ እርሱም ከኢጣልያዊ አባት እና ኢትዮጵያዊት ከሆነች እናት የተወለደ፣ በመድኃኔዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሒሳብ መምህር የነበረና ልጃገረዶቹ በጎበኙን በዚያ ቀን በኢሕአፓ ተገንጣይ ጓዶች የተገደለ ሰው ነበር። እርሱ ወጣት፣ ረጅም እና ውብ ሰው ሲሆን፣ ስለ እርሱ ከርቀትም ቢሆን የማውቀው ነገር እንደ ገብሬ ባሉ በጊዜው የመኢሶን ብርቱ ደጋፊዎች ከሆኑ አብዮተኞች ጋር ጓደኛ እንደ ነበረ ብቻ ነበር። ገብሬ ደግሞ የአካባቢው ብሩህ ጭንቅላት ያለውና አዲስ አበባ ውስጥ በኢሕአፓዎች የተገደለ የቀድሞ ተማሪ ሲሆን፣ ሬናልቶ በበኩሉ የመኢሶንን ንድፈ-ሐሳባዊ አቋሞችን የሚደግፍ ሰው ነው ሲባልም ሰምቻለሁ። እርሱ እንደ ግለሰብ የትኛውንም ዓይነት ፖለቲካዊ አቋሞች እና እይታዎች ለመተው መብት እያለው አገሪቱን እንደ ጎዳ ተደርጎና ሕዝቡን ለሚያበላሽ ጉዳይ ማስረጃ ባልተገኘበት ሁኔታ የራሱ የሆነ ፖለቲካዊ እምነት ስለ ነበረው ብቻ መገደሉ ተገቢ አልነበረም። የእርሱ መሞት የእኔን ሰብዓዊነት በጥልቀት ነካውና በመደብ ትግል እና የፖለቲካ ቅድስናን በመያዝ ስም በሕዝቡ ላይ እየሆነ ባለው ነገር

ተበሳጨሁ። የእርምጃውን ግብረ-ገባዊ ፋይዳ ላገኘው ስላልቻልኩ፣ *ከበርሜሉ* በዓል በኋላ ስሜቶቼን ለካሱ አሳየሁትና ስለ ተፈጠረው አስጨናቂ ኢጋጣሚ ደስ አለመሰኘቴን ነገርኩት። በአጋጣሚው እኔ ያዘንኩትን ያክል እርሱ ያዘነ አልመሰለኝም፣ ስለዚህም ሙግት መጀመር አልፈለግሁም። ስለዚህም፣ ምንም እንኳን ፓርቲውን እንደ ተራማጅ ድርጅት እንደ ማክበር ምንም ጥርጥር የሌለው ቢሆንም፣ የኢሕአፓ አባል እንዳልሆንኩኝ ካሱ በእርግጠኝነት አወቀ። እኔም በበኩሌ ነገሮች ከፈራረሱም በኋላም እንኳን ያንን ባይገልጥልኝም፣ ካሱ አንዳች ከፍተኛ ሥልጣንን የያዘ የፓርቲው አባል እንደ ሆነ በተወሰነ መልኩ አውቅ ጀመር። እኔ አተያዮቼን ተጠርጣሪ ሳልሆን እንድናገር በሚፈቅድልኝ አንዳች ዓይነት አንጻራዊ ራስ-ገዝነት ስመራ፣ በሚያሳዝነው የሬናልቶ ሞት ላይ ግን ያ የእርሱን ቁጥብ አቋም ያስረዳል።

ጓደኛዬ ካሱ እና እኔ የተከለከውን ድብቅ ሥነ-ጽሑፍ በጋራ ካነበብን በኋላ፣ የተጋጋሉ ሙግቶችን ያደረግንባቸው በርካታ አጋጣሚዎች ይታወሱኛል። ከሶማሌ ወረራ እና የኢትዮጵያውያን ወታደሮች ዕጣ ፈንታ ጋር በተያያዘ አንድ ያጋጠመኝን ነገር እዚህ ላይ መጥቀስ እፈልጋለሁ። አንድ ምሽት ላይ በምሕጻረ-ቃል ኢሕአሠ (የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ሠራዊት) ተብሎ በሚጠራው ጦር ሠራዊት የተጻፈ ወረቀት አብረን አነበብንና በይዘቱ ላይ የተቀጣጠለ ክርክር አደረግን። ወረቀቱ የሚያስቀምጠው ጉዳይ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ምንም እንኳን ሳንጃዎቻቸው በምዕራብ ሶማሌ ነጻ አውጪ ግንባር ላይ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም፣ ከሶማሌ ጦር ሰራዊት ይልቅ ወደ ፋሺስታዊው የኢትዮጵያ መንግሥት መቀሰር እንዳለባቸው ይናገራል። ይህ ነገር በኢትዮጵያውያን ወታደሮች አሰላለፍ ላይ በአስጨናቂ ሁኔታ ጫና ስለሚኖረው እንዲህ ማድረጉ ደመ-ነፍሳዊ አጸፋ ነው ስል መከራከሪያዬን እያቀረብኩ ወታደራዊ መግለጫዎቹ እንኳን ቀርቶ በተፈጥሮ በምናገናዝበው የአስተሳሰብ ደረጃዎች እንኳን ጨርሶ የሚያሽመደምድ አቋም ነው ስል ተከራከርኩኝ። ራሱን በኢትዮ-ሶማሌ ድንበር ላይ አቁሞ ወረራ የሚያደርገው ወታደር በታንክ ሲቀርበው እና ጠላት ወደ እርሱ ሲጠጋ ይዋጋል ወይስ ሳንጃውን ያጥፋል? በማለት ራሱ ካሱ በኢትዮጵያዊው ወታደር አሰላለፍ ቦታ ላይ ሆኖ ነገሩን እንዲያየው ብፈልግም፣ ለዚያች ምሽት ምንም ትርጉም ያልሰጠ ውጤት-አልባ እና የተሟሟቀ ውይይት አደረግን። ይህም ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት በነበረው አለመስማማት፣ ከግል





ስሜት እና ከገሃዱ ዓለም ሁኔታዎች ጋር ተያይዘው ባሉት ጉዳዮች ሁሉ እዚህም እዚያም እየዋዠቅን አላስፈላጊ ወደ ሆኑ የንድፈ-ሐሳባዊ ውይይቶች ገባን። በዚያ ሌሊት፣ ሁለታችንም በእጆቻችን የጦር መሣሪያዎች ኖረውን ቢሆን ኖሮ ጭቅጭቆቹ አስጠሊታ እና በጣም የግል ስለ ነበሩ ነገሮች የተለዩ ይሆኑ ነበር። እንዲህ ዓይነት ሐሳባዊ ትግል በሚኖረን ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት እርስ በርስ ሳንነጋገር እንቆይና ከዚያም ብዙም ሳንቆይ አንድ ቤት የምንጋራ እና የጋራ ፍላጎቶችንም የምናስተናግድ በመሆኑ እንታረቃለን።

የምንታረቅበት ሁናቴ አብዛኛውን ጊዜ ታዋቂ በነበረው የቦቲ ሆቴል፣ ምግብ ቤት እና ጭፈራ ቤት ውስጥ ተገናኝተን ወይ እየጠጣን አሊያም ከጭፈራ ቤቶቹ በአንደኛው ጊዜ እያሳለፍን ብሎም የደስታ መንፈስ የተሰበረውን ጓደኝነታችንን እንዲጠግነው እየፈቀድን ነበር።

ከካስ ጋር ስላለኝ ጓደኝነት የምናገረው ብዙ ነገር አለኝ። አንዳንድ ጊዜ ሐረር ውስጥ የታፈነን መስሎ ስለሚሰማን ለለውጥ ወደ ድሬዳዋ እንሄድና የምንወደው ሆቴል ውስጥ ክፍል ተከራይተን፣ በየጎዳናዎቹ ዞረን እና በአካባቢው የከተማ ማዕከል ቡና ቤቶች ተንቀዋልለን፣ ጠጥተን እና ደስታን አጣጥመን ገንዘባችንን ካባከንን በኋላ ወደ ሐረር እንመለስ ነበር። ከጉርሱም የሆነውን ጓደኛዬን እና ደደር በማስተምርበት ጊዜ የሥራ ባልደረባዬ የነበረውን ተሼን ለማግኘት ወደ ድሬዳዋ በራሴ የሄድኩበት አንደኛው ሌሊት ላይ አንድ እንግዳ ነገር ተከሰተ። ከተሼ ጋር የረጅም ጊዜ፣ ሆኖም ግን በተወሰነ መልኩ ግልጽ ያልሆነና በምጸት የተሞላ፣ ግንኙነት ስለ ነበረኝ በአጭር ቃል 'እርሱ ጓደኛዬ ነበር፣ ግን ደግሞ ጓደኛዬም አልነበረም!' ለማለት እችላለሁ። የሚያገናኙን፣ ደግሞም የሚለያዩን ነገሮች ስላሉን፣ አንድ ጊዜ ተሼ የእርስ በርሳችንን ትስስር ባሕርይ ለመግለጽ፣ "ፍላጎት ያጣ ግንኙነት" የሚለውን መግለጫ ተጠቅሞ ያውቃል።

ተሼ እና እኔ በአንደኛው ከሰዓት በኋላ ላይ *ለበርሜል* ተቀምጠን እየቃምን ቆየንና ከቆይታ በኋላ ተለያየን። እኔ ፈጽሞ ስክሬ ወደ ሆቴሌ ተመለስኩኝና በሆቴሉ እንግዶች እና ደንበኞች ፊት ለፊት፣ እብራተኛ ባሕርያት ማሳየትን ጨምሮ፣ እንግዳ የሆኑ ነገሮችን ማሳየት ጀመርኩኝ። ከዚያ በኋላ የማስታውሰው በከፍተኛ ሁኔታ መደብደቤን፣ ከሆቴሉ መወርወሬን እና ጎዳና ላይ ተዘርሬ ማደሬን ሲሆን፣ ከንጋቱ 5፡00 ሰዓት አካባቢ እየተንዘፈዘፍኩ

ነቃሁ። በእነዚያ ዘመናት መንግሥት በጣለው የሰዓት እላፊ ገደብ ከምሽቱ 5፡00 ሰዓት በኋላ ሰዓት እላፊውን የሚጥስ የትኛውም ሰው ይታሰር ስለ ነበረ፣ ይህ ሁኔታ በጣም አደገኛ ነበር። ታሳሪው ጸረ-አብዮተኛ እንደ ሆነ ከተጠረጠረ ደግሞ እስከ መገደል የሚያደርስ ኮስታራ ውጤቶችን ሊጋፈጥ ሁሉ ይችላል። መንግሥት የነጻ እርምጃ የሚባለውንና ጸረ-አብዮተኛ እንደ ሆነ ለጠረጠሩት ሁሉ የመንግሥት ካድሬዎችም ሆኑ የፖሊስ አባላት ነፃ እርምጃ እንዲወስዱ የፈቀደበት ጊዜ ነበር። በነቃሁ ጊዜ፣ የታነቅሁ እና መተንፈስ የማልችል ሆኖ ሲሰማኝ በአፍንጫዬ ይፈስ የነበረው ደም ረግቶ እንደ ነበረና ከፊቴ ላይ በዘዴ ማስወገድ እንደ ነበረብኝ ተገነዘብኩ። በወቅቱ የኪስ ቦርሳዬ ምንም ሳይጎድለው እና ሰዓቴም ሳይወሰድ ማግኘቴ እያስደነቀኝ፣ የተደበደብኩት በዘራፊዎች እንዳልሆነ ወደ አንዳች ድምዳሜ መጣሁ። ጊዜውን ከሰዓቴ ላይ ስመለከት ገና ጠዋት ሲሆን፣ ከሰዓት እላፊው ማብቂያ በፊት ለመሄድ የአንድ ሰዓት ያክል ጊዜ እንደ ቀረኝ አስተዋልኩኝ። ከሌሊቱ ቅዝቃዜ የተነሣ እየተንሰፈሰፍኩኝ፣ ጊዜያዊ መጠለያ ፍለጋ ዙሪያዬን ስመለከት ዳር ይዞ የቆመ ትልቅ መኪና አየሁና የቀበሌ ሰዎች እንዳያዩኝ በጥንቃቄ ወደዚያው አመራሁ። ክፍት ወደ ሆነው የመኪናው ጎን በዝግታ ተጠጋሁና ዘልዬ ስገባ፣ እስከደነቅ ድረስ፣ ካልተጠበቀ አጋጣሚ ጋር ተፋጠጥኩ። ከሴት ጋር የደስታ ጊዜ እያሳለፈ የነበረው ረዳት ሹፌሩ ወደ መኪናው እንደ ዘለልኩ በፍጥነት ተነሣና ባልተጠበቀው አገባቤ ግራ ተጋብቶ እጄን ያዘኝ። በደመ-ነፍስ የመታወቂያ ካርዴን አሳየሁትና የደረሰብኝን ስነግረው ከብርድ ልብሶቹ አንደኛውን እስኪያካፍለኝ ድረስ አዘነልኝና ሰዓት እላፊው እስኪያልቅ ድረስ በዚያ እንድቆይ ፈቀደልኝ። ንጋት ላይ ወደ ተሼ ቤት ሄጄ ለተፈጠረው ነገር በከፊል ከወቀስኩት በኋላ፣ ወደ ሐረር ከመመለሴ በፊት ሰውነቴን ተጣጥቤ ለተወሰነ ጊዜ እረፍት አደረግሁኝ። ሰዓት እላፊው ከመጀመሩ በፊት ከሆቴሉ ተጣልኩኝና ማለዳ 5፡00 ሰዓት አካባቢ በነቃሁበት አጋጣሚ ውስጥ ወደ ብርሃን የመጣው ምንድን ነው? ሞቼ ነበር፣ በሞት ጫፍ ላይ ነበርኩ፣ ወይስ ድብደባው ወደ ጥልቅ እንቅልፍ ላከኝ? ለእነዚህ ጥያቄዎች ምንም መልስ እስከማይኖረኝ ድረስ በዚያ ሌሊት የሆነው ነገር እስከ ዛሬም ድረስ ምሥጢር እንደ ሆነ አለ። እኔም ወደ ድሬዳዋ ልዝናና የሄድኩበት የመጨረሻው ጉዞ ያ ብቻ እንደ ሆነ ቀረ።

ምንም ምቾት የማይሰጡኝ በርካታ የተወሳሰቡ ነገሮች የተከናወኑበት





ወቅት ስለ ነበረ፣ በመላው ሕይወቴ ውስጥ ጨለማ የነበሩት ጊዜያት እነዚያ ነበሩ። አንዳንዶቹ የሆኑት ነገሮች በእኔ ዙሪያ ያጠነጠኑ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ተመሳሳይ ጉዳቶችን በሥቃይ ያስተናገዱትን፣ ነገር ግን ለመቋቋም አቅሙ ያልነበራቸውን የገዛ ራሴን ትውልድ የተመለከቱ ነበሩ። በዩኒቨርስቲ ታዋቂ የነበረው አደሬ አብዮተኛ ቦብላ ወታደራዊውን ትምህርት ቤት ትቶ ዩኒቨርስቲ የገባ ሰው ሆኖ ሳለ፣ ልክ እንደኔው *ባንዳ* ተብሎ በመጠራቱ በጣም አዝኜለታለሁ። ይማር በነበረበት በፖለቲካ ሳይንስ የትምህርት ክፍል ውስጥ በአብዮታዊው ትግል ላይ በጣም ንቁ ተሳታፊ ተደርጎ ይቆጠራል። እርሱ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ የወረት ጊዜ ላይ የምርጫ ዘመቻዎችን በማደራጀት በስፋት የተሳተፈ፣ ከወታደራዊው መንግሥት ጋር ወደ ሶማሌ ደስተኛ ሳይሆን የሄደ እና የዚያድባሬ መንግሥት ከኢትዮጵያ ወታደራዊው መሪ መንግሥቱ ኃይለማርያም ምንም ያልተለየ እንደ ሆነ ሲረዳ የተመለሰ ሰው ነበር። ለዚህም ነው ለምን ባንዳ እንደ ተባለ ምንም ሊገባኝ ያልቻለው። እርሱም በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ድብርት ከዚያም ወደ ፍጹም እብደት እስኪሄድ ድረስ ተጎድቶ ለሲጋራ እና ለአልኮል ገንዘብ እየለመነ በጭፈራ ቤቶች አካባቢ ሲመላለስ አየው ስለ ነበር፣ በቀደሙት ጊዜያት ያደረገውን አስተዋጽዖ ከግምት በማስገባት ለምን ምሕረት እና ኀዘኔታ እንዳልተደረገለት ብዙ ጊዜ እራሴን እጠይቃለሁ። ሆኖም ግን፣ ሌላው ቢቀር የእርሱን አደሬ ጓደኞች ጨምሮ፣ ማንም ሰው ሊረዳውና ሊታደገው አልቻለም። ኋላ ላይ በሳንባ ምች ታሞ እንደ ሞተ ሰሰማ፣ *በቦቴ እና ሊደጋን መንገዶች* ላይ በምሽቶች ተራቁቶ ይሄድ የነበረ ሰው በመሆኑ እንደዚህ ታሞ መሞቱ አላስደነቀኝም። የተማሪዎችን እንቅስቃሴ ጉዳይ ወደ ፊት እንዲገፋ በከፍተኛ ሁኔታ ዋጋ ከከፈሉ ሰዎች አንዱ እርሱ ነበርና በእንዲህ ያለ የሚዘገንን ሁኔታ መሞቱ ነገሩን የሚያሳዝን አጋጣሚ አደረገው። እንደ እርሱ በከንቱ ከተሠቃዩ ከብዙዎቹ መካከል ሌላኛው ሰው ከደሃ ቤተሰብ ተወልዶ ዩኒቨርስቲ የገባውና በምሕንድስና ትምህርት አሉ ከተባሉት ሰቃይ ተማሪዎች አንደኛው የነበረው ተማሪ እንግዳው ነበር። የሚያሳዝነው፣ እርሱም እንዲሁ ስሙ በመጥፋቱ የተጎዳ ሌላኛው ሰው በመሆን ባልተነገሩ በርካታ ዘግናኝ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ እንደዚያው አብዶ ቀረ። የቀድሞ ጊዜዎቹን ፈጽሞ የማያውቅና በሰፈሩ አካባቢ ወዝ አደር ተሸካሚ እንደ ሆነ የኋላ ኋላ ሰማሁ፤ ምን ዓይነት ምጸት፣

ምን ዓይነት መሥዋዕትነት ነው!

ልክ እንደዚህ ስማቸው ያልጠፋባቸው፣ ነገር ግን ሐረር ውስጥ ባሉት ወጣቶች የተተዉ አንዳንድ ገለልተኛ ምሁራን እንደ ነበሩ ትዝ ይለኛል። ያኔ የሥነ-ምድር ተማሪ የነበረው ደቤ ከእነርሱ አንደኛው ሲሆን፣ ለኢፒድ ይሠራ ነበርና አብዛኞቻችን እናገኘው የነበረውን ገንዘብ በቀላሉ ስለሚያገኝ ሁኔታው ከብራሞቹ ጥግ አስቀምጦት ቆይቷል። ከብዙ ጊዜ አንድ ጊዜ በጋራ *በርጫ* እናደርግና በሸዋበርና በቡቴ መካከል ወዳለው ታዋቂ ወደ ነበረው ጠጅ ቤት አሳዛኝ ጭፈራዎችን ለማድረግ እንሄድ ነበር። እርሱ ከየትኛውም ፓርቲ ጋር ያልተጎዳኘ በሚመስልበት ሁኔታ በአብዛኞቹ ወጣቶች የፖለቲካ እይታ ብስለት ማጣት ጨርሶ ተስፋ ቆርጦ ኢሕአፓን በጣም ይተቻል።[36] ሌላኛው ገለልተኛ ምሁር ዶላች የሐረር ሰው ተደርጎ የሚቆጠረው ዮሐንስ ሲሆን፣ እርሱ ከዊንጌት ትምህርት ቤት ወደ ዩኒቨርስቲ የገባ ብሩህ ጭንቅላት የነበረው ሰው ነበር። ዮሐንስ አብዮቱ ሲፈነዳ የቅድመ-ሕክምና ተማሪ የነበረ፣ ኮስታራ አንባቢና ጠልቆ የሚያስተውል ሰው፣ እንዲሁም በአንዳንድ መንገዶች ብቸኛና በቡቴ ጭፈራ ቤት ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ ከብዙ ጊዜ አንዳንድ ጊዜ የማገኘው ሰው ነበር። ስለዚህም መቀመጫ ሳብ አድርጌ ለጥቂት ጊዜ አነጋግረውና በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታ በተመለከተ ባለው ጥልቅ ምልከታዎች ላይ እንደዚሁም በጥቅሉ በሰሻሊስቱ ከንፍ እውቀቱ ሁልጊዜም እደመማለሁ። እርሱ በአንድ ፓርቲ ውስጥ ተይዞ በዚያ እንደ ታሰረ ሊቆይ የማይችል ነገሮችን በጣም በትንታኔ የሚያይ ሰው ሲሆን፣ ስለ ኢትዮጵያ አብዮት ተፈጥሮ እንደ ከስተት ኮስተር ያሉ ጥርጣሬዎች እና ጥያቄዎች ነበሩት። ደግሞም ስለ ወጣቱ ትውልድ እና በደፈናው ስለ ኢትዮጵያም በከፍተኛ ሁኔታ ተጨንቆ ነገሮችን ዛሬ ላይ ከሚታዩበት ሁኔታ ባለፈ ይመለከታቸዋል። ቀድሞ ወደማያውቀው የመጠጥ እና የማጨስ ወጥመድ ውስጥ እስኪገባ ድረስ በራሱ ጊዜ እያየቸው ባሉት ነገሮች በጣም ተስፋ ቆርጦ ስለ ነበር፣ መጽናኛ እንዲሆነን ከአንደኛው የጆንል አካባቢ ጠጅ ቤት ወደ ሌላኛው እንሄድና *ቆርንጄያችንን* (ባገለገሉ ወይም በተጣሉ ወረቀቶች የተጠቀለለ ትንባሆ) እናጨሳለን።[37] በእነዚያ ዘመናት ገለልተኛ አሳቢዎች የሚባሉት ይኖራቸው የነበረው የዕጣ ፈንታ አዝማሚያ ይህ ነበር።





1968 ዓ.ም ውስጥ በሕይወቴ ይከናወኑ የነበሩ በርካታ አሳሳቢ ነገሮች የነበሩ ሲሆኑ፣ ከእነርሱም ውስጥ ጥቂቶቹን ብቻ እገልጻለሁ። አንድ ጊዜ ከሰዓት በኋላ ላይ የበርጫ ሰዓታችን እስኪደርስ እኔና ጓደኞቼ የምንዘርበት ሐረር ውስጥ ታዋቂ በሆነውና አንደኛ መንገድ ተብሎ በሚጠራው መንገድ እየሄድኩ ነበር። መንገዱ በግራና በቀኝ በኩል ሱቆች ያሉበት ጠባብ መንገድ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ በመስኮት የተንጠለጠሉትን፣ ደግሞም "የዓይን" የሆኑትንም ልንሸምት የምንሄድበት መንገድ ነበር። መንገዱ ለሐረሪ ወጣቶች ልክ እንደ አዲስ አበባው ፒያሳ እንደ ማለት ነው። ታዲያ በዚያ እየሄድኩኝ እያለ፣ አንዲት ሾልስዋገን መኪና በድንገት ቆማ ስሙን አሁን የማላስታውሰው አንድ የማውቀው ሰው ከመኪናው ወረደና ትከሻዬን ይዞ ወደ መኪናው አስገባኝ። እርሱ አስተማሪ፣ ደግሞም የካሱ ጥሩ ጓደኛ የነበረና የመኢሶን ብርቱ ደጋፊ ከሆነበት የፖለቲካ ልዩነቶች የተነሣ ያፈነገጠ ተደርጎ ይታያል። እንዲሁም ደግሞ ያን ጊዜ የመንግሥት መንገድ ጠራጊ ተብለው ከሚታወቁትና በ1976 ዓ.ም ተቋቁሞ ድጋፍ ያገኘ የነበረው የላብ አደር ፓርቲ አንደኛው መኮንን ሆኖ ሠርቷል። እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ምንም ትርጉም የሌለውን "መንግሥት አፍራሽ የጅጅጋው ሰው" የሚለውን አስቂኝ ነገር ተናግሮ የተጠረጠሩ የኢሕአፓ አባላት ወደሚታሰሩበትና ቶርች የሚገረፉበት ራስ መኮንን አዳራሽ ወሰደኝ።

ከዚያም በኋላ፣ ኃላፊነቱ ሰዎችን በሌሊት ወደ ትንሽ ከፍል ወስዶ በአካባቢው አጠራር 'ወፌላላ' የሚባለውን ግርፊያ መግረፍ ለሆነው ዝነኛ ሰው አስተዋወቀኝ። አብዱል ይባል የነበረውን፣ ከተወለድኩባት መንደር ከጉርሱም የሆነውን ይህንን ሰው አውቀው ነበርና በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዴት ሲሳተፍ እንደ በቃ ሳይ በጣም ተገረምኩ። እርሱ የባለጠጋ ነጋዴ ልጅ ሲሆን፣ እርሱ ራሱ ሐረር ውስጥ እያደገ ያለ ሱቅ አለው። ለፖለቲካ ፍላጎት ለሌለው ሰው የሚሰጠው *ባንዳ* የሚለው ስም ተሰጥቶት ከተጎዱት ውስጥ አንዱ እርሱ ሲሆን፣ ሰዎች ከእርሱ ሱቅ ላለመግዛት አድማ እስኪያደርጉ ድረስ በጣም ተገልሎ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። የሸማቾቹ አድማ የእርሱን ንግድ ሥራ ወደ ኪሳራ ስላመጣው፣ ከዚህ ተስፋ መቁረጥ የተነሣ የመኢሶንን ፖለቲካዊ ሰፈር ተቀላቀለ። የተጠረጠሩ የኢሕአፓ ኮብላዮችን ለመምታት ተግባር ለምን ኃላፊነት እንደ ተሰጠው ብዙ ጊዜ እጠይቅ የነበረ ሲሆን፣ የእኔ ጥርጣሬ ፓርቲውን የሚያገለግልበት ሌላ ምንም ክህሎቶች ስለሌሉት፣ አሊያም ደግሞ

ባንዳ ብለው ስሙን በማጥፋት ኩራቱን ያቆሰሉበትን ለመበቀል ምርጥ አጋጣሚ ስለ ሆነለት ነበር።

እርስ በርስ ከልጅነታችን ጀምረን በአንድ መንደር እንደ ማደጋችንና እንደ መተዋወቃችን፣ ለምን እኔን ለመምታት ራሱን እንደሚገፋፋ ግራ ገብቶኝ እያለሁ፣ ጓደኛዬ ሽሜ እንደ ጠባቂ መልዓክ ድንገት ብቅ አለና በቁጥጥር ሥር ባዋለኝ ሰው እና በአስጨናቂው ገራፊ መካከል ቆሜ አየኝ። በአጋጣሚው የተደነቀው ሽሜ፣ 'እዚህ ምን አመጣሽ?' በማለት ጠይቆኝ መልስ ከመስጠቴ በፊት፣ ያመጣኝ ሰው ጣልቃ ገባና፣ ‹‹ዋጋውን ሊያገኝ ነው፡፡ ይህ መንግሥት አፍራሽ የጅጅጋ ሰው›› በማለት ተናገረ። ሽሜ ወደ እርሱ ተመለከተና ፈገግ ብሎ፣ "እናንተ ሰዎች የምታደርጉትን አታውቁም። ወንጀለኞችን ከምስኪኖች መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ?" በማለት ጠየቃቸው። ሰውየው ሽሜን፣ "እርግጠኛ ነህ ይህ ሰው ንጹሕ ነው?" ሲል መልሶ ጠየቀው። ሽሜ ጠላቶቻቸውን እንዳላወቁ በመግለጽ ጥብቅ እና የሚያረጋግጥ መልሱን ከሰጣቸው በኋላ እንዲለቅቁኝ በሥልጣን ተናገራቸው፣ በዚያ ሌሊት ልጋፈጠው እችል ከነበረው የማይገመት ክፉ ነገር ታደገኝ። እነርሱም ወዲያውኑ ለቀቁኝና እንደ ደነገጥሁ ወደ ቤቴ ሄድኩ። በዚያች የራስ መኮንን አዳራሽ ትንሽ ክፍል ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ምሕረት-የለሽ ድብደባ ደርሶባቸው እንደ ነበረ ታሪኮችን እሰማ የነበረ ሲሆን፣ እኔ ግን ክፍሏን ጎበኘኋት፣ ነገር ግን ባልጠበቅሁት መንገድ ግርፊያውን አመለጥኩኝ።

ሌላኛው በስፋት ልገልጸው የምፈልገው አጋጣሚ ሲበዛ አደገኛ የነበረው እና ትዝታው ዛሬም ድረስ የሚያስደነግጠኝን ክስተት ነው። ከትምህርት በኋላ፣ ከሥራ ባልደረቦቼ ጥሌ እና ገዜ ጋር ምሳ ልንበላ በቦቴ ጎዳና ቁልቁል እየወረድን በመጓዝ ላይ ነበርን። ከላሸንኮቭ የታጠቁ ወጣቶች በድንገት አስቆሙንና ከሁለቱ ጓደኞቼ ለይተው ከከበቡኝ በኋላ እነርሱ እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው። በዚህን ጊዜ አእምሮዬ የጫረው የመጀመሪያው ጥያቄ፣ "ከሁለቱ ቀድሞ የሚገድለኝ የትኛው ይሆን?" የሚል ሲሆን፣ 'ደሜ በከንቱ ሊፈስ ነው?' ስል ለራሴ አጉተመተምኩ። ከየትኛው የፖለቲካ ፓርቲ እንደ መጡ ለማወቅ ዕድሉን ሳላገኝ፣ በዚያው ቅጽበት ውስጥ ዙሪያውን ተመለከትኩና ለማምለጥ አስተማማኝ ወደ ሆነው በአቅራቢያዬ ወደሚገኘው ሆቴል በምችለው አቅም





ሁሉ ሮጥኩኝ። በጠባብ መተላለፊያ በኩል አልፌ በትንሽ አጥር ዘለልኩኝና ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ ዚግዛግ እየሮጥኩ አሳዳጆቼን አመለጥኳቸው። አንድ ቦታ ላይ ደርሼ ወደ ኋላዬ ስመለከት እስከዚያ ድረስ እየተከተሉኝ እንደ ሆነ በማየቴ ቤተ ክርስቲያኑን አልፌ ወደ ቀኝ በመታጠፍ ሽሜ ወደሚኖርበት ግቢ ገባሁ። መጠለያ አገኛለሁ ብዬ አሰቤ የነበረበት ቅርብ ቦታ የሽሜ ቤት ሲሆን፣ እኔም እያስተናገድኩት የነበረው ነገር የዳበረ ምሥጢራዊ ቅንብር ነበር።

በዚያው ቀን፣ ከኢሕአፓ የሆነ አንድ ወጣት ሰው ሽሜን ለመግደል በተልዕኮ ላይ ነበረና ሽሜን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ አገኘው። ወጣቱ መጀመሪያ ላይ ሰላምታ ሲሰጠው ምንም ያልጠረጠረው ሽሜ እንደዚያው ሲመልስለት፣ በዚያው ቅጽበት ወጣቱ ሰው ሽጉጡን አውጥቶ ተኮሰና እንደ ገደለው በመገመት ወዲያውኑ ሮጠ። ድንገተኛው አጋጣሚ በፈጠረው ድንጋጤ ምክንያት ሽሜ በአቅራቢያው ባለው ቦይ ውስጥ ሲወድቅ እግሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት። ሽሜ አጋጣሚው ከተፈጠረበት ቦታ ጥቂት ደቂቃዎችን ያክል ርቆ ወደሚገኘው ቤቱ ተወስዶ በወጌሻ እየታከመ ሳለ እቤቱ ደረስኩ። በወቅቱ እኔ ወደ ግቢው ስገባ የማልረሳው የእናቱ ሞቅ ያለ የአቅፋት አቀባበል ይደረግልኝ እንጂ፣ በአዳኞቼ ወጥመድ ውስጥ እየገባሁ እንደ ሆነ አላወቅሁም ነበር።

አሳዳጆቼ ተከትለውኝ ኖሮ ወዲያውኑ ሽሜ ወደሚገኝበት ክፍል ገቡና ትከሻዬን ያዙኝ። ሽሜ ቀና ብሎ ተመልክቶ፣ "ምን እያደረጋችሁ ነው?" ሲላቸው፣ "ጠላታችን ስለ ሆነ እርምጃ ልንወስድበት እንፈልጋለን" ሲሉ መለሱለት። "ሥራ አጣችሁ እንዴ?" በማለት መለሰላቸውና፣ "የተሳሳተ ሰው ላይ ዒላማ አድርጋችኋል - እርሱ የእኛ ነው" ብሎ ጨመረላቸው። ታድ የሚባለው ከአሳዳጆቼ አንደኛው፣ "የእኛ?" ሲል ጥያቄውን ሲያስተጋባ፣ ሽሜ ጫን ብሎ "አዎን!" አለው። ያን ጊዜ ታድ፣ "እጃችንን በእጃችን ልንቆርጠው ነበር" ሲል ተናገረና፣ 'ይቅርታ' በማለት ትቶን ሄደ። ከሽሜ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ስቆይ፣ በሁለታችንም ላይ የደረሰውን ተነጋግረን እንግዳ በሆኑት ክስተቶች ሁለታችንም ተደነቅን። ሁለት ጓደኛማቾች በተመሳሳይ ቀን ልንሞት የነበረ ቢሆንም፣ የዚያችን ቀን ጨምሮ ሁለት ጊዜ ሽሜ ሕይወቴን ስላተረፈልኝ ሁሌም አመሰግነዋለሁ። በእነዚያ ዘመናት እንደ እርሱ ያለ ሰው ማግኘት እምብዛም እንዳይቻል የሚያደርጉት ነገሮች እርሱ ቀጥተኛ፣ የውሳኔ ሰው፣ ሐቀኛ እና አንድ

ጠቃሚ ጥራት ጭምር የነበረው ሰው መሆኑ ነበር - እስጊ የሚሆነውን ነገር ለመድፈር አለመፍራቱ።

የእውነት ለመናገር፣ የእርሱ የፖለቲካ አቋም ምንም ቢሆን ምን፣ እርሱ እንዲሞት ጨርሶ አልፈልግም ነበር። በዚያን ጊዜ ሽሜ አቋሙን ቀይሮ ብርቱ የመኢሶን ፓርቲ ደጋፊ መሆኑ ግልጽ የሆነልኝ ሲሆን፣ ማርክሲዝምን ጠልቆ ያነበበ እና አብላልቶ የሚያስብ በመሆኑ ደግሞ በእኩዮቹ እና በጥቅሉ በመኢሶን ክበብ ውስጥ ባሉት ሰዎች ዘንድ በጥሩ ሁኔታ የተከበረ ሰው ለመሆን እንዳበቃውም ተገንዝቤያለሁ። ይሁን እንጂ፣ ለፓርቲው ካለው ንድፈ-ሐሳባዊ ድጋፍ በስተቀር፣ የቀረውን የሕይወት ዘመኑን የፓርቲ ወይም የመንግሥት መደቦችን ሳይቀበል፣ ደግሞም በየትኛውም ወንጀል-ነክ ተግባራት ውስጥ ሳይሳተፍ ሙያተኛ አስተማሪ በመሆን ሕይወቱን ያሳለፈ ሰው ሆነ። እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ማርክሲስት መሆኑን ቢደስትበትም፣ ዕድሎችን መጠቀም ከሚፈልጉት አንዳንድ የጋራ ጓደኞቻችን በተለየ ትልቅ ተጽዕኖ-ፈጣሪ ሰው የመሆን ቅንጣት ታክል መሻት ግን አልነበረውም። ለምሳሌ፣ ታዋቂ የነበረው የሕዝብ ድርጅት[38] አባል አልነበረም፣ ደግሞም ሰዎችን በመወንጀል ወይም የሰዎችን ስም በየትኛውም መንገድ በማጥፋት ተሳትፎ አድርጎ አያውቅም። እንደውም እርሱ የመኢሶን ፓርቲ አባል መሆኑን እንኳን አንዳንድ ጊዜ እስከጠራጠር ድረስ፣ ሽሜ በትውፊት ከሚታወቀው በላይ 'ትልቅ ሰው' ከሚባሉት ሰዎች ጎራ የሚመደብ ነው። ሽሜ በእጁ የሚታወቅበት 'ፊትላ' ብለው ሐረሪዎቹ እርሱን የሚጠሩበት ተጫዋችነቱ መገለጫው ሲሆን፣ አንዳንዴ ደግሞ ከዚያ ተቃራኒ ሆኖ የሚገኝበት ባሕርይ ነበረው።

ጥፋቶቹ ተብለው ከሚገለጹት ነገሮች መካከል አልኮል የሚጠጣበት ያልተቋረጠ ልማዱ እና በሚበሳጭበት ጊዜ ከሰዎች ጋር የሚኖረውን ንግግር ማቀብ የማይችል መሆኑ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ። በሰከረ ጊዜ ሁሉ ስለ ኢሕአፓ እና ተከታዮቹ መጥፎ ቃላትን የሚናገር ሲሆን፣ እንደውም አንዳንድ ጊዜ የኢሕአፓን ተልዕኮ በሚያበሳጫቸው መልኩ ሲተረጉመው፣ "የልጆች ጦርነት" በማለት በድፍረት ይነግራቸዋል። እንዲሁም ደግሞ የፖለቲካ ብስለታቸው እንደ ጥላ እንደ ሆነ ገልጾ፣ ስለ ፓርቲው አባላት የሚያንቋሽሹ ንግግሮችን ጨምሮ ይናገራል። ፖለቲካዊ ንቃተ ሕሊናቸውን "ሊፋፋ ንቃተ ሕሊና" በማለት የማርክሲስት እውቀታቸው ከቆዳ አልፎ ያልዘለቀ ወይም





ከእርሱ እይታ አንጻር ቀጭን እንደ ሆነ በአደባባይ ይናገራል። የፖለቲካዊ እስተሳሰቦቻቸው ምንጭ በዋናነት ድብቅ በሆኑ የተከለከሉ የምሥጢር ጽሑፎች ላይ የተመሠረተ እንደ ሆነ በመጠቆም፣ ጠንካራ የጥንታዊ ማርክሲዝም እና ሌኒኒዝም ንባቦች ላይ ባለመመሥረቱ ይሳለቅባቸዋል። በእርግጥ፣ ከሚያንቋሽሻቸው ንግግሩ የተነሣ ከእነርሱ ጋር የመረረ ጠላትነትን እትርፎ እንደ ነበረ አይካድም።

አንድ ወቅት ላይ እኔን ከሽሜ በአካላዊ ሁኔታ በሚያርቀኝ መልኩ ሰፈር ቀየረና ጣፋጭ የሆነውን የጋራ በርጫ ጊዜ፣ በአንድ ላይ መጠጣታችንንም አቆምን። እርስ በርስ መንገድ ላይ ለመገናኘት አጋጣሚ ስናገኝ በፖለቲካዊ አኳኋን ሰላምታ እሰጠውና፣ ፈገግታ ተለዋውጠን እንለያያለን። በትንንሽ ነገር ተጨቃጭቀን አናውቅም፣ ወይም አጨቃጫቂ ሙግቶችንም አድርገን አናውቅም። አንድ ጊዜ ከኢሕአፓ ይልቅ የመኢሶንን አቋም እንደሚወድ ሲያምንልኝ ጊዜ፣ ወደዚያ አቋም ቀስ በቀስ እንደ ተወሰደ እኔም አውቄ ነበርና ወደዚያ አቋም መምጣቱ ባያስደስተኝም፣ አቋሙን ግን አከበርኩለት። ነገር ግን እርሱን ካጀቡት ጋር የፓርቲውን ንድፈ-ሐሳባዊ እና ፖለቲካዊ አቋም ለማሻሻል እስቦበት ራሱን እንደሚሰጥ ምንም ጥርጥር አልነበረውም። ይሁን እንጂ፣ እስከዚያ ድረስ የእርሱን ጓደኝነት ትልቅ ዋጋ ስለምሰጠው፣ ከስንት ጊዜ አንዴ በአልኮል ጫና ውስጥ በቂ ብርታት አሰባስቤ በሌሊት ሄጄ እጎበኘዋለሁ። ወደ ቦታው በድንገት እደርስና በሩን አንኳኩቼ ስሜን ሳሳውቅ በሩን ይከፍትልኝና ወደ ክፍሉ ያስገባኛል። እንዳየሁት፣ "አንተ ፋሺሽት፣ አንተ አውሬ፣ ፋሺሽታዊ አገዛዝ ለመደገፍ መረጥክ፤" ብዬ በምጮኽበት ጊዜ በፈገግታና መደነቅ ፊት "ጥበበ ከልብሽ ነው?" እያለ አስቀምጦኝ ለጥቂት ጊዜ ተሳስቀንና ተጨዋውተን እንለያያለን። በዚያ መንገድ ያጣሁትን የተወደደውን ግንኙነታችንን ከጥሩው ጓደኛዬ ጋር በድብቅ አድሳለሁ እንጂ፣ መቼም እንደ ጠላት አይቼው አላውቅም ነበር፣ እርሱም እኔን እንደዛው። ስለዚህም፣ ከእነዚያ ግራ የሚያጋቡ እና አደገኛ ዘመናት አልፎ የተሻገረ አንዳች ዓይነት መግባባት የነበረን ይመስለኛል። በጥልቀት ደረጃ እርስ በርስ ተግባብተን ስለ ነበር፣ በኢሕአፓ ሰፈር ከነበሩት አብዛኞቹ ጓደኞቼ ይልቅ ሽሜ የበለጠ እውነተኛ እና ሐቀኛ ሰው መሆኑን እመሰክርለታለሁ።

ይህንን የታሪኬን ክፍል ከመዝጋቴ በፊት፣ ሐረርን ሳልዘጋጅ እና

ባልተጠበቀ መልኩ ትቼ እንድወጣ ያስገደደኝን አንድ ያልተጠበቀ ውጤት ያመጣ አደገኛ አጋጣሚን ልተርክ። ይሄኛው አጋጣሚ በድንገት በቁጥጥር ሥር ከዋለው ጓደኛዬ ከካሱ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ አንድ ጊዜ መንግሥት ጅጅጋን ከሶማሌዎች ያስለቀቀበትን ድል ምክንያት በማድረግ ትልቅ ሕዝባዊ በዓል አወጀ። አዋጁ የመጣው በቀበሌዎች በኩል እንደ መሆኑ፣ በእነዚያ ዘመናት አስቸጋሪ የእስርም ሆነ ሕዝባዊ መብቶችን የማጣት ትሩፋቶች ስለ ነበሩት፣ ማንም ሰው እንዲህ ያሉ በዓላትን አይቀርም። የክብረ-በዓሉ ሥነ-ሥርዓት የሚካሄደው በስታዲየም በመሆኑ፣ ካሱ እና እኔ ወደ ቦታው በአንድነት ሄድን። በትልቅ ሕዝብ መካከል፣ የደህንነት መኮንኖች በድንገት ካሱን በመንጠቅ ከስታዲየም ይዘውት ሲወጡ በጣም አስደነገጠኝ። ከእርሱ ጋር አብሬ እኖር ስለ ነበር የእኔ የሆኑትን ሁሉ በእርሱ ቤት ውስጥ አድርጌያለሁ። የመንግሥት ካድሬዎች እስከዚያ ነጥብ ድረስ እንኳን ቀድሞ ከነበረኝ ተራማጅ ፖለቲከኛነቴ የተነሣ እና በዋናነት የኢሕአፓ አባላት እና መኮንኖች ከሆኑ ጓደኞች ጋር ስለምቀራረብ እንደ አደገኛ ሰው አድርገው መገመታቸው አይቀርም።

ሕይወቴን አደጋ ላይ መጣል አልፈለግሁም ነበርና በዚያችው ሌሊት ከተማዋን ጥዬ ለመውጣት ወሰንኩኝ። ፔጆ ታክሲ ይዤ ወደ ድሬዳዋ ሄድኩኝና በዚያው ሌሊት በባቡር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት አክስቴ ወደምትኖርበት ንፋስ ስልክ ተጠለልኩኝ። ለተወሰነ ጊዜ ያክል በዚያ ራሴን ካስጠጋሁ በኋላ፣ ወደ ዩኒቨርስቲ ሄጄ ትምህርቴን እንድቀጥል በማመልከት ከዓመታት የቀወሰ መዋለል በኋላ ትምህርት ቤት ገባሁ። የሁለተኛ ዓመት የታሪክ ዋና ትምህርት ዓይነትን የሚያጠና ተማሪ አድርገው ሲቀበሉኝ፣ ከስድስት ዓመታት በፊት ትቼው የነበረውን ያንኑ ቦታ ተመልሼ ገባሁበት፣ ምን ዓይነት ብክነት ነው!

## እንደገና ወደ ዩኒቨርስቲ

በ1970ዎቹ መጨረሻ፣ በፖለቲካ ትግል ውስጥ ከሁለቱም የፖለቲካ ጎን በተፈጠሩ ድንገተኛ ሁኔታዎች የተጎዱት ሁሉ እርስ በርስ በጥርጣሬ ይተያዩ ስለ ነበር፣ በዩኒቨርስቲው ውስጥ የምሁራን ድባብ ከተለመደው በታች ዝምተኛ ሆኖ ቆየ። ድባቡ ሊፈጠሩ በሚችሉ አስፈሪ ሁኔታዎች የተሞላ በመሆኑ፣ ተስፋ-ቢስ





በሆነው የአብዮቱ ዓመታት ውስጥ ማን ምን እንደሚያደርግ መናገር ከባድ ነበር። የቅድመ-አብዮታዊው ጓድነት፣ እምነት እና የንቃተ-ሕሊና ባህል በዘመኑ ሊገኙ ባለመቻላቸው፣ በአጭር ቋንቋ አንድ ነገር ለዘላለም ጠፍቶ እንደ ነበር ማንኛውም ሰው በቀላሉ መናገር ይችላል። "የድሮ ጥበቃዎች" ተባብለን የምንጠራራቸውን የድሮ ጓደኞቼን በዩኒቨርስቲው ውስጥ ሳገኛቸው ከእኔ ቀድሞ ወደ ዩኒቨርስቲው ተመልሶ የገባውና በግቢው ማደሪያዎች ውስጥ ክፍል ያገኘው አንደኛው ጓደኛዬ እጅግ ተደስቶ ተቀበለኝ፣ ኋላ ላይም፣ የክፍል ጓደኛው ሆንኩኝ።

ከዚሁ ወዳጄ ጋር በባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ምን ምን ነገሮች እንደ ተከሰቱ ልምምዶቻችንን ተካፈልን። ከእርሱ ጋር የመጨረሻውን *በርጫ* እና የመጨረሻውን ኮስታራ የፖለቲካ ውይይት ያደረግሁት ከየዘመቻ ጣቢያዎቻችን ከወጣን በኋላ በቤቱ ተገናኝተን ነበረና፣ ከዘመቻ ከለቀቅሁበት ጊዜ ጀምሮ እያንዳንዱን የሕይወቴን ታሪክ ነግሬው እንደ ነበር ትዝ ይለኛል። ይህም ሲሆን፣ ከሆሳዕና የመጣና ሳሚ የሚባል አንድ የተጋጋለ ወጣት አብዮተኛ በዚያ ውይይት ላይ ከእኛ ጋር ይጫወት እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ሁላችንም ውጤቱ የሚጠይቀውን የትኛውንም ከፍያ ለመክፈል የተዘጋጀንና በሚካሄደው አብዮት ላይ ለመሳተፍ በጉጉት ወደ ፊት የምንመለከት የተቃጠሉ ተራማጆች ነበርን።

ከቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ተሞክሮው የገዛ ታሪኩን ካካፈለኝ በኋላ፣ በአዲስ የማርክሲስት እና ሌኒኒስት ድርጅት ውስጥ ይሳተፍ እንደ ነበረ ምንም ሳይደብቅ ነገረኝ። ከዚያም ለጥቆ፣ አብዮታዊ ትግሉን ለመቀጠል ምርጥ የሆነው መንገድ ማሌሪድ[39] ተብሎ የሚጠራውን ተራማጅ ድርጅት መቀላቀል እንደ ሆነ አጽንዖት ሰጥቶበት ነገረኝ። ስለ ድርጅቱ ብዙም ባላውቅም፣ ከወታደራዊው መንግሥት ጋር የሚሠሩ በተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች የተቋቋመው በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች በመኖራቸው፣ በመንግሥት ምሪት ሥር የሚንቀሳቀስ ማርክሲስት ቡድን እንደ ሆነ ገመትኩ።[40] ከእነርሱ



የጀሊንት ሙከራ ግራ ሲጋባ

እንደኛው ማሌሪድ ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ ሆኜ የነገረኝን ሰማሁት፣ ነገር ግን ምን ማድረግ እንዳለብኝ ለማወቅ ተቸገርኩ። ፖለቲካ ስለ ሰለቸኝ፣ ላመልጠው ወደ ዩኒቨርስቲ ስመጣ እፈልግ የነበረው መላው ነገር ሐረር ውስጥ ከተበከለው የፖለቲካ ድባብ እና ተከትሎትም ከመጣው መታፈን እፎይታ ማግኘት የምችልበትን አስተማማኝ መንግሥት ሰማይ ነበር። ወደ ዩኒቨርስቲ ያመጣኝ ነገር ራሴን ላስጠልልበት እና እድሜዬን ላራዝምበት መፈለጌ እንጂ፣ ትምህርቴን መቀጠሉ ግንባር ቀደም ምክንያቴ አልነበረም።

ከምላ ጎደል በየቀኑ ሰጠጣ፣ ሌሊት ድረስ ቆይቼ ወደ ቤቴ ስገባ፣ እና *‹‹ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል››* እንደሚባለው፣ በስካር ሁኔታዬ ውስጥ መራራ ስሜቶቼንና ተስፋ መቁረጦቼን ስናገር ማህ የምለው ጓደኛዬ አስተውሏል። አንዳንድ ጊዜ እርሱ ላይ ጥቂት የምጠራጠርባቸው አመለካከቶች ቢኖረኝም፣ ማህ ጥሩ ጓደኛዬ የሆነ ሰው እና ጓደኝነታችንም በተወሰነ መልኩ በኃላፊው ጊዜ ውስጥ ባለፍንባቸው በተለያዩ የፖለቲካ ዱካዎች የተከበበ ነበር። በመንገዱ ዳርቻ ላይ ገና እንዳልደረስንና ሥራውን እና ለአብዮቱ ሲሉ የሞቱ ሰዎች የነበራቸውን ሕልም ልንፈጽም የምንችልበት አዳዲስ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ እየነገረኝ፣ እርሱ አባል የሆነበትን ቡድን እንድቀላቀል የምር አስብበት ዘንድ ደጋግሞ መጠየቁን ተያይዞታል። የእኔ አስቀያሚ ሁኔታ እና በጥቅሉ አስጠሊታ የሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ገጠመኞች እንዳሉ ሆነው፣ ኃይል-አልባ የሆንኩ እና ለእርሱም መገፋፋት የምሸነፍ እንዳልሆንኩ መስሎ ተሰማኝ። ለዚህም ምክንያቱ ይሄ ትክክለኛው ጊዜ ስላልሆነ፣ ሰዎች እርስ በርስ ስለማይተማመኑ፣ እንዲሁም ጓደኛማቾች እርስ በርስ እየተፋለሙ ስለሚገዳደሉ ጭምር ነበር። ለዚህ እንደ ማስረጃ ከአንድ ቤተሰብ የተገኙ ሁለት ወንድማማቾች ሁለት የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ይዘው የሽሙጥ የመደብ ጦርነት በመካከላቸው ሲቀሰቀስ ጦርነቱ በታናሽየው መገደል እንዳበቃ መጥቀስ ይቻላል፤ ይሄስ ምን ይባላል?[41]

አንድ ወቅት ላይ ማህ አነስተኛ የጥናት ክበብ ዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ እንድንጀምር ጠየቀኝና የተወሰኑ ተማሪዎችን እንድመለምል ኃላፊነት ሰጠኝ። "ያንን የማደርገው እንዴት ነው፣ ደግሞስ ማንን ነው የምመለምለው፣ በምንስ የፖለቲካ ባንዲራ?" ከሚሉት ጥያቄዎች ጋር ኃላፊነቱን በማቅማማት





ተቀበልኩኝ። የኢትዮጵያ ፖለቲካ በጣም አጥፊ የነበረው፣ ለእርስ በርስ መወነጃጀሉም አስተዋጽዖ ያደረገው ትውልዱ በስፋቱ ልክ እርስ በርስ ይተዋወቅ ስለ ነበር ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ስሜ ላይ አሉታዊ መጠሪያ የተለጠፈ ቢሆንም፣ ከየትኛውም የጥርጣሬ ጥላ በላይ የእኔን ሐቀኝነት የሚያውቁ ጓደኞች እንዲሁም ደግሞ አንዳች ዓይነት ጥርጣሬን የሚጥሉብኝ ሌሎች ሰዎችም ጭምር ነበሩ። ተልዕኳቸው ምን እንደሚሆን ግልጽ ያላደረግሁላቸውን አዳዲስ የፖለቲካ የቡድን አባላት ወጥቶ መመልመሉ ለእኔ ከባድ ሥራ ስለ ሆነብኝ የገዛ ራሴን ስልት ነደፍኩኝ። በንጹሐኑ ላይ አስጊ እና ከግብረ-ገብም አኳያ በራሱ ተቀባይነት የሌለው የማጥመድ ሙከራ ቢመስልብኝም፣ የማውቃቸውን እና የማምናቸውን ከፖለቲካ አኳያ በመካከል ያሉትንና ንጹሐኑን መረጥኩኝ። ያን ጊዜ የማኅበረሰብ ጥናት ተማሪ የነበረውን የሐረር ልጅ እና ሲበዛ እውነተኛ የሆነውን ሰው ጴጥሮስን ሞከርኩት።[42] የጥናቱን ቡድን እንዲቀላቀል እርሱን ስጋብዘው በተለመደው የሚረብሸው አሳሳቁ ከሳቀብኝ በኋላ፣ "እየቀለድክ ነው? የራሴን ሕይወት ልደሰትበት፣ እጠጣ ዘንድ ብቻዬን ተወኝ" ሲል ፍርጥ አድርጎ በቀጥታ መለሰልኝ። የልምሸ የሚባል ሰውን ቀረብኩኝ፣ እርሱም፣ "ጥቤ፣ እባክሽ ተይኝ፤ ትምህርቴን ልማርበት" ሲል ያለማፈር መለሰልኝ። በሙከራዎቼ ላይ በከፊል ልብ ነበርኩኝና ብዙም በማይገርም መልኩ ልምምዱ ሳይሳካ ቀረ። ያልተሳካውን ጥረቴን ለማህ ከመንገር ይልቅ የአዲስ አበባው አዲሱ ቡቴ ሆቴል ወደ ሆነልኝና ኮባ ሰፈር ወደሚባለው የአካባቢው መጠጥ ቤት ሄድኩና ሙትት ብዬ እስክሰክር ድረስ ሰክሬ ወደ ክፍሌ ተመለስኩኝ።[43] ሁሉንም ለእርሱ ያለኝን ቅያሜና የጥርጣሬ ስሜት በመግለጥ የመጣልኝን ሁሉ የጥላቻ ቃላት በማህ ላይ ስተፋ አደርኩኝ። ማህ ገር ሰው በመሆኑ፣ በእርሱ ላይ እነዚያን ሁሉ መጥፎ ነገሮች ስናገር ቃል እንኳን አልመለሰልኝም። በሚቀጥለው ቀን፣ እስከነቃ ድረስ በክፍሉ ውስጥ ቆየና ስነቃ ረጋ ብሎ ቁም ነገር ያለበት ውይይት ከእኔ ጋር ማድረግ እንደሚፈልግ ነገረኝ። በቀደመው ሌሊት ስሜቶቼ እንዴት እንደ ተጎዱ የእውነቱን ነገረኝና ገና ከጅማሬው ኃላፊነቱን አልቀበልም ማለት እችል እንደ ነበረ ገለጸልኝ። ራሴን ከአብዮቱ እንዳላርቅና ሕይወቴንም በአልኮልና ተስፋ መቁረጥ እንዳላባክን በማሰብ ኃላፊነቱንም የሰጠኝ ለገዛ ራሴ ጥቅም እንደ ነበረ ግልጽ አደረገልኝ። በዚህን ጊዜ፣ ይቅርታ ጠይቄው ስለ ኃላፊነቱ አመሰገንኩት።

እኔም ለእርሱ የልቤን ገለጥኩለትና እነዚህን ነገሮች በመገፋፋት እንደ ፈጸምኳቸውና ከዚህ በኋላ ፖለቲካ ላያነሣብኝ ግልጽ አደረግሁለት። ያ ሁኔታ ነገሩን ሁሉ አረገበው - ፖለቲካም ከዚያ በኋላ በመካከላችን አልነበረም።

ትምህርቴ ላይ ለማተኮር እና ሁልጊዜም እንደምመኘው ጎበዝ ተማሪ ለመሆን እውነተኛ ፍላጎት ቢኖረኝም፣ ያለመታደል ሆነና፣ ብዙ በመዋለሌ ያ ሳይሳካልኝ ቀረ። በዚህ መልኩ ጠፍተው የቀሩ በርካታ ጓደኞች ቢኖሩኝም፣ ግቢውን ተቆጣጥሮት የነበረው ፊተኛው ነውጠኛ የባህልና የፖለቲካ ድባብ ግን ከዚያ በኋላ አልነበረም። የትምህርት ክፍለ-ጊዜያት አሰልቺ መስለው በሚታዩበት በዚያን ዘመን ግቢውን ለአንድም ሆነ ለሌላ ምክንያት የተቀላቀሉ አዲስ ሂደትን በማይቀበሉ ተራማጅ ተማሪዎች ዘንድ ጥርጣሬዎች እና በርከት ያሉ ማስፈራሪያዎች ነበሩ። የማጣት እና የሽንፈት ስሜት እንደ ነበረ ግልጽ በሆነ መልኩ የደህንነት ሰዎች መጥተው ከተማሪዎች ማደሪያዎች እንኳን ሳይቀር ተማሪዎችን ይዘው የሚሄዱባቸው ጊዜያት አጋጥመዋል። መንግሥት ራሱን አደላድሎ መሠረተ፣ ደግሞም በመቶዎችና በሺዎች የሚቈጠሩት ሰዎች የተሰዉለት አገራዊ ጉዳይ ተሸርሽሮ የጠፋ መሰለ። ስለዚህም፣ ተስፋ መቁረጥ እና ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ የመጣ ከባድ ሁኔታ ተቆጣጠረኝና ኮባ ሰፈርን በማዘወትርበት የጠጪነት ልማዴ ገፋሁበት። ብዙም ሳይቆይ፣ ኮባ ሰፈር አዲሱን ሂደት ለማንቀበለው ሰዎች ስለ ሁኔታችን የምናለቅስበት እና ስላለፉት ጥሩ ትዝታዎቻችን የምናወሳበት ታዋቂ ቦታ ሆነ። ለእኔ፣ የጭፈራ ቤቶች እና የመጠጥ ቤቶች በትንሽ ቦታ ላይ ልክ ሐረር ውስጥ እንደ ነበረው የቦቴ ሆቴል ሌላኛው ቤርሙዳ ትሪያንግል ሆነብኝ። ይህ ሁኔታ "ሠንሰለታማ መስተጋብር፣ አንድ አስጨናቂ ስሕተት እና መመለስ የማይችል!" የሚል ርእስ ያለውን ፊልም ያስታውሰኛል። ኮባ ሰፈርን ያዘወትር የነበረውና ከጥንቱ አብዮት አባላት አንደኛው ቦታውን 'አሲስ' ሲል ጠራው። በፖለቲካ ለደከማቸውና በአእምሯቸውም ለጠወለጉ ጓዶች ማረፊያ የሆነ የምድረ በዳ "ማረፊያ" ስፍራ ማለቱ ነበር።

የትምህርት ክፍለ-ጊዜያትን በቋሚነት አለመገኘቴ፣ የትምህርት ቤት መገልገያ ዕቃዎቼን የምይዘው አልፎ አልፎ መሆኑ ሳያንስ እኔ እና የቀድሞ ዐማፂያን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲጋራ ማጨስ ጀመርን። ማኅበራዊነት ውስጥ ጥሩ ጸባይ የነበራቸው የቀድሞዎቹ ሰዎች ሲጠፉ እና ቀውሱ ከቁጥጥር





ውጪ ሲሆን አስተማሪዎቻችን ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? በእርግጥ፣ ከእኛ ጋር በክፍል ውስጥ የሚያጨሱ አንዳንድ መምህራን ነበሩ። አንዷን ሲጋራ አብሬያቸው የምካፈላቸው ሞግ፣ ዜድ እና ካት የተባሉ ጓደኞች ስለ ነበሩኝ፣ የኮድ መነጋገሪያችን የሆነችውን 'ወጋሁ' የምትለውን ቃል በመጠቀም ሲጋራ የማጨስ ተራችንን እንቀባበልበታለን።

በወታደራዊው አገዛዝ ተወርሶ አብዮት ቅርስ ትምህርት ቤት የተባለውና ቀደም ሲል በሱዳን ኢንቴሪየር ሚሺን (ኤስ ኣይ ኤም) እየተመራ የክርስቲያን ልጃገረዶች አካዳሚ (ጂሲኤ) ይባል የነበረው ትምህርት ቤት ውስጥ በትርፍ ሰዓት ስለማስተምር፣ ገንዘብ ለእኔ ችግር አልነበረም። ከዚህም በተጨማሪ፣ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ተማሪዎች ጋር ከተወዳደርኩኝ በኋላ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ውስጥ ጊዜያዊ ጋዜጠኛ የምሆንበትን ሥራ አገኘሁ። አሟልቶ ማስተማሩ እና ጊዜያዊ ጋዜጠኛ መሆኑ በርካታ ገንዘብ አመጣልኝ፣ ነገር ግን ያ ማለት በትምህርቴ ላይ ያነሰ ትኩረት እና ያነሰ የክፍል መገኘት ማለት ስለ ነበር፣ ውጤቴ እንዲጎዳ የራሱን አስተዋጽዖ አደረገ።

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢቴቪ) የነበረኝ ልምምድ የሚያስደስት ሲሆን፣ ይኸው ዓይነቱ ጋዜጠኝነት ፈጽሞ የተለየ ለሆነ የልምድ ዓለም የተጋለጥኩ እንድሆን አደረገኝ። የእኔን ዓለም ለሁሉም የሕይወት ጎዳናዎች በከፈተ በርካታ ጉዳዮች ላይ ሪፖርተር ሆኜ ብሠራም፣ የጊዜውን መንግሥት ከውስጥም ሆነ ከውጭ ስለምጠላው፣ በውስጤ ያለ አንዳች ነገር ደግሞ የገዛ ራሴን እምነት እየጣስኩ እንደ ሆነ ይነግረኝ ጀመር። የመንግሥቱን አገዛዝ ወድጄው አላውቅም ነበርና በዋናነት የመንግሥትን አጀንዳ ለሚያገለግል የቴሌቪዥን ጣቢያ መሥራት የተወሰነ ዓይነት ከዳተኝነት መስሎ ተሰማኝ። ተሞክሮው ዓይንን የሚያበራ፣ ክፍያውም መልካም ሆኖ ሳለ፣ ነገር ግን የማለቅስበት ግዙፍ የግብረ-ገብ ሸክም ነበረኝ። በአገሪቱ ብቸኛ የቴሌቪዥን ጣቢያ ውስጥ መሥራቱ የሚያመጣልኝ የውሸት ኩራት እና የሕዝብ ታዋቂነት ቢኖርም፣ መወሰን ባልቻለ ማንነት ውስጥ ሆኜ ስሠራ ቆየሁ። በዚህኛው የሕይወቴ ደረጃ ላይ ምናልባት በ20ዎቹ እድሜ ክልል ውስጥ መሆኔ አያጠራጥርም።

ለቴሌቪዥን ዘጋቢነት ስሠራ የምችለውን ያክል ገሃዳዊ እውነታውን ለማስቀመጥ የበኩሌን ባደርግም፣ ነገር ግን በእነዚያ ዘመናት ገሃዳዊ መሆን

በጣም አስቸጋሪ ነበር። በእነዚያ ዘመናት ታዋቂ የፖለቲካ ቁልፍ ሰው የነበረው እርገጤ ተናጋሪ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ ስለ አንድ ክስተት ዘገባ አቀርባለሁ። ስለዚህም፣ ንግግሩን አሳጥርና አንደኛው የቲቪ. ሐተታ ላይ በሌላ ጉዳይ ዙሪያ ትኩረት አደርጋለሁ። በሚቀጥለው ቀን ወደ ጣቢያው ሲመጣ በምሽቱ ዜና እወጃ ላይ ንግግሩ የቀረበበትን ሁኔታ በተመለከተ ቅሬታ ያቀርባል። በዚህም ምክንያት፣ አንድ ግለሰብ በእነዚያ ዘመናት ባለው ሥልጣን ልክ ዶለተብኝ።

አንድ ወቅት ላይ ጤፍ ለመሸጥ ከጎጃም ስለ መጡ ገበሬዎች ዘገባ እንድሠራ ኃላፊነት ተሰጠኝ። ገበሬዎቹ ከጎጃም በከፍተኛ ዋጋ ይዘውት የመጡትን እህል እንዲሸጡ በአካባቢው ደላሎች ተታለሉ። የእኔ ተግባር የእነዚህን "ስግብግብ ነጋዴዎች" ሥራ መመርመርና በምሽቱ ዜና ላይ ዘገባዬን ማቅረብ ስለ ነበር፣ ቃለ ምልልሱን ለማድረግ የካሜራ መሣሪያዎችን ይዤ ወጣሁ። ታስረው ባሉበት ቀበሌ ጣቢያ ስደርስ ግን ያየሁት ነገር ግራ አጋባኝ። በሥራ ዝርዝሩ ላይ እንደተገለጸው ሰዎቹ ስግብግብ ነጋዴዎች ሳይሆኑ፣ ተራ ድሃ ገበሬዎች ሆነው አገኘኋቸው። ቃለ መጠይቁን ካደረግሁላቸው በኋላ፣ ስለ ዋጋ ገደቡ የሚያውቁት ነገር እንደሌለና በደላላው እንደ ተታለሉ መረጃውን አሰባሰብኩኝ። ስለዚህም ሆነ ብለው ያደረጉት ወንጀል እንዳለ ተደርጎ ሊከሰሱ ስለማይገባ በዘገባዬ ላይ እነርሱን 'ስግብግብ ነጋዴዎች' ብዬ እንዳልገልጻቸው መረጥኩኝ። ነገር ግን ስግብግብ ግለሰቦች የሚለውንና እንደዛም ሆኖ ትክክለኛ ስያሜ ያልሆነውን፣ ሆኖም ከመጀመሪያው መጠሪያ ይልቅ ቀለል የሚለውን ተጠቀምኩኝ። በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ያደረጋቸውን የሁኔታውን እይታ የማቅረብን እና የቀበሌ መኮንኖቹን ክስ አቅርቤ ፍርዱን ለሕዝብ የመተውን ብልህ ስልታዊ አቀራረብ ተጠቀምኩ። በመጨረሻው ትንታኔ ላይ ከበደለኝነት የሕሊና ወቀሳ ማምለጥ ሳልችል በመቅረቴ አስደሳች በሆነው የጋዜጠኝነት መስክ ውስጥ የመቆየት እና ከውስጥ ውጥረቴ የተነሣ እቁሞ በመውጣት ፍላጎቴ ትግሎች ውስጥ ገባሁ። በመጨረሻም፣ ሥራውን መልቀቁ ግዴታ የሚሆንበት ጊዜ መጣ።

ክፍል በቋሚነት የምገኝና በርትቼ የማጠና ብሆን የበለጠ ልሠራ ብችልም፣ ከሌሎች ጋር ሲተያይ ያንን ዓመት ጥሩ በሆነ ውጤት አጠናቀቅሁ። በተለይ ከቅኝ ግዛት ጋር በተያያዘ ያለውን የአፍሪካ ታሪክ ትምህርት 'ኤፍ' (ወዳቂ ነጥብ) አገኘሁ። እንግሊዛዊውን አስተማሪ ብዙ ጊዜ ለመልካም ምክንያቶች፣





አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እርሱን ለማንቋሸሽና ለማበሳጨት ስል የተግዳሮት ጥያቄዎችን አነሣበታለሁ። ታሪክን የምገነዘብበትን አኳኋን የማርክሲስት አተያዬ እስከዚያ ነጥብ ድረስ ተጽዕኖ አድርጎበት ስለ ነበር ሁልጊዜም ቢሆን ጥያቄዎቼን የማቀርበው ከማርክሲስት እይታ አንጻር በመሆኑ፣ አስተማሪው ያንን አካሄድ መቼም ወድዶት አያውቅም። እርሱ ጥሩ እና ብዙ የሚያውቅ አስተማሪ ነበርና ጉዳዩን ከእውነታው አንጻር ለማቅረብ በሚሞክርበት ጊዜ፣ እኔ ደግሞ ሐሳባዊ እንደ መሆኔ ከእኔ እይታ አኳያ የአፍሪካን ታሪክ እያበላሸው እንደ ሆነ አሰብኩ። ነገር ግን፣ በአፍሪካ ታሪክ ላይ የፕሮፌሰሩን ያክል በጥሩ ሁኔታ ያነበብኩኝ እና በሙያተኝነት የሠለጠንኩኝ እንዳልሆንኩ ምንም ጥርጥር አልነበረውም።

ከእርሱ ጋር በወሰድኩት ሌላኛው ትምህርት ዓይነት፣ በሥነ-ቁፋሮ የ 'ኤ' ውጤት የሰጠኝ ሆኖ ሳለ በአፍሪካ ታሪክ ትምህርት ላይ ግን እንደ ቅጣት ውሳኔ አድርጎ፣ ሆነ ብሎ የ 'ኤፍ' ውጤት እንደ ሰጠኝ በማወቁ ወደ ቢሮው ሄድኩና የቀሩትን ውጤቶቼን አሳይቼው፣ "አንተ ዘረኛ፣ አድሃሪ" እና የመሳሰሉትን መጥፎ ቃላት በመጠቀም ጮህኩበት። ውጤቴን ሊያሻሽል ቃል እየገባልኝ ሊያረጋጋኝ ሲሞክር እኔ ግን ተቃወምኩት። እንደውም፣ ክፍሉን ለቅቄ ስወጣ፣ "የአንተ የቀደሙ አባቶች ሕዝባችንን እና ምድራችንን ቅኝ ገዙ፣ አሁን ደግሞ አንተ አእምሯችንን ቅኝ ልትገዛ ትፈልጋለህ። ያንን በእኔ ላይ ማድረግ አትችልም። እኔ አብዮተኛ ነኝ። እኔ የአብዮታዊ ትውልድ አካል ነኝ። አልገዛልህም። የእኔን 'ኤፍ' ውጤት ለእምነቶቼ የከፈልኩት መሥዋዕትነት መገለጫ እና የክብር ባንዲራዬ ሆኖ በመዝገቤ ላይ እንዲቆይልኝ እፈልጋለሁ።" አልኩት። ያን ጊዜ ውጭ ድረስ ተከትሎኝ ወጣና እንድረጋጋና ነገሩን ከእርሱ ጋር እንድፈታ ሲለምነኝ፣ በውሳኔዬ የማልነቃነቅ ሆኜ ላልሸነፍ ጸናሁ። እንደውም "አንተን ስምህ በትክክል ይገልጽሃል። እንደ ስምህ (ዊልድ) = ያልተገራ/መረን ነህ" ብዬ ሰደብኩት (ስሙ "ዊልዲንግ" ወይም ያን የመሰለ ነበር)። ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ፣ በድል አድራጊነት ስሜት ከሕንጻው ወጣሁ።

ከረጅም ጊዜ በኋላ፣ ስድስት ኪሎ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ በሚገኝ አንድ ቡና ቤት ውስጥ ከጓደኛው ጋር ቢራ እየጠጣ ሳለ ይህንኑ አስተማሪዬን አገኘሁት። "እርሱ ለአእምሮዬ የማያቋርጥ ስጋት ነው" በሚል ንግግር ከጓደኛው ጋር አስተዋወቀኝ። ያች አስተያየት ትልቅ ሙገሳ ነበረችና ማንነቴን አሳበጠችው።

እንደ ሙሌ፣ ካሱ እና ሌሎችም ከአርጌው ትውልድ የሆኑ ጓደኞቼ የትምህርት ክፍሉን (ዲፓርትመንቱን) ተቀላቀሉና በክፍል ውስጥ ያለው ድባብ በመቀየሩ የሦስተኛ ዓመት ትምህርቴ ከሁለተኛው ዓመት ይልቅ የተሻለ ሆነ። ነገር ግን እነዚህን የድሮ ጓደኞቼን ማግኘቱ የበለጠ አጥፊ ነገር ይዞ መጣ። አብዛኞቻችን በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የተማርንና ገንዘብ የምናገኝ የነበርን ሲሆን፣ ሁላችንም ከኃላፊው ጊዜ እንደ መታሰር እና ጓደኞችን ማጣት ዓይነት ጠባሳ የቀረልን ተስፋ ቆራጮች ነበርን። በዚህም ሆነ በዚያ፣ ስለ ራሳችንም ሆነ በዙሪያችን ስላሉት ነገሮች እፎይ ብለን የተረጋጋን አልነበርንም። በጣም ወደምናዘወትርበትና መወያየት ከፈለግን፣ ለመሰባሰብ፣ ለመደሰት፣ እና ከሁሉም በላይ ከተስፋፋብን የጭንቀት እና 'ቤት-አልባነት' ስሜት ለማምለጥ ቦታ ወደሚሰጠን ወደ ኮባ ሰፈር እንሄዳለን። ሙሌ ስሜቶቹን "አጠቃላዩ መሰበር" ሲል የገለጸው ሲሆን፣ ይህም ካልሆነ በሐረሪዎቹ ቋንቋ 'ድብርት' ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ከሞላ ጎደል በእያንዳንዱ ሌሊት ልንገዛው የምንችለውን ያክል ቢራ በመጠጣት ስሜቶቻችንን እዚያው እንገልጻለን።

ምንም እንኳን እኔ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አገልግሎት እና ከማስተማር የማገኛቸው ወርሐዊ ደመወዞች ቢኖሩኝም፣ ዕለታዊ በሆነ መልኩ ኮባ ሰፈር መጠጥ ቤቶችን የማዳርስ በመሆኔ ባዶ እጄን የምቀርባቸው ጊዜያት ነበሩኝ። ስለዚህም በዱቤ ወይም የእጅ ሰዓቴን ለቡና ቤት ባለቤቶቹ በማስያዝ ቀስ ብዬ እንደምከፍል ቃል እየገባሁ እጠጣለሁ። የቡና ቤቶቹ ባለቤቶች ያምኑኛል፤ ሌላው ቢቀር የቲቪ ሰው ነኝ እኮ። በሚቀጥለው ቀን እንደ ጂሚ ያሉ ከድሬዳዋ የመጣው የአጎቴ ልጅ ጓደኛ ጋ እሄድና ሰዓቴን ለማስመለስ ስል ገንዘብ እበደረዋለሁ። ያን ጊዜ የሂሳብ አያያዝ (አካውንቲንግ) ተማሪ የነበረው ጂሚ የመጣው ከነጋዴ ቤተሰብ ስለ ነበረ ሲበዛ ቸር ሰው ሆኖልኛል።

በመጀመሪያ ዓመት ትምህርቴ ላይ ከነበሩት ውጤቶች ጋር ሲወዳደር ፈጽሞ የማይበቃ ይሁን እንጂ፣ የ3ኛ ዓመት ትምህርቴን ከሌሎቹ ጋር ሲተያይ አሳማኝ በሆነ ውጤት አጠናቀቅሁኝ። 4ኛ ዓመት ተማሪ ስሆን የመጨረሻው ዓመት የትምህርት ቆይታዬ እንደ መሆኑ፣ ትምህርቴ ላይ ብዙ ትኩረት ለማድረግ እና በጥሩ ሁኔታ ለመጨረስ ፈለግሁ። ሆኖም ግን፣ ራስን መግዛትን እና ለትምህርት የተሰጠሁ መሆንን አጥቼ ስለ ነበረ በድጋሚ በውሳኔዬ





የመጽናት ችሎታ አልነበረኝም። እነዚህ ሁለት ነገሮችም በኃላፊው ሕይወቴ ውስጥ ከነበረው መበጥበጥ የተነሣ ያጣኋቸው ጥራቶቼ ናቸው። ወሰኜ ከነበረው ይልቅ እንደውም የበለጠ እንዝህላል ሆንኩኝ፣ ደግሞም ከሌላው በበለጠ የክፍል ትምህርት መቅረት ጀመርኩኝ። በጣም ያዝንልኝ በነበረው አማካሪዬ፣ በጋሽ አምበርብር ወሳኝ ጣልቃ-ገብነት ባይሆን ኖሮ የባለ አራት ክሬዲት ሰዓት ትምህርትን መመዝገብ የረሳሁበት ጊዜ ተፈጥሮ ያውቃል። ጋሽ አምበርብር እንዝህላል ባሕርዬን በማወቁ፣ "ለመመረቅ አንድ ሌላ ዓመት እዚህ ማሳለፍ ትፈልጋለህ?" ሲል አንድ ወቅት ላይ ጠይቆኝ ያውቃል። በዚያን ጊዜ ከስምንት ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ ከዩኒቨርስቲ አሠራር ርቄ ስለ ነበር ብቅ ጥልቅ የምልበት ሁኔታ ውስጥ ነበርኩኝ። ምንም ያላሳሰበኝ መሆኔን በማስተዋሉ እንደ ማስታወሻ እንዲሆነኝ "ለግዴለሽነትህ አንድ ቀን ዋጋ ትከፍላለህ" ሲል ከባድ ንግግሩን ጨመረልኝ። ተስፋ በመቁረጥ ቢሮውን ለቅቄ እንድሄድ የማይፈልግ ደግ ሰው ነበረና፣ "ጥበበ ለአንተ ግሩም መጪ ጊዜን አያለሁ" በሚሉ የማበረታቻ ቃላት እንዴት እንደ ደገፈኝ አስታውሳለሁ። ከልቡ እንደ ተናገረው ያወቅሁት ንግግሩ ያን ጊዜ ትርጉም ኖሮት ባይገባኝም፣ ለዚያ ትልቅ አነጋገር ክብደት የሰጠሁት ግን በጣም በችግር ነበር። በእርሱ እገዛ፣ ያንን ለመመረቅ እንድወስደው ይፈለግብኝ የነበረውን የትምህርት ዓይነት መመዝገብ ቻልኩኝ።

ርእስ ለመምረጥ በጣም በመቸግሬ አውራ የሆነውን መጣጥፍ ለመጻፍ ለረጅም ጊዜ አቅማማሁ። አውራ የሆነውን የመመረቂያ የጽሑፍ የቤት ሥራዬን ከአብዮቱ ጋር የተያያዘ ርእስ ኖሮት ለመሥራት ብፈልግም አብዮቱ ግን በቦንብ የጋየ ያክል ስለ ሆነ፣ በአስተማሪዎች ኅብረት ንቅናቄ ታሪክ እና ለኢትዮጵያ አብዮት ያበረከተው ነገር ላይ መጣጥፌን ለመጻፍ ፈለግሁኝ። ነገር ግን "ስለዚያ ምን እጽፋለሁ፣ ደግሞስ ምን ያክል ገሃዳዊ እሆናለሁ፣ ውጤቱስ? በጥቅሉ አብዮቱ የጠፋ ጉዳይ ሆኗል?" የሚሉ ጥያቄዎች አስቆሙኝ።

ለታሪክ የትምህርት ክፍል አብዛኞቹን የመንፈቅ የወረቀት የቤት ሥራዎቼን እጽፍ የነበረው ከማርክሲስታዊ አስተሳሰቤና ፍላጎቴ ጋር አብሮ በመሄድ ትርጉም የሚሰጡትን ርእሶች በማንሣት ነበር። ለምሳሌ፣ ለሁሉም የዓለም ታሪክ ክፍለ-ትምህርቶቼ፣ ወረቀቶቼን የጻፍኩት በዓለማአቀፍ የሠራተኛ መደብ እንቅስቃሴዎች ላይ ሲሆን፣ ለመጨረሻው መጣጥፌ ከእነዚህ የጥናት ወረቀቶች

መካከል ርእሶችን ለመምረጥ ሞከርኩኝ። ነገር ግን በጣም ጥቅል ሐሳቦች መስለው ስለ ቀረቡ፣ የትምህርት ዓመቱ ሊያልቅ ሲል አውራ ወረቀት ሥራዬን የአፍሪካ ውስጥ ግንባር ቀደም ተጋድሎ ላይ ለመሥራት ወሰንኩኝ። የወረቀት ሥራዬ ርእስ፣ *"ፕራይመሪ ሪዚስታንስ ኢን አፍሪካ፡- ኤ ቲዮረቲካል አፕሮች"* (ግንባር ቀደም ተጋድሎ በአፍሪካ፡- ንድፈ-ሐሳባዊ አቀራረብ) የሚል ሆነና እንደ ዕድል ሆኖ፣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለ ጨረስኩት ለአማካሪዬ በጊዜው አስረከብኩት። የሚከነክነው ነገር፣ አሁን ላይ ብርቱ ደጋፊዬ የሆነውና አንድ ጊዜ ግን ተጨቃጭቄው የነበረው እንግሊዛዊ የታሪክ ምሁር አማካሪዬ መሆኑ ነበር። በመጨረሻም፣ 1971 ዓ.ም ላይ ተመረቅሁኝ።

ከምርቃት ከብረ-በዓሌ ጋር ተያይዞ ያለውን የሚያስደምም ታሪኬን እዚህ ጋ ላካፍል። ምረቃ ሰሞን ላይ፣ ካጠናቀቅሁበት የትምህርት መምሪያ (ፋከሊቲ) የማዕረግ ልብስ ተሰጥቶኝ ቁምሳጥን ውስጥ እንዳስቀመጥኩት ትኩረት ሳልሰጠው ቀርቼ ተረሳ። ለምረቃ ከብረ-በዓሉ አርፍጄ እስከነቃ ድረስ ከምርቃት ቀኔ በፊት ባለው የዋዜማ ሌሊት በጣም አስከስክር ጠጥቼ ነበር። በዚያ ዕለት ከእንቅልፌ እንደ ነቃሁ ከራስ ምታት ሕመም ጋር ሆኜ ከብረ-በዓሉ ወደሚደረግበት የራስ



*ከኮ/ል መንግሥቱ እጅ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ስቀበል*

መኮንን አዳራሽ አመራሁ። አማካሪዬ ጋሽ አምበርብር አዳራሹ ውስጥ እየፈለገኝ ባለበት ሰዓት ላይ በበሩ በኩል አምርቼ *መቀመጫ ስላገኘሁ ተመቻችቼ* ተቀመጥኩኝ። በመጨረሻ አየኝና እኔ የማላውቀው ለነበረ ልዩ ሁኔታ ተጠብቆ በቆየው የፊት *መቀመጫ* ወስዶ አስቀመጠኝ። የእያንዳንዱ ክፍል ምርጥ ተማሪዎች ብቻ ተመርጠው ዲፕሎማዎችን ከያኔው የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት ኮ/ል መንግሥቱ ኃይለማርያም እጅ እንደሚቀበሉና የፊት ወንበሮቹም የተጠበቁት ለእነዚህ ተማሪዎች መሆኑን ኋላ ላይ አወቅሁ። በእኔ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከነበሩት ሦስቱ ተማሪዎች ካሉና አሰናቀን ጨምሮ አንደኛው ባለማዕረግ እኔ ነበርኩኝ። ወደ ፊት *መቀመጫ* የወሰደኝ አማካሪዬ "ዛሬን እንኳን ቁም ነገር አታደርግም?" ሲል ገሥጾኝ የምረቃ ከብረ-በዓሉ በደማቅ ሥነ-ሥርዓት





ተጀመረ፣ ተመራቂዎችም ዲፕሎማዎቻቸውን ተራ በተራ ወሰዱ። የእኔ ተራ ሲደርስ ተነሥቼ ወረፋዬን ያዝኩኝና ብቻ አስፈሪ በሆነ ሁኔታ እዚያ ሊሆን ፈጽሞ አይገባውም ነበር ብዬ ወደማስበው ሰው - ወደ ፕሬዘዳንቱ-መራመድ ጀመርኩኝ። በዚህ ጊዜ ስሜቱ ለምን እንደ ተቆጣጠረኝ ባላውቅም፣ ምናለ ከሥልጣን ያወረድናቸው ንጉሡ በዚያ በነበሩ ብዬ አሰብኩኝ። የሆነው ሆኖ፣ ምንም የፍንደቃ ስሜት ሳይኖረኝ ዲፕሎማውን ከኮሎኔል መንግሥቱ እጅ ተቀበልኩ። ምንም እንኳን ከታዳሚዎች ዘንድ ጥቂት የጭብጨባ ድጋፍ ብሰማም፣ በጭራሽ ደስተኛ አልነበርኩም።

በዚያ የምረቃ ቀን ስድስት ኪሎ አካባቢ ከሚገኙ ጠጅ ቤቶች በአንደኛው ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር ጠጅ እየጠጣን ሌሊቱን አጋመስነው። የዕለቱ አርእስተ ዜና የምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ በሆነበት መልኩ ቲቪው ሲከፈት ምን እንደ ታየ ገምቱ! አብሬው እሠራ የነበረውና በደንብ ያውቀኝ የነበረው የቲቪ ሠራተኛ በቲቪው መስኮት ፊት ለፊት አመጣኝ። ጠጅ ቤት ከነበሩት ጓደኞቼ "ጥቤ! ጥቤ!" የሚል ጩኸት ስሰማ፣ ዘገባውን ተከታተልንና ለቅንጣትም ታክል ግድ ሳይኖረኝ በሁኔታው ተሳስቀን ነገሩ አለፈ። አልፈበት ከነበረው ነገር ጋር እና የእኔ ትውልድ ከፍሎት ከነበረው ነገር ጋር መዝኜው ስለ ቀለለብኝ፣ ምርቃቴን አስመልክቶ ከብረ-በዓል አላደረግሁም። አብዮቱ ተመሰቃቅሎ በነበረበት እና የአብዛኞቻችን ከፍተኛ የመነሣሣት ስሜት አቅጣጫውን ስቶ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ ለእኔ የግል ስኬት የሚባል ነገር አልነበረም። በቀይም ሆነ በነጩ ሽብር አስቀያሚ ድራማ ምክንያት ሕይወታቸው በመነጠቁ፣ ለበዓሉ መድረስ ያልቻሉ ነገር ግን የበለጠ ይገባቸው የነበሩ አያሌ ብሩህ ተማሪዎች ነበሩ።

ከምርቃት በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዳስተምር ተመደብኩኝ። የታሪክ ትምህርት ክፍሉ ከነበረኝ ውጤት አኳያ እና ልምዴንም ከግምት በማስገባት እንደ ምሩቅ ረዳት አስተማሪ እንዲመድበኝ እየጠበቅሁኝ ነበር። ከዚያ ይልቅ፣ ትምህርት ክፍሉ በመንግሥት ግፊት የዩኒቨርስቲ ኃላፊዎች ባስጀመሩት የባለ ሦስት ዓመት መርሐ-ግብር የተመረቁትን ሌሎቹን አዳዲስ ተመራቂዎች ለዚሁ ሥራ ወሰዷቸው። ከትምህርት ክፍሉ የተመረቅነው አብዛኞቻችን አዲስ ነገር ለመቀበል የማንችል፣ ችግር ፈጣሪ ማርክሲስቶች ተደርገን ስለ ተቆጠርን፣ እኔና እኩዮቼ ቀስ በቀስ ገለል ተደረግን። ይሄ ነገር ከእኛ በፊት ባሉት በበርካቶች ላይም የተከናወነ ነገር በመሆኑ ምንም

አይደንቅም። ለዚህ መጠቀስ ያለበት ጥሩ ምሳሌ ብሩህ ተማሪ የነበረ ቢሆንም፣ በትምህርት ክፍሉ ውስጥ እንደ ሠራተኛ እንኳን ሊመለመል ዕድል የተነፈገው እስኔ ነው።[44]

ስለዚህም፣ የትምህርት ሚኒስቴርን መቀላቀልና ሐረር ውስጥ የማስተማር ሥራን መጀመሩ የእኔ ምርጫ አልነበረም። በቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት በኩል ወደ ዩኒቨርስቲ ገብቼ ቢሆን ኖሮ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለማስተማር ግዴታ ይጥልብኝ ነበር። ከሞላ ጎደል ለሁለት ዓመት ያክል ሐረር ውስጥ ባለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያስተማርኩኝ በአለማያ ኮሌጅ ደግሞ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ሳስተምር ቆየሁ። ወደ ሐረር መመለሱ ጫት ወደምቅምበት እና ወደምጠጣበት የድሮ ሕይወት ዘይቤ መመለስ ስለ ነበረ፣ ስሕተት ለመሆኑ አያጠራጥርም። ዲግሪዬን ከያዝኩኝ በኋላ እንኳን ይሄ ነው የሚባል ቋሚ የባሕርይ ለውጥ አልነበረኝም። ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ሐረር ሊያስፈራሩኝ ሞክረው የነበረበት እና ስሜ የጠፋበትን አስጨናቂ ልምምድ ያሳለፍኩበት ቦታ ስለ ነበር፣ ምናልባት ወደ ተለየ ቦታ መሄድ ይኖርብኛል።

በአንደኛው ጥሩ ማለዳ ላይ ሩሲያ ውስጥ ወታደራዊ ሥልጠና ወስዶ ገና መመለሱ የነበረው ተከሴ በእኔ የሕይወት ዘይቤ ላይ የነበረውን ስጋት ለመግለጥ ሲል ብቻ በማለዳ ሊጐበኘኝ መምጣቱ ትዝ ይለኛል። ሁልጊዜ እንደምጠጣ እንዲሁም የማይወዳቸውን ዓይነት የሕይወት ዘይቤ በሚመሩ ሰዎች እንደ ተከበብኩኝ በማስተዋሉ፣ ከእኔ ይጠብቅ የነበረው ይሄንን እንዳልነበረ በግልጽነት ነገረኝ። የተሞላውን ወታደራዊ የድርጊት መመሪያ በእኔ ላይ ለመጫን እየሞከረ ነው እንጂ ብዬ እስካሰብ ድረስ ስለ እኔ ግድ ብሎት የነበረ ወዳጅ ይሁን እንጂ፣ እያስቸገረኝ ያለውን አባዜ በጥልቀት ያስተዋለ አይመስልም። እኔም ብሆን የእርሱን ጥልቅ አመለካከት ከቁብ የቆጠርኩ አይመስለኝም። የኋላ ኋላ ግን ምን ማለቱ እንደ ነበረ ለመረዳት ረጅም ጊዜ መውሰዴ ብቻ ሳይሆን፣ ደግሞም ምክሩን ተግባራዊ ለማድረግ ምንም አለማድረጌ ለዚህ ማስረጃ ነው።

ሐረር ውስጥ የነበረኝ ሕይወት ጥሩ የመሻሻል ሂደትን በሕይወት ውስጥ እንዳደርግ አንጂ፣ ሐረር ውስጥ ተጐሳቍሎ እንዳይቀር የእውነታቸውን ይፈልጉ በነበሩ ጥሩ ጓደኞቼ እርዳታ በጥሩ ሁኔታ አበቃ። አዲስ አበባ ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ውስጥ የሚሠሩ በተወሰነ መልኩ በጥብቅ የማገኛቸው





ጓደኞች የነበሩኝ ሲሆን፣ እነርሱም በከፍተኛ ትምህርት ዙሪያ የሚወጡ የሥራ ዕድሎችን በወጡ ቍጥር ያስታውቁኛል። ከሐረር የሆነው የእኔ ጥሩ ጓደኛ ዜድ፣ በከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን በአንዳች የከፍተኛ ብቃት ደረጃ ይሠራ የነበረ የሥነ-ልቦና (ሳይኮሎጂ) ትምህርት ምሩቅ ነበር። በዚህም መሠረት፣ አሥመራ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የታሪክ ምሁር እንደሚፈልግ ዜድ አስታወቀኝና ወዲያውኑ እንዳመለከት ሲመክረኝ፣ አዲስ አበባ ድረስ ሄጄ ለሥራ ቦታው በማመልከት ቃለ መጠይቅ አደረግሁኝ። ሁሉ ነገር ጥሩ ሆኖ ስላለቀ፣ ከትምህርት ሚኒስቴር የመልቀቂያ ደብዳቤ እስካቀረብኩኝ ድረስ ሥራው እንደሚሰጠኝ ተነገረኝ። ሆኖም ግን፣ የመልቀቂያውን ሰነድ ከትምህርት ሚኒስቴር ለማግኘት ያላሰለሰ ጥረት አድርጌ ሳይሳካልኝ ስለ ቀረ፣ በጣም ተበሳጭቼ ወደ ሐረር ሄድኩኝ።

ይኸው ዩኒቨርስቲ በቀጣዩ ጊዜ ሌላ ማስታወቂያ ሲያወጣ ለትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት ብርቱ የሆነ ልመና ላደርግ ወሰንኩኝ። ያን ጊዜ በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ቋሚ ተጠሪ የሚለውን ጠቃሚ ቢሮ ይዞ ወደ ነበረው ሁሴን ቢሮ ሄድኩኝ። በፊቱ የእውነቴን አልቅሼ በቁምነገር መለቀቄን ይፋ እንዲያደርግ ለመንኩት። ውጤቶቼን አሳይቼው አሥመራ ዩኒቨርስቲ የማስተማር ዕድል ሲሰጠኝ ይህ ሁለተኛው ጊዜ መሆኑን ነገርኩትና በዚህ ጊዜ ይህንን የማይገኝ ዕድል ማጣት እንደማልችል ወተወትኩኝ። ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መሐይምነትን ከማጥፋት ዘመቻ ጋር በተያያዘ ለሚረቀቅ መርሐ-ግብር እንደ አስተባባሪ ሆኜ ልዛወር እንደ ሆነ ጠቀም ሲያደርገኝ፣ ለፈጸመልኝ ውለታ አመሰግኜው፣ ከዚያ ይልቅ ወደ አሥመራ ዩኒቨርስቲ መዛወሩን እንደምመርጥ የእውነቴን ነገርኩት። ቢያቅማማም በመጨረሻ ግን ሊለቀኝ በመስማማቱ፣ ስለ ተረዳኝ እና ስለ ጉልህ ጣልቃ ገብነቱ ሁልጊዜም አመሰግነዋለሁ። ለልመናዬ አይሆንም ብሎኝ ቢሆን ኖሮ ሕይወቴ ምን ዓይነት የጉዞ ዱካ ይኖረው እንደ ነበረ አላውቅም።

## በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ማስተማር እና ተዛማጅ ተሞክሮዎች

መልቀቂያውን በእጄ እንደ ያዝኩኝ፣ ሐረር ውስጥ ከነበረኝ የማስተማር ሥራ በይፋ ለቀቅሁኝና የአሥመራ ዩኒቨርስቲ ፋክሊቲን በ1975 ዓ.ም ተቀላቀልኩኝ። በአሥመራ ዩኒቨርስቲ የነበረኝ ተሞክሮ ከሕይወት ዘመኔ

ቆይታዎች ሁሉ እጅግ የሚማርከው የሕይወት ገጽታ ሆነልኝ። መልካሙ ሕልም ወደ መፈጸም የመጣበት ስለ ነበር፣ ኃላፊ ጊዜዬን ወደ ኋላ ልጥል እና ወደ አዲስ ሕይወት ልሻገር ሞከርኩኝ። ለዚህም ተግባራዊነት ከጥልቅ ፍቅር እና ራስን መስጠት ጋር ለማስተማር ሞከርኩኝና በሥራ ባልደረቦቼም ሆነ በተማሪዎቼ ዘንድ ጥሩ ስም ማግኘት ጀመርኩኝ። ነገር ግን የመጠጣት ልማዴን እስከዚህ ዘመን ድረስ አላቆምኩም ነበር። በሕይወቴ እሉ ከምላቸው ምርጥ ጓደኞች አንዱ የሆነልኝን አቤን፣ ጦሚቴን እና ሌሎችንም ዓይነት አዳዲስ ጓደኞች አፈራሁ፣ ሐረር ውስጥ ከእኔ ጋር በአንድ ዓይነት እስር ቤት ታስሮ የነበረውን ተስፍንም አገኘሁት። ያጋጣሚ ነገር፣ አሥመራ ውስጥ በመንግሥት ባለቤትነት ሥር የነበረ የኢንዱስትሪ ተቋምን በሥራ አስኪያጅነት ያገለግል የነበረውንም ቴህን አገኘሁት። ሕይወትን እንደገና በምጀምርበት ጊዜ በአዲስ ጓደኞች መከበቤ ትልቅ ደስታ ሰጠኝ።

አሥመራ ፈተናዎች የሞሉባቸው ቡና ቤቶች ያሉባት የምትሰብ ከተማ ስትሆን፣ *ኮምፒሽታቶ* እና *ሲክሬቶ* ቡና ቤቶች ልክ እንደ *ኮባ ሰፈር* ያሉ አዲሶቹ መጥፊያዎቼ (ቤርሙዳ ትራያንግል) ሆኑ። አሥመራ ውስጥ ቢያንስ እንደ ዩኒቨርስቲ መምህር ተደላድዬ እቀመጣለሁ፣ የኃላፊ ጊዜ የመጠጥ ልማዶቼን ወዲያ እተዋለሁ፣ ደግሞም የተረጋጋ ሕይወት እመሠርታለሁ ብዬ አስብ ስለ ነበር፣ ሕይወቴ በዚያ ወደ ተሻለ ነገር ይለወጣል የሚል ግምት ነበረኝ። ያለመታደል ሆኖ ግን፣ ያ የቁም ቅዠት ብቻ ሆኖ ቀረ።

በአሥመራ የነበረው ሕይወት የራሱ የሆኑ ገደቦችን የያዘ ሲሆን፣ እርሱም የጦርነት ቀጣና የነበረ በመሆኑ፣ ከመሃል አገር ለመጣነው መመሳሰል አለመቻላችንን ያካትታል። ለዚህም ምክንያቱ ኤርትራውያን ነዋሪዎች በወታደራዊው መንግሥት ኤርትራዊ ላልሆነ ለማንኛውም ሰው ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገቡ በመደረጋቸው ነው። እስከዚያም ጊዜ ድረስ ገና ወጣቶች ስለ ነበርን፣ ወደ ማኅበረሰቡ መግባት እና ለጋ የነበረውን ሕይወት ማጣጣም እየፈለግን የፖለቲካ ዐውዱ ግን ያ ይሆን ዘንድ ሳይፈቅድልን ቀረ። ከመሐል አገር የሆኑ ሰዎች የውጭ አገር ዝርያዎች እንደ ሆንን አድርገው በቅኝ ግዛት መልክ ይዘውናል። በእርግጥ፣ የንግድ ትስስር እናደርጋቸው የነበሩ በተለይ ከሙስሊሞቹ ዘንድ የሆነ የነጋዴው መደብ አንዳንድ ጓደኞች ነበሩን። እንደኛው ጥሩ ጓደኞችን ያላገቡ የፋከልቲ አባላት ይኖሩበት የነበረው ናኩራ አፓርታማ





አጠገብ ሱቅ የነበራቸው አቦ ተከሌ ሲሆኑ፣ አቦ ተከሌ ከሱቃቸው የትኛውንም ነገር በዱቤ እንድንወስድ እስኪፈቅዱልን ድረስ በጣም ያመኑን ሰው ነበሩ። በተለይ በሳምንት ማብቂያዎች ላይ ድግሶችን በምናቅድ ጊዜ ጥሬ ገንዘብ ሳንከፍል በዱቤ ቢራዎችን እንገዛለን።

አሥመራ በነበርኩኝ ጊዜ የደረሰብኝን የሚያስደነግጥ ሁኔታ ለማካፈል እፈልጋለሁ። አንድ ሌሊት ላይ ጓደኛዬ ጦሚቲ እና እኔ *ቼርቺ* ወደ ተባለና *አባ ሻወል* ተብሎ በሚታወቅ የተጨናነቀ የመኖሪያ አካባቢ ኮረብታ ጫፍ ላይ ወደ ተከፈተ አዲስ የመዝናኛ ማዕከል ሄድን። የተማሪዎችን የፈተና ወረቀቶች እናርም ከነበረበት አሰልቺ ረጅም ቀን እረፍት ለመውሰድ ነበር የፈለግነው። ወደ አፓርታማችን ስንመለስ፣ በምንመለስበት ቀጭን ጎዳና ላይ ጓደኛዬ እና እኔ እየተጓዝን በነበረበት ፊት ለፊት እና ቀርበን በንብ ፈነዳ። ጓደኛዬ በደመነፍስ ወደ ቀኝ ሲሮጥ እኔ ደግሞ ቀጥታውን ወደ ፊቴ ሮጥኩኝ። ይሁን እንጂ፣ የጓደኛዬን የት መሆን እያጣራሁ ወደ ኋላ እና ወደ ፊት እየተመለከትኩኝ ሳለሁ፣ በድንገት በርካታ የደህንነት ሰዎች ከአካባቢው ቡና ቤት መጡና ከበቡኝ። ጓደኛዬን ፍለጋ ወደ ኋላና ፊት መመልከቴ የተሳሳተ ምልክት ስለ ሰጣቸው፣ አንዳንዶቹ ሽጉጦቻቸውን አውጥተው እጆቻቸውን ወደ ራሴ በመጠቆም ደገኑብኝ። በጦር ቀጣና ውስጥ እየኖርኩ እንደ ሆነ እስኪመስል ድረስ ቦንቡን የወረወርኩት እኔ መስያቸው ይመቱኝ ጀመር። እኔ ተልዕኮ ላይ የነበርኩኝ የኤርትራ ሕዝቦች ነጻነት ግንባር (ኤሕነግ) አባል እንደ መሰልኳቸው ወዲያውኑ አስተዋልኩኝ። ላደርገው የመጣልኝ ምላሽ ለደህንነት ሠራተኞቹ የመታወቂያ ወረቀቴን በማሳየት ከመሃል አገር የመጣሁ የዩኒቨርስቲ መምህር መሆኔን እንዲያውቁልኝ ማድረግ ቢሆንም፣ አላመኑኝም ነበርና መደብደባቸውን ቀጠሉ። በመጨረሻም፣ ለሰዓታት ጥያቄ ወዳስተናገድኩበት ወደ አካባቢው ፖሊስ ጣቢያ ይዘውኝ ሄዱና ወንጀለኞች ወደ ሞሉበት እስር ቤት ጣሉኝ።

መጀመሪያ ላይ ያዘኑልኝ በሚመስሉ ወጣቶች ሰላምታ ከተሰጠኝ በኋላ፣ የሻማ ስጠን ተብዬ ገንዘብ ተጠየቅሁኝ። ለዚህ ጥያቄ ካልተባበራችሁ ውጤቱ አስጨናቂ ሊሆን ይችላል። በእስር ቤቶች ውስጥ ስለሚኖሩ የዝምድና ደንቦች በመጠኑ አውቅ ስለ ነበር፣ ጥያቄውን በመታዘዝ ራሱን የእስረኞች መሪ አድርጎ ለነበረው ሰው ገንዘብ ሰጠሁ። እስር ቤቱ ውስጥ ምንም ምግብም ሆነ የሚጠጣ ነገር ሳላገኝ ለሦስት ቀናት ያክል ቆየሁ። በእስር ቤቱ ውስጥ ያሉት ከሦስት

ቀናት በኋላ ሌላ እስር እና ግርፋትን ወደማይበት ሌላ ቦታ እንደምወሰድ ሲነግሩኝ ከማልቀስ በቀር ላደርገው የምችለው ምንም ነገር አልነበረም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳለሁ፣ የመታሰሬ ዜና የማኅበረሰብ ሳይንስ ዲን ወደ ነበረችው ሲስተር ማና ዘንድ ደረሰና ሲስተር ማና ወደ ፖሊስ ጣቢያው ዘንድ መጥታ እንድለቀቅ ጠየቀች። ከእስር ቤቱ አውጥተውኝ ዲኗ፣ ዋና መኮንን የነበረው ሰው እና ደደር ውስጥ የፖሊስ መኮንን የነበረው ኮሎኔል መስፍን ወደሚገኙበት ክፍል ተወሰድኩኝ። ኮሎኔሉ ታዋቂ ዐማፂ እንደ ነበርኩኝ ደህና አድርጎ ያውቅ ነበርና አደጋው በተከሰተ ሌሊት በቁጥጥር ሥር ያዋሉኝ የደህንነት ሰዎች የጻፉትን ሪፖርት አነበበልኝ። በነበረው የመጋነን ደረጃ እና "ነበልባል ያለው የተወሳሰበ ቦንብ" የመጣል ወንጀል በውሸት የተከሰስኩበት መንገድ አስደነቀኝ። ሪፖርቱ የቀረበው የዓይን-ምስክር እንዳቀረበው የምስክርነት ቃል ተደርጎ ስለ ነበረ፣ በኮሎኔሉ ፊት እያለቀስኩኝ፣ "ይህንን ወንጀል ለመፈጸም ብዬ ከአዲስ አበባ እዚህ ድረስ ለምን እመጣለሁ?" ስል ጠየቅሁት። እዚህ ያለሁት አስመራ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለማስተማር መንግሥት በመደበኝ መሠረት ነው ስል አስረዳሁ። ይህን ጊዜ፣ ዲን የነበረችው ሲስተር ማና፣ "የተጠነሰሰውን ወንጀል ጥበበ የፈጸመ ከሆነ፣ የገዛ ሕይወቴን እሰጣለሁ" በማለት ጣልቃ ገባች። ኮሎኔሉ ከዲኗ ጋር መጥቶ ከነበረው ጦሚቴ ጋር የፍንዳታውን ባሕርይ እንዳስረዳ ጠየቀኝ። ሁለታችንም ስንንገዛገዝና አለማወቃችንን ስናሳይ፣ ሳቀና የዩኒቨርስቲ መምህራን ሆነን ሳለ በነገሩ ላይ እውቀት በማጣታችን ገሠጸን። ከውስጤ ሆኜ የጠየቅሁት ጥያቄ፣ ወታደራዊ ሳይንስ ሳናጠና ይህንን እንዴት ልናውቅ ይጠበቅብናል የሚል ነበር። በጣም ባከሳኝ የሦስት ቀናት እስር ቤት ውስጥ ከቆየሁ በኋላ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ከእስር ቤት ተለቅቄ ወደ መኖሪያዬ ሄድኩ። መኮንኑ ባያምነኝና ሲስተር ማና ጣልቃ ባትገባ ኖሮ ምን እሆን ነበር ብዬ አሰብኩኝ። በወሳኙ ሰዓት ላይ ላደረገችልኝ ድጋፍ እና ዩኒቨርስቲው ውስጥ በእኔ ስለ ጣለችው ትልቅ እምነት ሲስተር ማናን መቼም አልረሳትም።

አስመራ ዩኒቨርስቲን ከተቀላቀልኩኝ ከአንድ ዓመት በኋላ፣ የድኅረ-ምረቃ ትምህርቴን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዳከናውን ዕድል ተሰጠኝ። በ1977 ዓ.ም በታሪክ ትምህርት ክፍል በሁለተኛ ዲግሪ (ኤምኤ) ተመዝግቤ ስገባ እንደ ትምህርቱ መርሐ-ግብር ጥቅል ሆኖ የዳሰሳ ትምህርቶችን ማስተማር ነበረብኝ። በትምህርት ክፍሉ እና አሁን ድረስ እንደ ቀድሞው ችግር ፈጣሪ እና ሊከሰት





የሚችል ስጋት አድርገው በሚያዩኝ በአንዳንድ የፋኩልቲው አባላት ላይ ደስ የማይል ስሜት እንዳደረብኝ ብዙም ሳልቆይ አስተዋልኩኝ። ለዚህም ከፊል የሆነው ምክንያት የእኔው ጥፋት ስለ ሆነ በባለፉት ዘመናት ጥላዎች ሥር አለፍኩኝ። በተለይ በአንድ አንጋፋ የታሪክ ምሁር ላይ ተደጋጋሚ የሆነ የጎሪጥ አስተያየቶችን ተመለከትኩ። በመጨረሻ ላይ ግን በቀደሙት ዘመናችን ላይ የመረዳትን ዕድል በሰጡን አንዳንድ አጓጊ አጋጣሚዎች ምክንያት ጥሩ ጓደኛማቾች ሆንን።

በሁለተኛ ዲግሪዬ ዙሪያ ምቾት አልተሰማኝም ነበርና ለማቆም ወሰንኩኝ። ነገር ግን፣ ትምህርት ክፍሉን እና በትምህርት ችሎታዬ እንድገፋ ዕድሉን የሰጡኝን ተቋም ለማሳመን የመጀመሪያውን መንፈቀ-ዓመት ጥሩ ውጤት ማምጣት እንዳለብኝ አሰብኩኝ። የመጀመሪያውን መንፈቀ-ዓመት ካጠናቀቅሁ በኋላ፣ ያኔ ዲን ለነበረችው ሲስተር ማና ጥያቄዬን ግልጽ አደረግሁላት። ስትመልስልኝም፣ "ተጋፈጠው፤ ያ እንዲሆንብህ አልፈቅድም። ለማቆም እና ለመመለስ ከወሰንክ የድኅረ-ምረቃ ትምህርትህን ለመማር ሌላ ዕድል እንደማይሰጥህ ልታውቀው ይገባል" ስትል በመጻፍ በጥያቄዬ አለመደሰቷን ገለጸችልኝ፤ ደግሞም በድኅረ-ምረቃ ሥራዬ እንድገፋበት መከረችኝ። ባቋርጥና ብመለስ፣ በዩኒቨርስቲው ውስጥ የነበረኝን ጥሩ ስም እንደሚያሳጣኝ ጭምር አስጠንቅቃኝ ደብዳቤውን ያበቃችው በእኔ ላይ ያላትን መተማመን በመግለጽ እና ጊዜያዊ ተግዳሮቶቹን መወጣትና መርሐ-ግብሩን ማጠናቀቅ እንዳለብኝ በማረጋገጥ ነበር። ምንም እንኳን ጥብቅ እና ርኅራኄ ያለበት ደብዳቤ ቢሆንም፣ ያን ያክል ቦታ ልሰጠው አልፈለግሁም። ደብዳቤው በመወሰንና ባለመወሰን አስቸጋሪ ቦታ ላይ ስላኖረኝ፣ ለተወሰነ ጊዜ በውስጤ ከተከራከርኩ በኋላ በመጨረሻ ማምለጫ አጣሁና ልገፋበት ወሰንኩኝ። መለስ ብዬ ሳስበው፣ ከሲስተር ማና ውትወታ የተነሣ የወሰድኩት ውሳኔ ልጸጸትበት ምንም ምክንያት የማላገኝበት ነገር ነው።

ያ በእንዲያ እንዳለ፣ እጅጌዬን ሰብስብ አድርጌ፣ ብርታቴን አሰባስቤ በትምህርቱ ላይ ትኩረት ለማድረግ የምችለውን ሁሉ ማድረግ ነበረብኝ። ምንም እንኳን ለትምህርት ክፍሉ እንደ 'ጠፋው ልጅ' ተደርጌ በአንጋፋ ፕሮፌሰሮቼ ኢታይ የነበረ ቢሆንም፣ በሁለተኛው መንፈቀ-ዓመት ላይ ጥሩ መሥራት ቻልኩኝ። ነገር ግን፣ በትምህርት ክፍሉ ውስጥ አንድ ያልተጠበቀ

አጋጣሚ ሁኔታዬን ለወጠው። የተካረረ ግንኙነት ከነበሩኝ ውስጥ አንደኛው የሆነው አንጋፋ ፕሮፌሰር እና እኔ በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ፈተና ቢሮ ውስጥ ለ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ክትትል እንድናደርግ ተመደብን። በሆነ መልኩ አንግዳ ነገሮች ተከስቱና በመካከላችን ተሥሎልን የነበረውን መስመር ተላልፈን አንዳችን ሌላችንን አሳፈርን። ለዚህ ክስተት በጣም ወሳኝ የሆኑትን አንዳንድ ዝርዝሮች ላቀርብ እፈልጋለሁ። አንጋፋ ፕሮፌሰሩ ክልላዊ የብሔራዊ ፈተና አስተባባሪ ሆኖ የተመደበበት ጣቢያ እኔም የተወሰኑ በከተማው ውስጥ ያሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንደኛው አስተባባሪ ሆኜ በተመደብኩበት በደብረ ማርቆስ ነበር። የፈተና ሰነዶቹን አስተማማኝ በሆነ የፖሊስ ጣቢያዎች በማድረስ ሥራ በዝቶበት ስለ ዋለ፣ የሆቴል ክፍል ለመያዝ ጊዜ ሳያገኝ ቀረ። እኔ ግን ከተማው ውስጥ በኤርትራውያን የንግድ ሰዎች ባለቤትነት ተይዞ የነበረ ጥሩ የተባለለት ሆቴል ውስጥ ክፍል ይዣለሁ። እስኔ እና እኔ በከተማው ጎዳናዎች ላይ እንዲሁ ያለ ሥራ እየዞርን ሳለ፣ በድንት አንጋፋውን ፕሮፌሰር የጫነችው ላንድሮቨር መኪና ቆማ ፕሮፌሰሩ የሆቴል ክፍል አሁን ድረስ እንዳላገኘ ሾፌሩ ነገረን። በዚህ ጊዜ፣ እስኔ ክፍሌን አስለቅቄ ፕሮፌሰሩ እንዲከራየው እንድፈቅድለት ስለ ጎተጎተኝ ምክሩን ተቀበልኩና ሐሳቡን አቀረብኩኝ። መጀመሪያ ላይ፣ ፕሮፌሰሩ ካቅማማ በኋላ ቆይቶ ግን ጓደኛዬና እኔ ቸክ ስላልን የያዝኩትን ክፍል ለመከራየት ተስማማ። በሚቀጥለው ቀን በዛው ሆቴል ሌላኛው ክፍል ውስጥ ለእኔ መኝታ ክፍል አገኘልኝና ያ አጋጣሚ በመካከላችን አዲስ የጓደኝነትን ዘመን ከፈተልን። ሁለተኛ ዲግሪዬን ለማጠናቀቅ እንዲሁም ለወደፊቱ የሥራ ሁኔታዬ የፕሮፌሰሩ ሚና በጣም ወሳኝ ጠቀሜታ ነበረው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች አለመግባባቶችን ለማጥራት እና ያልተፈቱ የግንኙነት እንቅፋቶችን ለማስወገድ እንዲያ ያሉ አጋጣሚዎች ያስፈልጓቸዋል።

ያንኑ ሆቴል በጋራ አሳለፍንበት፣ አብረን በላን እንዲሁም የከተማይቱን ቡና ቤቶች በጋራ ጎበኘናቸው። በሂደቱም፣ እንዳችን የሌላችንን ማንነት አወቅን፣ እዚያ የፈጠርነው ጥምረትም ለዘመናት ጸንቶ ዘለቀ። እንደውም እርሱ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን እንድጨርስ የሚያስፈልገውን ድጋፍ እና ማበረታቻ በመስጠት በትምህርት ክፍሉ ውስጥ በብርቱ ለእኔ በጣም የሚከራከርልኝ ሰው ሆነ። ተለዋዋጭ ግንኙነት የነበረን ቢሆንም፣ ደግሞም በኃላፊው ጊዜ ውስጥ





የአጋጣሚ አለመግባባት የነበረን ቢሆንም፣ ለእርሱ ያለኝ ምስጋና ግን ከልብ ነው። ከጥንቱ ጎራ ከሚመደበውና ሁሌም ጠበቃችን ሆኖ ከሚቆመው አንደኛው የሆነው ሼፍ ዋጋ የሚያስከፍለው ቢሆንም እንኳን፣ ሁልጊዜም ቢሆን ለጓደኞቹ በቅርብ የሚገኝ ሰው ነበር። እርሱ ባለማቋረጥ የሚረዳ የነበረ፣ በከፍተኛ ፍላጎት የሚሟገት፣ እና ለትውልዱም ደግሞ የመነሣሣት ምንጭ የሆነ ሰው እንደ ሆነ በሚገባ ያስመሰከረ ሰው ብቻ ሳይሆን፣ ብሩህ ጭንቅላት ያለው ምሁር ጭምር ነበር። ሌላው የምገልጸው ነገር በጣም ብሩህና ከትውልዳችን እምብዛም የማይርቅ አማካሪ ማግኘቴን ነው። አማካሪዬም ፕሮፌሰር ባሕሩ ነበረ። አማካሪዬ የሚሆንልኝን ይህንን ፕሮፌሰር በማግኘቴም በጣም ዕድለኛ ነበርኩ። እርሱ እንደ ተማሪው ሳይሆን፣ ይልቅ እንደ ሥራ ባልደረባው አድርጎ መቀበሉ ሳያንሰው ሁለታችን በወዳጃዊ መንፈስ አብረን እንድንሠራ የተመቻቸ የግንኙነት ስፍራን ሊፈጥር እንደ ቻለ እመሰክርለታለሁ። በጊዜው እርሱ ከእኔ በእድሜ በጣም ባይበልጥም፣ 'አንቱ' እያልኩ ስጠራው ቆይቼ የበለጠ በወዳጃዊነት እየተቀራረብን ስንሄድ፣ በዚያ መንገድ እርሱን መጥራቱ ምቾት እንደማይሰጥ ተሰማኝ። አንድ ቀን ቢሮው ድረስ ሄድኩና ጉዳዩን ሳዋየው ፈገግ ካለ በኋላ፣ "ከሐረር ባህል የመጣህ ሆነህ ሳለ፣ ነገሮችን ምን ያክል አካብደህ እንደምትቆይ ለራሴ ስጠይቅ ነበር፤" ሲል መለሰልኝ። ይህን ጊዜ፣ ሁለታችንም ሳቅንና አንዳችን ሌላችንን እንዴት እንደምንይዝ ነገሩን ፈታነው።

በታሪክ ትምህርት ክፍል ውስጥ ባለው የድኅረ-ምረቃ ትምህርት ክፍል አራት ተማሪዎች ነበሩ። ትምህርት ከመጀመሩ ብዙም ሳይቆይ አባቡ የሚባለውና ከአራቱ አንደኛው የነበረው ተማሪ ትምህርቱን አቋርጦ ለቀጥታ የፒኤች.ዲ ትምህርት ወደ ቡልጋሪያ ሲሄድ የቀረነው፣ ቤን፣ ሰሌ እና እኔ በድኅረ -ምረቃ ትምህርታችን ላይ ገፋንበት። ከቆይታ በኋላ፣ ትምህርት ክፍሉ ለሁላችንም የምርምር ውጥን-ሥራችን በከተሞች ልማት ፍሬ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር እንዲሆን መረጠ። ውጥን-ሥራዬን ወይ በአርጎባ ሕዝቦች ታሪክ ላይ አሊያም ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ትውፊታዊ ሃይማኖቶች በአንደኛው ገጽታቸው ላይ ሳተኩር እንደምችል አስቤ የነበረ ቢሆንም፣ ምርጫውን ሳይሰጡኝ ቀሩ። እኔ ግን፣ አጋዴን ውስጥ ስልታዊ ከተማ በሆነችው ጅጅጋ ታሪክ ላይ ለማጥናት እፈልግ የነበረ ሲሆን፣ ጅጅጋን እንድመርጥ ውሳኔዬን ካጠናከሩት ነገሮች አንደኛው በዚያ ከተማ ትገኝ ከነበረችው አዜብ የምትባል

ልጃገረድ ጋር የነበረኝ ጓደኝነት ነበር። ጅጅጋን መምረጤ ኋላ ሳስበው መልካም ምርጫ እንደ ነበረ ተረዳሁኝ። በምርጫዬም ሳልጸጸት ጥሩና ጠቃሚ ጥናት ለማድረግ ወሰንኩ። ደግሞም ኢጋዴንን በማካተቱ በዚያ ልምምድ ውስጥ የገዛ አባቶቼ የነበራቸውን ሚና እና የከፈሉትን ዋጋ በተመለከተ ብዙ ተምሬያለሁ። ጅጅጋን በማጥናቴ ውስጥ የነበረኝ ተሳትፎ በአፍሪቃ ቀንድ የችግር ቀጣና ከሆኑት ጋር በተያያዘ ትልቅ የጥናትና ምርምር ውጥን-ሥራን ለማከናወን ሰፊ መስከና በር ከፈተልኝ።

በ1977 ዓ.ም ሰሜናዊውን እና ማዕከላዊ የኢትዮጵያ ክፍሎችን የመታው ሰፊ ድርቅ ከመከሰቱ የተነሣ መንግሥት የመንደር ምሥረታ ዕቅድን ይዞ መጣ። ዕቅዱም፣ የፋኩልቲ አባላት፣ የአስተዳደር ሠራተኞች እና ተማሪዎች ለመልሶ ስፈራው መርሐ-ግብር ዝግጅት መሳተፍ እንዲችሉ ሁሉም ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች እንዲዘጉ የግድ የሚል ሆነ። አዲስ ነገር ለመቀበል ዝግጁ ያልሆኑ የምንባለውና በመርሐ-ግብሩ ውስጥ የተሳተፍነው ተማሪዎች በታሪካዊው የአድዋ እና የማይጨው ዘመቻዎች ላይ በ1928 እና በ1977 ዓ.ም ከተሳተፉት አርበኞች ጋር በተያያዘ መልኩ ራሳችን ላይ ለመቀለድ "ባልቻ አባ ነፍሶ" ብለን መጠራራት ጀመርን።[15] ይህንን ስናደርግ፣ እየጠቆምን የነበረው እውነታ እኛም እንዲሁ በሁለት ዘመቻዎች የተሳተፍን መሆናችንን ነበር፤ ይሄኛውን እና በ1967/8 ዓ.ም የተካሄደውን በማገናኘት።

## አዲሱ የእቅጣጫ ቅያሪ - ትልቁ አስደናቂ ክስተት

መንግሥት እውነተኛውን መርሐ-ግብር ባስጀመረ ጊዜ፣ በጎጃም ክፍለ-አገር ቻግኒ ወረዳ ውስጥ ባለው ጉምላክ ተብሎ በሚጠራ ቦታ ተመደብኩ። በሕዝብ መጓጓዣ መኪና ለሁለት ቀናት ከተጓዝን በኋላ፣ ወደ ጣቢያው ስንደርስ የጉምላክን ሜዳ ከብበው የተተከሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ድንኳኖችን ማየት ቻልን። እያንዳንዱ ድንኳን ስምንት ሰዎችን የሚይዝና ለሠራተኞችና ተማሪዎች በየደረጃቸው የተዘጋጁ የተለያዩ ማዕዘናት ያሉበት ሲሆን፣ ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት የምንከርምባቸው አዳዲሶቹ ቤቶቻችን አድርገን ገባንባቸው። በዛው አውቶቡስ ውስጥ የነበርን ስምንታችን በዘፈቀደ ተሰባስበን የስምንት ሰዎችን ቡድን ሠራንና ከወረድንበት ብዙም ባልራቀው አንደኛው





ድንኳን ውስጥ እንድናርፍ ተመደብን። ከዚያች ድንኳን ጓደኞቼ መካከል ተስፋዬ፣ ጌች፣ ታሜ፣ አሌክስ፣ ገብሬት፣ ቴዲ የሚባሉ ስሞችን አስታውሳለሁ።

ጉምላክ ከደረስን ከሁለት ቀናት በኋላ የመስክ ሥራ ስንጀምር የእኔ የሥራ ድርሻ አዘውትሬ አቦ ተክሌ ብዬ ከምጠራው ሰው ከትትል ጋር ከታሪክ ትምህርት ክፍል የሆኑትን የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች በኃላፊነት መምራት ነበር። የተሰጠን ሥራ አሰልቺ ተግባር ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ማለዳ ወደ ቁጥቋጦዎች ሄደን እንጨት ከጫካ እንቆርጥና አዲስ ለሚመጡት ሰፋሪዎች የባለ ሣር ጣሪያ ክዳን ያለው ጎጆ ቤት እንሠራለን። እኔን ጨምሮ አብዛኞቻችን ቀደም ብሎ ጎጆ ቤቶችን የመገንባት ልምድ ያልነበረን ከመሆናችን ባሻገር፣ አካባቢው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ እና የራቀ ድንግል መሬት ነበር። ስለ አካባቢው መልክዐ-ምድር እና አጠቃላይ ከባቢ ሁኔታ ጥቂት እውቀትን ማሰባሰብ እንደ ቻልኩኝ ሁሉ ወደ መስኩ ከመምጣቴ በፊት፣ "ምንም አልኮል መጠጣት የለብኝም፣ ምንም ሲጋራ ማጨስ የለብኝም፣ ደግሞም ምንም ጭፈራ አላደርግም" ብዬ ለራሴ ነግሬ ጭምር ነበር። በዚህ ድንግል መሬት ውስጥ ጊዜዬን በጥበብ ለመጠቀም እና ስለ ቀረው ሕይወቴ ጉዞ ወሳኝ የሆኑ አቋሞችን ለመውሰድ ሆን ብዬ አስቤበታለሁ። ጥልቅ በሆነ ማሰላሰል እና ሰፊ በሆነ መልሶ የማሰብ ሁኔታ አንዳች ዓይነት የማመዛዘኛ ወረቀትን ስለ ኃላፊው ጊዜዬ እንድሠራ እና ራሴን ለመለወጥም እውነተኛ ከሆነ ዕቅድ ጋር ልመጣ ፈለግሁኝ። ምንም እንኳን ይህ ግዙፍ የሆነ ራስን የመለወጥ ተግባር እንዴት እንደሚከናወን ምንም ፍንጩ ባይኖረኝም፣ በሆነ መልኩ በታደሰ እና በተነቃቃ ስብዕና ከመርሐ-ግብሩ ለመውጣት እየተጠባበቅሁኝ ቆየሁ።

ጓደኛዬ ሞግ፣ "ጥቤ በሂደት ራስህን እያጠፋህ ነው" እስኪለኝ ድረስ ከብዙ መጠጥ እና ማጨስ የተነሣ የማያቋርጥ ክብደት የመቀነስ ሁኔታ አጋጥሞኝ ስለ ነበር፣ ሕይወቴን ማባከኑን ለማቆም ቁርጠኛ ሆንኩ። በዘመቻ ጣቢያችን በደረስን በሁለት ቀናት ውስጥ ሰዎች አካባቢውን አስሰው በከፊል አካባቢውን ይዘው የነበሩት የሺናሻ ሰዎች ወደ አካባቢያቸው በግፊት ለመጡት በሺዎች ለሚቆጠሩት አዳዲስ እንግዶች ምግብና መጠጥ የሚሸጡበትን የአካባቢ ንግድ ሥራ እንደ ጀመሩ አስታወቁን። ብዙም ሳንቆይ ጊዜያዊ ምትክ የአካባቢው ምግብ እና መጠጥ ቤቶች እንዳሉ ስላረጋገጥን በከተማዋ ከደረስን ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ከችግሬ ለመውጣት መፍትሔ በማድረግ አስቤው የነበረው ሁሉ

በቀጭኑ አየር ላይ እንደ ጉም በንኖ ጠፋ። ለመኖር የማይመች ከሆነ ሙቀቱ እና በረሃነቱ ባሻገር፣ ጉምላክ በጣም አሰልቺ የሥራ ጣቢያ ስለ ነበር፣ በቁጥቋጠው ውስጥ አድካሚ ከነበረው ሥራ መልስ ከአንዳንድ ጓደኞቼ ጋር ምግብና የአካባቢው ቢራ ወደሚገኝበት ጣቢያ መሄድ ጀመርን። ወደ አካባቢው ሄጄ ጥሩ ምግብ ለማግኘት እና በመጠኑ ለመደሰት ይሄ ለእኔ ጥሩ ሰበብ ሆነልኝ (ይህም የገዛ መሐላዎቼን ለማፍረስ ተፈጥሯዊ የሆነ ዝንባሌዬ ተጨምሮበት ማለት ነው)። ድካሙን ለማስወገድና ስልቹነቱን ለማስቆም አንዳች ነገርን ፈልገን ስናገኘው አንድ ዓይነት ነገርን ደግመንና ደግመን በመሥራቱ ላይ ተጋን። ጊዜያዊ ምትክ የሆኑት መጠጥ ቤቶች ከምግብ ማዕከሎቻቸው ጋር ለእኔ እና ለብዙዎቹ የሥራ ባልደረቦቼ መጠመጃ እና ለእኔም የማላመልጠው ወጥመድ ሆኖ በድጋሚ መጥፊያዬ (ወይም ቤርሙዳ ትራያንግል) ሆኑብን።

አንድ ምሽት፣ ከሥራ መልስ፣ በሥነ-አእምሮ (ሳይኮሎጂ) ትምህርት ክፍል ውስጥ መምህር ከነበረው የሐረር ልጅና የድሮ ጓደኛዬ ከሆነው ከታዴ ጋር ምግብ ለመብላትና ዘና ለማለት ወደ አካባቢው ምግብ ቤት ከሄድን በኋላ፣ ዳግም የሚባል የአካባቢውን አረቄ ጠጥተን ወደ ሠፈራ ጣቢያዎቻችን ሙትት ብለን ሰክረን ተመለስን። በማለዳ ከመጥፎ ራስ ምታት ጋር ነቃሁ፣ ደግሞም አስጨናቂ በሆነ ጸጸት ተሞልቼ ለመሥራት በጣም ተቸገርኩኝ። በሕሊናዬ የውስጥ ጥልቀት ውስጥ በብርቱ የሚገሥጸኝና "መሐላህን ለምን ትጥሳለህ?" እያለ ደጋግሞ የሚናገረኝ ድምፅ ልቋቋመው የማልችለው ስለ ሆነ፣ ላልጠጣ እና ላልሰክር በድጋሚ ውሳኔ አደረግሁኝ። ይሁን እንጂ፣ የሰው ውሳኔ ደካማ እንደ ሆነ በእኔ ሁኔታ ውስጥ ሲበዛ ራሱን ግልጽ አደረገ። በየዕለቱ የጉልበት ሥራው እንደ ተጠናቀቀ፣ ወደ ምግብ እና መጠጥ ቦታው የመሄዱ ፈተና በጣም ከባድ ሆኖብኝ ሰነበተ። የእኩዮች ግፊት፣ ስልቹነቱ፣ እና በአብዛኛው የሚቀርብልን ጣዕም-አልባ ስፓጌቲ ምግብ- ሁሉም እረፍት ለማግኘትና ለዕለቱ አንዳች የተለየ የሆነን ነገር ለመለማመድ እንድንፈልግ ጫና በማድረግ ያሤሩብን ነገሮች ነበሩ።

በግዞት ጣቢያው የምንመራው ሕይወት እንደተለመደው መሆኑ ቀጠለ። የሆነ ቦታ ላይ በኃላፊው ጊዜ ላይ ለማሰላሰል፣ በጥልቀት ለማሰብ እና በተለወጠ የሕይወት እይታ ለመውጣት አድርጌው ስለ ነበረው ውሳኔ ማሰብ ስጀምር ውሳኔዬ እንዳልተፈጸመና ደግሞም መጠጣትና ማጨስ እስከ ቀጠልኩኝ ድረስ እንደማይፈጸም አወቅሁኝ። ሁኔታዎች ምንም ሆኑ ምን፣ በሕይወት መሰላል ውስጥ የቆምኩት እንደ ተማሪ ወይም እንደ አስተማሪ የትም





ቢሆን የት የማይቀየር ሰው መሆን እንዳለብኝ ተረዳሁ። ሌላ ቦታ አደርገው እንደ ነበረው ሁሉ በጉምላክም አደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች አደርግ ነበርና፣ "ይህ አጥፊ የሕይወት ዘይቤ የት ይቆም ይሆን?" ብዬ ራሴን መጠየቅ ቀጠልኩኝ።

በጊዜ ሂደት ውስጥ፣ ከምግብ እና መጠጥ ቦታው ቀስ በቀስ መራቅ ጀመርኩኝ። ምሽት ላይ ከሥራና እራት በኋላ፣ የእግር ጉዞ በማድረግ ውብ የሆነችውን የጉምላክን ፀሐይ ስትጠልቅ በማየት እደሰታለሁ። ከእግር ጉዞው በኋላ ወደ ድንኳኔ መጥቼ ሬዲዮ እከፍትና ቢቢሲ ዜና እንዲሁም ሌሎች የሬድዮ ዝግጅቶችን አደምጣለሁ፣ ወይም ከምወዳቸው ዘፈኖች ጥቂቶቹን ከእኔ ጋር አምጥቼ ስለ ነበር የካሴት ዘፈኖቼን እያደመጥኩ እደሰታለሁ። እነዚህም የሚያካትቱት በመሣሪያ ብቻ የተቀነባበረ የጃፓኖች ሙዚቃ፣ የአሜሪካን አገርኛ ሙዚቃ በኬኒ ሮጀርስ፣ እና እንደ አርታ ፍራንክሊን ያሉ ሌሎች፣ ታዋቂውን አፍሪካ አሜሪካዊውን የሙዚቃ ሰው ሥራዎች ነበር።

እነዚህን በማደርግ ጊዜ፣ በባሕሪው ዝምተኛና ራሱን የገዛ፣ ደግሞም ወደ አካባቢው ምግብም ሆነ መጠጥ ቤት ሄዶ የማያውቅ አንድ ሰው በድንኳኑ ውስጥ ነበር። እርሱ ዝምተኛና ቁጥብ ሰው ስለ ነበር፣ ከቀረነው ጋር የሚቀላቀለው አልፎ አልፎ ነበር። ከሥራ በመጣ ቁጥር ሁሉ እራቱን ይበላል፣ የእግር ጉዞ ያደርጋል፣ ከዚያም ወደ ድንኳኑ መጥቶ ያርፋል። ከሜካ እንጨት ቆርጠን ለራሳችን የሠራነው የእርሱ እና የእኔ የእንጨት አልጋ ጐን ለጐን ሲሆን፣ አንድ ምሽት ላይ ሁለታችን ብቻ አብረን በነበርንበት አጋጣሚ ውስጥ ዜና የማደምጥበትን የሬዲዮኑን ድምፅ እንድቀንስለት ጠየቀኝ። ዓይነተኛ በሆነው የሐረሪ አገላለጽ፣ "ይሄ የአንተ የግል ቤት መሰለህ እንዴ?" ብዬ ስመልስለት፣ እረፍት እና የጸጥታ ጊዜ እንደሚፈልግ ረጋ ብሎ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ አስረዳኝ። እኔ ግን፣ ዘና ማለት እንደሚያስፈልገኝ ችክ ብዬ እንድፈጽምለት የጠየቀኝን ነገር ችላ አልኩት። ምንም እንኳን ቢበሳጭም፣ ከዚያ በኋላ ከእኔ ጋር መጨቃጨቅ አልፈለገም።

ይህ ሰው የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቱን እየተማረ በዛውም የምጣኔ-ሐብት (ኢኮኖሚክስ) ትምህርት መምሪያ ውስጥ መምህር ሆኖ የሚሠራ ሰው እንደ ነበር አስቀድሞም አውቄያለሁ። አዲስ አበባ ውስጥ በድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤቱ እንግዶች ማረፊያ ውስጥ በአንድ ዓይነት የመኖሪያ ሕንጻ ውስጥ አብረን

ኖረናል። ያን ጊዜ፣ ሰላምታም እንኳን ተለዋውጠን እስከማናውቅ ድረስ ከእርሱ ጋር ምንም ዓይነት መግባባት አልነበረንም። ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ በሆኑ የሕይወት ዘይቤዎች ውስጥ እንኖር ነበርና እኔ እና ከሐረር የሆኑት ሌሎቹ ጓደኞቼ ይህንን ባሕርይ "ደቡር" ብለን እንገልጸዋለን፤ - ደባሪ እንደ ማለት። ዛሬ ላይ ግን፣ በመድረሻ ዕጣ ፈንታ ኩተያዙ በአንዳች ያልታወቀ የክስተቶች ቅደም-ተከተል የተነሣ በአንድ ጣራ ሥር አብረው የሚኖሩ የድንኳን ጓደኛሞች ሆነን ተገኘን።

ቀስ በቀስ፣ በተለይም ደግሞ ወደ ምግብ እና መጠጥ ቦታዎች መሄድ ካቆምኩኝ በኋላ፣ ሁለታችን አንዳች ዓይነት ያልተለመደ ግንኙነትን ማዳበር ጀመርን። አንድ ላይ ሆነን የቀኑን ሞቃትና ወበቃማ አየር ንብረት ከሚያመጣው ውጤት ለማገገም ስንል ቀዝቃዛውን የጉምላከን አየር በምሽት የምናጣጥምበትን የረጅም ርቀት የእግር ጉዞዎችን እናደርግ ጀመር። እርሱም ቀስ በቀስ ልቡን እየከፈተ በእግዚአብሔር ስላለው እምነት እና ያ ደግሞ እንዴት የእርሱን ሕይወት እንደሚመራው አጫወተኝ። መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያነብብ እና ሕይወቱን የሚመራበትን መርኖዎች ከዚያ መጽሐፍ እንደሚያወጣ ሲነግረኝ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ስለ ክርስትና እምነት መስማቱ ለእኔ ያልተለመደ ነገር ነበር። አማኝ ሆኖ ምሁር የመሆኑም ነገር እንዲሁ ለእኔ ያልተለመደ ነገር በመሆኑ፣ ስለ ሃይማኖት ጉዳዮች በሰፊው መሐይም ሆኜ ራሴን አገኘሁት።



በጉምላከ የዘመቻ ጣቢያ

ሕይወትን ለመምራት የተደራጀ መርኅ ከሃይማኖት ወይም ከእምነት መጽሐፍ እንደሚገኝ መስማቱ የማርክሲስትን *"ሃይማኖት የሰዎች የአንቅልፍ ኪኒን ነው"* የሚል አዋጅ የሚናገሩትን መጻሕፍት ሳላፍር እገዛ ለነበርኩት ለእኔ አዲስ ዜና ነበር። ለዓመታት፣ ያንን አዋጅ አስተናግጄው፣ አምኜበት፣ እና ይልቁኑም በክፍል ውስጥ በጋለ ስሜት ሆኜ አስተምሬው ነበር።





ይህንን ሰው አብልጬና አብልጬ በሰማሁት ቍጥር እያወራው ያለው ነገር በሙሉ አዲስ እና ሊገባኝ የማይችል ዓለም ሆነብኝ። ይህ እንግዲህ ያደግሁት በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ መሆኑን፣ ከአባቴ ጋር በመደበኛነት የምሄደው ወደ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን መሆኑን፣ እና በጾምና ሕጉን በመጠበቅ የተሰጠ አማኝ ለመሆን የሞከርኩትን ሁሉ የሚገዳደር አዲስ ነገር ነበር። ልጅ ሆነን ቅዱስ ቁርባን ስንወስድ በእነዚያ ዘመናት ይሰማኝ የነበረውን ደስ የመሰኘትና የቅዱስነት ስሜት፣ እግዚአብሔር በእነዚያ አጋጣሚዎች ውስጥ ለእኔ በጣም እንደ ቀረበ ያክል ይሰማኝ የነበረውን ሁሉ በግልጽ አስታውሳለሁ። ቅዱስ ቁርባን በምንወስድበት ቀን፣ ራሳችሁን ታረክሳላችሁ ተብሎ ተነገሮን ነበረና ከዛፍ ላይ ቅጠል እንኳን ለመቁረጥ በማይፈቀድልን መልኩ ስለ ባሕርይዎቻችን እና ስለ ድርጊቶቻችን በጣም ጥንቁቅ መሆን ነበረብን። እኔም፣ በእድሜ የገፉት የማኅበረሰቡ ሰዎች የተባረከ ቅዱስ ልጅ ነው እስኪሉኝ ድረስ ጥሩ ልጅ ነበርኩኝ።

በልጅነት ዘመኔ እግዚአብሔርን የምፈራበት የመረጋጋት ስሜት ያለኝ ገር እና ጥሩ ባሕርይ የያዝኩ ልጅ ሆኜ አድጌያለሁ። በድህነት በማደጌ እና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰብ በመገኘቴ፣ እግዚአብሔር እውነተኛ የኃይሌ ምንጭ ነው፣ ደግሞም ኮሌጅ ገብቼ ጥሩ ተማሪ እንድሆን ያስቻለኛል፣ እንዲሁም በጥቅሉ በሕይወት ውስጥ ስኬት ይሰጠኛል ብዬ አምን ነበር። ሐረር ውስጥ የ፱ኛ ክፍል ተማሪ በነበርኩኝ ጊዜ፣ በከተማው መሃል ወደሚገኘውና ደጃፉንና በሮቹን እሳለመው ወደ ነበረው፣ ደግሞም፣ እግዚአብሔር እንዲረዳኝ እጸልይበት ወደ ነበረው መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን እሄድ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። በቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት በነበርኩኝ ጊዜ በልዩ ልዩ የክርስትና እምነቶች ልዩነቶች ላይ ጥናት አድርጌ በጣም አሳማኝ የሆነውን አንደኛውን እምነት እንደምይዝ ለእግዚአብሔር ቃል መግባቴ ራሱ ትዝ ይለኛል። የቤተ ሙከራ ትምህርት ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እምነቴ በመጠኑ ተንጦ የነበረበት ቦታ ነበር። በሳል ባልነበርኩበት እድሜ ላይ በላቀ የዓለማዊ ሥልጠና፣ በከፍተኛ ፍጥነት እና ከተለያዩ የእምነት አቋሞች የመጡ ሰዎችን በመተዋወቅ በድንገት ወደ አዲስ የዩኒቨርስቲ ድባብ በግድ ገባሁ።

በቤተ ሙከራ ትምህርት ቤቱ ውስጥ፣ በብዙሃኑ ባህል ከመዋጤ በፊት በጾምና በጸሎት ራሴን የተሰጠሁ አድርጌ ለማቆየት በመሞከር ሃይማኖታዊ

ጥሪቶቼን የሙጥኝ ለማለት ታግያለሁ። ብልጭ ድርግም የሚለውን እምነቴን እንዴት፣ የት ወይም መቼ እንዳጣሁት ግን በእውነት አላውቅም።

ኤርትራዊው የምጣኔ-ሐብት ምሁር፣ ጣዕመ፣ ክርስቲያን የሆነበትን እምነቱን እና ያ ደግሞ ለእርሱ ሕይወት ምን ማለት እንደ ሆነ ደግሞ ደጋግሞ አካፈለኝ። ጊዜ በገፋ ቍጥር፣ ስለ እምነቱ ግልጽ የሆኑትን ነገሮች፣ በተለይ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙነት ላይ ትኩረት በማድረግ ተጨማሪ ነገሮችን ይነግረኝ ጀመር። ታሪኩን እየፈጠረ እንደማይነግረኝ ለእኔ በጣም ግልጽ እስኪሆን ድረስ እንደሚታመን እና የሚደገፉበት ሰው ከልቤ ሳደምጠው የሐቅ ሰው እንደ ሆነ እያስተዋልኩ መጣሁ። ለምሁራን፣ ወይም ከፍተኛ ትምህርት ላላቸው እንደ ጣዕመ ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ማመን ፈጽሞ አብሮ የማይሄድ ነገር ነው ብዬ እገምት ስለ ነበር፣ ነገሩ ፈጽሞ የማይገባኝ ነገር ሆነብኝ። የእኔ ሐሳብ "ክርስቲያን ነኝ"! የሚሉ ምሁራን ከእውነታ ንክኪ ጨርሰው የሚወጡ ሲሆኑ ግድ ነው የሚል ሲሆን፣ ይህ የእኔ እምነት መሠረት ያልነበረው ግምት እንደ ነበረ አረጋገጥሁ።

አወያይ እና ታሪካዊ በሆነው ቁስአካላዊነት ላይ፣ እንዲሁም ከማርክስ እና ኤንግልስ እስከ ስታሊን ካሉት የማርክሲስት የጽሑፍ ሥራዎች የሚስብ ተውኔታዊነትን ተጠቅሜ ስለ ሰው ልጅ ዝግመታዊ አመጣጥ በጋለ ስሜት አስተምሬ አውቃለሁ። አብዛኞቹ ተራማጅ የተማሩ ሰዎች ከሚያንቆለጳጵሱበት የትምህርት ባህል ውስጥ ተካፋይ ከነበሩት አንዱ እኔ የነበርኩ ስሆን፣ ስለዚህ ጉዳይ ምንም ቅሬት ወይም ጥርጣሬ አስተናግጄ አላውቅም። በጊዜው የእነዚህ ፍልስፍናዎች የማያወላዳው አዋጅ "እግዚአብሔር ሞቷል!" የሚለው ነበር። በታሪክ ጉዳዮች እና ከመደብ ትግል ንድፈ-ሐሳብ ጋር በተያያዘ የማርክሲስት ቋንቋ ባሠለጠነው የሰው ፍጻሜ ላይ ያሉኝን እውቀቶች በማስተላለፌ በተማሪዎቼ ዘንድ በጥሩ ስከበርና ስወደድ ኖሬያለሁ። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ መልካም አርዓያነት ያለው እውነት ብዬ እገምተው በነበረው በዚህ ነገር ላይ ምንም ከስታራ ተግዳሮት በተቃውሞ መልክ ከማንም ዘንድ መጥቶብኝ አያውቅም ነበር።

ምናልባት ለእኔ ሳይታወቀኝ አንዳች ዓይነት የምሁራዊነት ባዶ ጉራ አዳብሬ ሊሆን ይችላል። ከጥንታዊ ፍልስፍና እስከ እንደ ጄን ፖል ሳርትሬ





'ኤክዘስታንሺያሊዝም' ያሉ፣ የአይን ራንድ 'ፖዘቲቪዝም' እና በርትራንድ ሩሴል ያሉ እግዚአብሔርን የሚክዱ "አናሊቲካል ፊሎዞፊ" ዓይነት ዘመናዊ የፍልስፍና አዝማሚያዎች ድረስ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በርካታ መጻሕፍትን አንብቤያለሁ። ሥነ-ጽሑፍን በተመለከተ፣ ጥንታዊ ሥነ-ጽሑፎችን በአብዛኛው ከብሪታንያ እና ሩሲያ የሥነ-ጽሑፍ ትውፊቶች (ከበርናርድ ሻው እስከ ዶስቶቪስኪ ድረስ) አንብቤያለሁ። እንዲሁም በኤ. ጄ. ክሮኒን፣ ሐሮልድ ሮቢንስ፣ ኢርቪን ዎሌስ እና የመሳሰሉት የተጻፉ ልብ ወለዶችንም አንብቤያለሁ።

ከዓለም አቀፍ የኮሚዩኒዝም እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ እየሆነ ያለውን የትኛውንም ነገር እያጣሁ እንዳልሆንኩኝ እርግጠኛ መሆን እፈልግ ስለ ነበር፣ ዓለም አቀፋዊውን ተራማጅ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በቅርበት እከታተላለሁ። በምሥራቅ አውሮጳ፣ በተለይም ከአልባኒያ የሚተላለፈውን የቲራና ራዲዮ ሥርጭት በመከታተል እየተከናወኑ የነበሩትን ክስተቶች በብዛት አደምጣለሁ። የአልባኒያ የሠራተኞች ፓርቲ ታሪክ ላይ የተጻፈውን ትልቅ መጽሐፍ ከማንበብ ባለፈ፣ በመሪያቸው በኤንቨር ሆዛ ሲበዛ ተስቤያለሁም። እንዲሁም በካፒታሊስት ማኅበረሰብ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ በጕጕት ስከታተል ኖሬያለሁ። አንድ ጊዜ አብዮቱ ከመፈንዳቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ለንግድ ሥራ ጕዞ 1966 ዓ.ም ላይ ወደ ኢትዮጵያ ለመጣ አሜሪካዊ መኮንን ጉዳይ አስፈጻሚ እንደ ነበርኩ ትዝ ይለኛል። ታዲያ ይህ ሰው ከመሄዱ አንድ ቀን በፊት ከእርሱ ዘንድ እንደ ስጦታ ምን ልቀበል እንደምፈልግ ጠየቀኝ። በየትኛውም መንገድ ሊረዳኝ ፈቃደኛ ስለ ነበር፣ በከፍተኛ ጥማት ላነብባቸው እፈልጋቸው የነበሩትን በተራማጅ አስተሳሰብ ላይ የነበሩትን የአውሮጳ ማርክሲስቶች መጻሕፍትን ዝርዝር ሰጠሁት። እርሱም፣ ሊያደርግልኝ ከሚችላቸው መልካም ነገሮች ሁሉ ይልቅ እነዚህን ዝርዝሮች ሲመለከት እጅግ ተደንቆ የነበረ ቢሆንም፣ አንዳቸውም ግን ከእርሱ አልደረሱኝም። በመሠረቱ፣ ያን ጊዜ ትክክለኛ የመልእክት አድራሻ ኖሮኝ እንደ ነበረ እንኳን በእርግጠኝነት አላስታውስም።

በ1965 ዓ.ም አገር ጎብኚ ሆኖ ከኔዘርላንድ የመጣውን ፈላስፋ ከአዲስ አበባ ወደ ድሬዳዋ በሚወስደው ባቡር ውስጥ እንደ ተዋወቅሁ አስታውሳለሁ። በጀመርነው ውይይት ውስጥ ብዙም ሳንቆይ ተራማጅ ማርክሲስቶች እንደ

ሆንን አንዳችን ሌላችንን አወቅን። በመላው ጉዞ ላይ ከምላ ጎደል ምንም ሳናቆም እየተወያየን የነበረ ሲሆን፣ በጭውውታችን ውስጥ የተለየ የማርክሲስት ሥነ-ጽሑፍን ባነሣ ቊጥር ጽሑፉን እንዳነበብኩት እያሳወቅሁት አስደንቀዋለሁ። ከዚህ የተነሣ፣ እርሱም ስለ አፍሪካ የገዛ ራሱ አውሮጳዊ ግምት እንደ ነበረው ተረዳሁ። እየተስገበገቡ የሚያነብቡ እና በዓለም ላይ እየሆነ ያለውን የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ትውልዶች እንዳሉ ምንም ፍንጭ ኖሮት አያውቅም ነበር። ከባቡር እንደ ወረድን፣ በተመሳሳይ የፔጆ ታክሲ ወደ ሐረር ተሳፍረን ሄድንና ከእኔ ጋር ለሳምንት ያክል አብሮ ወዳሳለፈበት፣ ደግሞም ከሌሎች የሐረር ጓደኞች ጋር በርሜን አብሮን ወዳጣጣመበት ወደ አጎቴ ቤት ወሰድኩት። ጫት እንዴት እንደሚቃም የተግባር ሥልጠና ሰጠሁትና በፍጥነት ሲለምደው የበርጫ በዓላችንን የወደደው መሰለ። አዲስ ያገኘሁት አውሮጳዊው ማርክሲስት ጓደኛዬም ወደ አገሩ ሲመለስ ያንኑ ጥያቄ ጠየቀኝ፦ "ምን ላደርግልህ እችላለሁ?" እኔም፣ የማርክሲስት መጻሕፍትን፣ በተለይም በአዲሶቹ የአውሮጳ ወይም የአሜሪካ የፖለቲካ ሶሻሊስት ምሁራን የተጻፉትን እንዲልክልኝ ጠየቅሁት።

ከጥቁሮች ንቃተ ሕሊና እንቅስቃሴዎች ልዩ ልዩ ባሕርያት ጋር ተላምጄ ስለ ነበር፣ በአሜሪካ ከነበረው የሰብዓዊ መብት እንቅስቃሴዎች ጋር በጥሩ ሁኔታ መግባባት መጀመር ችዬ ነበር። ከዚህ የተነሣ፣ የብላክ ፓንተር ሙቭመንት ተብሎ የሚጠራው እንቅስቃሴ ላይ በጣም ተደምሜ በኤልድሪጅ ክሌቨር የተጻፈ *ሶል ኦን አይስ* የተባለውንና ሌሎችንም በአንዳንድ አባሎቻቸው የተጻፉትን መጻሕፍት ማንበቡን ተያያዝኩት። በአንጀላ ዴቪስ እና አሜሪካ ውስጥ ስላለው መዋቅራዊ ዘረኝነት ላይ ስለ ነበራት ትግል ሲበዛ ከመደነቄ የተነሣ፣ ለዓመታት ይገዌው የኖርኩት የአፍሮ ጠጉር አበጣጠሬ እርሷ በሕይወቴ ላይ የነበራት ተጽዕኖ ምልክት ሆኖ ቆይቷል። ሌላው ያስደመመኝ የሰብዓዊ መብቶች እንቅስቃሴ ዘመን ተሚጋች ማልኮልም ኤክስ በመሆኑ በገዛ ራሱ የጻፈውን ግለ-ታሪክ አንብቤያለሁ፣ ደግሞም የእርሱን ሕይወት እና ዘመን የሚገልጸውን የተቀዳ ታሪክ አድምጬያለሁ። ሊታይ እንደሚችለው ሕይወቴ በእያንዳንዱ አቅጣጫ እየሄደ ይሁን እንጂ፣ ምን እፈልግ እንደ ነበረ እና በመጨረሻ ምን ማሳካትን እፈልግ እንደ ነበረ አላውቅም ነበር። ሕይወቴ ጨርሶ ስላልተረጋጋ እና ልቅ ስለ ነበር የተሻለ የሚገልጸው አባባል "ድንበር-አልባ





ሕይወት" የሚለው ነው። ለሕይወቴ ስልታዊ አቅጣጫን ማንም ስላልሰጠኝ፣ ግልጽ የሆነ ትኩረት እና ራእይ አልነበረኝም። ብዙ ያነበብኩ እና ሐሳባዊ የዓለም አቀፍ መነሣሣቶች የነበሩኝ ብሆንም፣ ምንም ጥሩ ነገር በሌለው እና ራስን በማጥፋት ሕይወት ውስጥ ኖርኩኝ፣ ከፉ በሆነ ወታደራዊ አገዛዝ ከብደት ተጨፈለቅሁ። የኢትዮጵያ አብዮት ያልተፈታ ነገር ያለው መሆኑ ለእኔ እና ለአብዛኞቹ የእኔ ትውልድ ሰዎች ሲያስጨንቀን ቆይቷል። የኢትዮጵያ አብዮት የገፋፋው መጠባበቅ ከፍ እያለ መሄዱ፣ ለዚያም የነበረን አዎንታዊ ነውጠኝነት፣ እና ተስፋችንን ቆራርጦ ወደ ተለየ አቅጣጫ ተጓዘ፣ ደግሞም አንጠልጥሎ ተወን።

በእንዲህ ዓይነት ዳራ ውስጥ ነው እንግዲህ እንግዳ በሆነ መልኩ በግፊት በሆነው የሰፈራ ጣቢያ ላይ ሕይወቴ የተለየ የአቅጣጫ ለውጥን የወሰደው። ምንም ትልቅ ሐሳባዊነትን ለአእምሮዬ ሳልመግብ፣ ምንም ነውጠኛ ራእይን ሳላቀጣጥል እና ሕይወቴን ሳላሟሙቅ ከማርክሲዝም የቁም ቅዠት ጨርሼ በመንቃት ወደ እውነቱ ለመመለስ የምይዘውን ነገር እፈልግ ነበር። ከሕይወት ውስጥ በእጅጉ ጠፍተዋል ብዬ አስባቸው የነበሩ ነገሮችን ተከታትዬ ለመያዝ ሞከርኩኝ። ራስ ወዳድ ካልሆነ ሕይወት ወደ ራስ ወዳድ ሕይወት 180 ዲግሪ አቅጣጫ በመቀየር፣ አብዝቼ በመጨፈር እና ልቅ በሆነ የወሲብ ስሜት የፍቅር ሕይወትን ያለገደብ በመምራት እንደ አብዮተኛ ማድረግ እጠላቸው የነበሩትን ነገሮች ኖሬባቸዋለሁ ማለት እችላለሁ። ይህ ሕይወት ልታይ ልታይ ባይነት ውስጥ፣ ጥፋተኝነት፣ እና የማያመልጡት ተቃርኖ ጋር በተቀየጡ በአንዳንድ ልምምዶች እና ተግባራት ውስጥ ከተተኝ። አሳማኝ የሆኑ ብሩህ ዕድሎች ያሉኝ የዩኒቨርሲቲ መምህር ሆኜ እንኳን መንገዴ እንደ ጠፋብኝ እና ምንም ግልጽ አቅጣጫ ሳይኖረኝ እየተንቀሳቀስኩ እንደ ነበረ ለእኔ ግልጽ ሆነልኝ። በእነዚያ ዘመናት የነበረኝን ሕይወቴን "እየኖሩ ማባከን እና እያባከኑ መኖር፣ ደግሞም ጥቅል ገንዘቡ ሲቆም ይህንን ዓለም መሰናበት" በሚል ልገልጸው እችላለሁ።

ጉምላክ ውስጥ ጣዕመን ሳገኘው የሕይወቴ ዳራ ይሄንን ይመስል ነበር። ምንም እንኳን ያ እንዴት እንደሚሆን ምንም ፍንጩ ያልነበረኝ ብሆንም እንኳን፣ በድንግሊቱ ምድር ያለው የዘመቻ ተሞክሮ እና ጥቅጥቅ ያለው ጫካው የሰጠኝ የማሰላሰል ጊዜ ቋሚ ነገርን ስለ ሕይወት መልሼ እንዳስብ አድርጎኛል ብዬ እገምታለሁ። የጉምላክ ጫካ እና ጸጥተኛ አካባቢው ለሕይወቴ አደናጋሪ

የሆነውን መንገድ የማጠራበትን ትክክለኛ ነገር ስላቀበለኝ፣ በዚህም ምክንያት ያለፈውን ሕይወቴን እንዳገናዝብ አስችሎኛል። የነበረኝ ቅዠት ይህ በስብዓዊ መንገድ ብቻ ሊጨበጥ የሚችል ነገር እንደ ሆነ አድርጌ መውሰዴ ነበር፣ - እንደዚያ ግን አልነበረም። የተለያዩ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ አሁንም አሁንም በዛው ወጥመድ እየተያዝኩ በአንድ ዓይነት መንገድ ሳሽቆለቁል ላስተዋለው አሳዝን ነበር።

ጣዕመ ስለ እግዚአብሔር የነበረው እውቀት፣ የእርሱ ሐቀኝነት እና ትክክለኛ እምነት ኃይለኛ ተግዳሮት ሆነብኝ። በደንብ እየተላመድን ስንመጣ፣ "ምሁር እንደ ሆኑ በእግዚአብሔር ማመን ይቻላል ወይ?" "በምሁራዊ አስተሳሰብ እግዚአብሔርን እንዴት መረዳት ይቻላል?" "እምነታችንን በእርሱ ላይ ለማኖር ማረጋገጫ የሚሆነው ነገር ምንድን ነው?" የሚሉ ኮስታራ እና ሐቀኛ ጥያቄዎችን ለማንሣት በቂ ብርታትን ጎትቼ አወጣሁ። በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር የሚታወቅ ሊሆን ይችል እንደ ሆነ፣ ደግሞም እንደ እኔ ያለ ዳራ ያላቸው ሰዎች እንዴት ሊያገኙት እንደሚገባ እየጠየቅሁት ነበር ማለት ነው። ጣዕመ መልሶቹን የሚያቀርብባቸው መንገዶች ላይ በጣም ጠንቃቃ በመሆን ጥያቄዬን ለመመለስ ሲል በእኔ በኩል ተቀባይነት የማይኖረውን እና ምናልባትም እርሱን እንዳርቀው ሰበብ ሊሆን የሚችለውን መጽሐፍ ቅዱስን ለአንድ ጊዜም እንኳን ሊጠቅስ አልሞከረም። እርሱ እንዲሁ በቀላሉ ከገዛ የሕይወቱ ልምምድ ጋር በተያያዘ ያሉትን ታሪኮች፣ እግዚአብሔር ለእርሱ ምን ማለት እንደ ሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበቡ ሕይወቱን ለመምራት እና ለማስታጠቅ እንዴት እንደ ረዳው እና በሚችለው ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሕይወት ለመኖር እንዴት ዓላማ ይዞ እንደሚንቀሳቀስ ያሉ ታሪኮችን ይነግረኝ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስን ሳያጣቅስ በዚያ ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች በራሱ ቋንቋ አሻሽሎ ይነግረኝ ስለ ነበር እኔ እና በድንኳኑ ውስጥ ያሉት ቡድኖች የሌለንን አንዳች ነገር በዚህ ሰው ውስጥ እንዳለ ማየት ጀመርኩኝ። ጣዕመ ልዩ ነበር! በእኔ ትውልድ ከነበሩት ሰዎች ውስጥ በአብዛኞቹ ያላየሁትን ጥርት ያለ ሕይወት በእርሱ ውስጥ አይቻለሁ።

አንዳች ዓይነት የመተማመን ግንኙነት እየመሠረትን ስንሄድ፣ "ይህንን እምነት ለመለማመድ የምትሄደው የት ነው?" የሚለውን ጥያቄ ልጠይቀው ደፈርኩኝ። በገርነት ፈገግ ካለ በኋላ፣ ፈጽሞ የማላውቀውን ቦታ ጠቀሰልኝ።





ከእርሱ ጋር እዚያ የሚሄደው ማን እንደ ሆነ ጠየቅሁት - ተራ ሰዎች ወይስ እንደ እርሱ ያሉ ምሁራን? አሁንም በድጋሚ ደግነት ባለው ፈገግታ፣ እርሱ በሚሄድባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም ዓይነት ሰዎች እንደሚገኙ ነገረኝ። በገዛ ራሴ አለማወቅ የተዘለፍኩ ያክል ተሰማኝና መጨረሻ ላይ፣ "በዚህ በጉምላክ ያለንን ተልዕኮ ስንጨርስ ወደዚህ ቦታ ልትወስደኝ ትችላለህ?" ስል ጠየቅሁት። በአዎንታ መለሰልኝ፣ እኔም ይህንን ቦታ እስከየው ድረስ ምን ያክል እጓጓ እና እጠማ እንደ ነበርኩ አልረሳውም።

ከዚህ ሰው ጋር በእምነት እና ክርስትና ጉዳዮች ላይ የነበረን ውይይት ቀጠለ፣ ደግሞም ጠለቅ ያለ ገጽታን እየያዘ መጣ። የኃጢአትን ትርጉም፣ የኃጢአትን ውጤቶች ሳያውቁ ሰዎች ሕይወታቸውን እንዴት እንደሚኖሩ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ መስቀል እና ፋይዳው በሚሉ ኮስታራ ርእሶች ላይ መወያየት ጀመርን። ከጣዕመ እየተቀበልኩኝ በነበረው የእውቀት መገለጥና ብርሃን ሕይወቴን መልሼ መመርመር ስሞክር፣ አንድ ነጥብ ላይ የጠፋሁበትን ሁኔታ ተገነዘብኩኝና እርሱ ያመነበትን እግዚአብሔር ማስተናገድ እንዳለብኝ ተሰማኝ። ልቤ እንዛለት ዘንድ ከዚያም የተነሣ የተሰባበሩትን የሕይወቴን ቁርጥራጮች እንዲሰበስብልኝ እግዚአብሔርን ለማወቅ ጓጓሁ። ጉምላክ ውስጥ ከጣዕመ ጋር ከገጠመኝ መገለጥ የተነሣ አንድ ነገር በአእምሮዬ ውስጥ በማቃጨሉ የክርስትና እምነት በአእምሮዬ ውስጥ ኃላፊ ጊዜዬንና መጪ ጊዜዬን እንዳየሁበት ብልጭታ ሆኖ ያገለገለበትን እውነታ ከእርሱ ተማርኩኝ። ምንም እንኳን የመጣው ካልተጠበቀ ማዕዘን ቢሆንም፣ ጉምላክ በነበርኩኝ ጊዜ ላሳካው ተስፋ አድርጌ የነበረው ያንን ለውጥ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስን እንድቀበል እና ሕይወቴን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር እንድሰጥ በራሱ ተነሣሽነት ጣዕመ መንገድ መርቶኝ ባይሆን ኖሮ፣ በራሴ እንደዚያ ለማድረግ አቅማማ ነበር ብዬ አስባለሁ። ጣዕመ ግን፣ በማላውቀው ምክንያት የተነሣ ያንን ለማድረግ ያልፈለገ ይመስል ነበር። የእርሱ ስልት በቂ የሆነ የእምነት ጥራቶችን በገዛ ራሱ የሕይወት ተሞክሮዎች ላይ መሠረት አድርጎ በሕይወቴ ውስጥ ተቀማጭ ማድረግና ከዚያም ያንን ሁሉ በጥልቀት እንዳስብ ዕድል በመስጠት፣ በገዛ ራሴ አኳኋን ውሳኔውን እንድወስድ ለማድረግ የፈለገበት ይመስለኛል። በሠፈራው ጣቢያ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ለእኔ ያነበበት ወይም ከእኔ ጋር የጸለየበትን የትኛውንም አጋጣሚ ስለማላስታውስ፣ ወደ የትኛውም ውሳኔ ሊያጣድፈኝ

እንዳልፈለገ አስተውያለሁ። ነገር ግን፣ ስለ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ ስለ ሥላሴ ፍሬ ሐሳብ፣ ኃጢአት፣ ድነት፣ እና የመሳሰሉት ብዙ ነገሮች አስተምሮኛል። ስለ ክርስትና እምነት ሀሁ ከእርሱ ብዙ በተማርኩ ቍጥር፣ በልቤ ውስጥ የበለጠ ለማወቅ የበለጠ እፈልግ ነበር። ያን ጊዜ፣ በቀደሙት ዘመናቴ የክርስትና እምነትን ችላ ማለቴ ለብዙ ግራ መጋባት፣ መዋዠቅ እና በሕይወቴ ውስጥም መልህቅ እንዳጣ ዋናው ምክንያት መሆኑን የእውነት አገናዘብኩኝ።

በለጋ የጎልማሳነት ዓመታቴ ላይ ለክርስትና እምነት የቅርብ ትኩረትን ለመስጠት የተወሰኑ ጊዜያት ያክል ዕድሉን አግኝቻለሁ። በደደር በነበርኩኝ ጊዜ፣ ከሸሜ ጋር በሜኖናይት ሚስዮናዊያን ይተዳደር ወደ ነበረው የክርስቲያን ልጃገረዶች ትምህርት ቤት እንዲሁ ለደስታ ስንል እንሄድና የቢሊ ግራሃም ወንጌል ስብከት ዓይነቶቹን ተንቀሳቃሽ ሥዕሎችን እያየን ኃይለኛ ስብከቶችን እንሰማለን። ነገር ግን፣ አእምሯችን የተጠቀጠቀው በሌላ ነገር ስለ ነበረ፣ ምንም ስሜት እንዲሰጠን አናደርግም። እዚያ እንሄድ የነበረው ልጃገረዶችን ለምንፈልግበት ከንቱ ራስ ወዳድ ፍላጎት ነበር። ለበርካታ ጊዜያት፣ በሰባኪው ተውኔታዊ አቀራረብ እና የድምፅ አጠቃቀም ላይ ስንስቅ እና አንዳንድ የእብሪተኝነት አስተያየቶችን ስንሰነዝር ቆይተን አዳራሹን ትተን እንወጣለን። ፊልሙን ይመለከቱ የነበሩትን ወጣት ተማሪዎች እንደ ከንቱ እስረኞች፣ ጅሎች እና የሃይማኖት ባሪያዎች አድርገን ገምተናቸው እናውቃለን። ሁለታችንም በዚያን ጊዜ ሃይማኖት "የሰዎች የእንቅልፍ እንክብል ነው" ብለን የምራችንን የምናምን ሰዎች ነበርን።

ከአጎቶቼ ልጆች አንደኛው በሚስዮናዊያን የመጣ የተሳሳተ እምነት ተደርጎ ይቆጠር ወደ ነበረው አዲስ እምነት የተለወጠበት ጊዜ ላይ አሞኝተውታል፣ ደግሞም ነፍሱን ከሕይወቱ ነጥቀውታል ብዬ በማመኔ በጣም መቆጣቴን አስታውሳለሁ። የአጎቴ ልጅ ሰለሞን ተግባቢ ሰው ሆኖ ሳለ ከአዲሱ እምነቱ በኋላ ግን በድንገት ወደ ደመ-ነፍሳዊ ፍጡርነት የተለወጠ መሰለ። ስለዚህም፣ እርሱን የለወጡትን ሰዎች አጥምጄያቸው በቃላት ጎድቻቸው፣ በድንጋይም ወግሬያቸው አውቃለሁ። ለዚያም ደግሞ ቆየት ብዬ "ዋጋዬን" ማግኘት ነበረብኝና የአጎቴ ልጅ ያደረግሁትን ባወቀ ጊዜ በእርሱ አሸናፊነት የተጠናቀቀ የእውነት አካላዊ ፍልሚያ አደረግን።





በዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበርኩኝ ጊዜ ያገኘኋቸው ሌሎቹ ክርስቲያኖች ከስድስት ኪሎ ወደ አራት ኪሎ በሚወስደው መንገድ ሳልፍ፣ ከምህንድስና ፋኩልቲ ፊት ለፊት ከሚገኘው የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ሲወጡ አልፎ አልፎ የማያቸው ነበሩ። ጠርቀም ያሉት አንድ ላይ ተሰባስበው ባየሁ ቍጥር፣ አእምሮ እና ውስጣዊ ጥማት የጎደላቸው ስሜት-አልባ እና አከርካሪ የሌላቸው ፍጥረቶች የሆኑ ያክል ቆጥሬያቸው አውቃለሁ። በአእምሮዬ ውስጥ እነዚያን አስተያየቶች እንዴት ልፈጥር እንደ ቻልኩኝ እርግጠኛ ባልሆንም፣ ያ የአእምሮዬ የአስተሳሰብ ሁኔታ ግን ኮስታራ በሆኑ አማኞች ላይ ያለኝን አመለካከት ቀረጸው። የወላጆቼ እምነት በሆነው የኦርቶዶክስ ክርስትና አኳያ ምን አመለካከት እንደ ነበረኝ በትክክል አላስታውስም። ሁሉን ባንድ የመደብኩበት የብዥታ ስሜት በአሮጌ ትውፊቶች እስር ሥር ያሉ ወግ አጥባቂዎች እንደ ሆኑ ነበር።

በእነዚያ አስቸጋሪ ዓመታት የመድሃኒዓለም ትምህርት ቤት አስተማሪነቴ ላይ ሳለሁ፣ ድሬዳዋ ውስጥ የሜኖናይት ቤተ ክርስቲያንን ለመጎብኘት ዕድል አግኝቻለሁ። አጠር ያለ ተለዋጭ ገለጻ በማድረግ የዛን አጋጣሚ ዝርዝር ሐሳብ እንደሚከተለው ለመስጠት እፈልጋለሁ።

በመድኃኔዓለም ትምህርት ቤት ውስጥ ብርሃኔ ከሚባል ታሪክ የሚያስተምር ማየት የተሳነው መምህር ጋር ተዋወቅሁኝና ጥሩ ጓደኛሞች መሆን ስንጀምር ብሬ እያልኩ እጠራው ጀመር። እርሱ ገር እና ሲበዛ ቸር ሰው ከመሆኑ ባሻገር፣ ሁለታችንም የምናስተምረው የትምህርት ዓይነት ተመሳሳይ በመሆኑ አንዳችን ሌላችንን በሙያዊ ረገድ አብዝተን መረዳዳቱን ተያያዝነው። ስለዚህም፣ እንደ ጓደኛ በማኅበራዊ እና አእምሯዊ ግንባሮች ላይ መንገዶቻችን በብዙ ተጠላለፉ። በጥቂት ጥርጣሬ ያዩኝ ከነበሩት አንዳንዶች በተለየ ብሬ ያለምንም ጥርጣሬ ሙሉ ለሙሉ ተቀብሎኝ ስለ ነበር፣ የእርሱን መኖሪያ አንዳንድ ጊዜ ስጐበኝ በጥልቀት ልቤን የሚሰረስሩ ሃይማኖታዊ መዝሙሮችን ለአጭር ጊዜም ቢሆን መስማቴን አስታውሳለሁ። ታዋቂ በሆነው የወንጌል ዘማሪ በደረጀ ከበደ የተዘመረውንና እርሱ ቤት የሰማሁትን *"እኔስ በበኩሌ ልበረታ ነው ምኞቴ፤ ጠዋት ማታ ጊዜ አጣሁኝ፣ ዘወትር በውጊያ ላይ እያለሁኝ"* የሚለውን መዝሙር አልረሳውም። መዝሙሩ የእኔን ሁኔታ የሚናገር በመሆኑ እንደምወደው ለብሬ ስነግረው፣ እርሱም አንዳች ዓይነት መደነቅን ያሳየኝና የትኛውንም አስተያየት ወይም ማብራሪያ ከመስጠት ይታቀባል።

ብሬ በጣም ያምነኝ ደግሞም ያከብረኝም የነበረ በጣም የሚስብ ጓደኛ ሲሆን፣ እኔም እርሱን አከብረው እንደ ነበረ ተሰምቶኛል። ቤርሙዳ ትሪያንግል በምንለው የቦቴ አካባቢ አብሮን አልኮል እንዲጠጣ አንዳንድ ጊዜ ከእኔ ጋር አወስደውና ብዙ አልኮል በወሰድኩኝ ቁጥር ባሕርዬ የሚለወጥበትን ሂደት እንዲመለከት እጠይቀዋለሁ። በሚቀጥለው ማለዳ የአዳሬን ዘገባ ሲሰጠኝ በደቂቃዎች ዝርዝር ውስጥ ሁኔታዬን አስተካክሎ ሲያስረዳ መስማቱ ያስደንቀኛል። እንደ ሰከርኩ እና በምራመድም ጊዜ እየተንገዳገድኩ ሳለሁ ወደ ቤት ለመውሰድ ስመራው እንዴት እንዳመነኝ እና እንደ ተደገፈብኝ ሳስብ አደነቃለሁ።

አሁን እንግዲህ የብሬን ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ ጎበኘሁ የነበረኝን አጋጣሚ ወደምተርከበት ሁኔታ መለስ ልበል። የሜኖናይት ሚስዮናዊያን ፍሬ ወደ ሆነውና እርሱ ወደሚያመልክበት የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብሬን ልወስድ አልፎ አልፎ ባሉት እሑዶች ላይ ወደ ድሬዳዋ እንሄዳለን። የእኔ ተልዕኮ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አምልኮ ብሬን መውሰድና አምልኮው በተጠናቀቀ ጊዜ ደግሞ ወደ ሐረር መመለስ ነበር። በዚህ ጊዜ፣ አብሬው ብቀመጥም፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ለሚከናወኑት ነገሮች ለአንዳቸውም ግን ትኩረት ሰጥቼ አልከታተልም። በሰባኪው የሚነገረውን አንዱንም ቃል ለመስማት ትኩረት አላደረግሁም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሙዚቀኞች የሚዘምሯቸውን መዝሙሮች ቃላትም ሰምቼ አላውቅም። የማደርገው ነገር ቢኖር ሰዓቴን መመልከትና ትዕግሥት-አልባ በመሆን የዝግጅቱን መጠናቀቀ መጠበቅ ብቻ ነበር። አምልኮ ካለቀ በኋላ ለምግብ ወይም ለስላሳ መጠጥ ለመጠጣት የአካባቢውን ምግብ ቤቶች እንፈልግና እርሱ ለስላሳ መጠጡን ሲጠጣ እኔ ግን የናፈቀኝን ቢራ እጠጣለሁ። በዚያ ዘመን፣ እኔ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልፍ ነበር፣ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በእኔ ውስጥ አላለፈችም ነበር።

እንዲህ ያለ የረጅም ታሪክ አቅጣጫ ቅያሪ ያደረግሁት በጣዕመ በኩል ሕያው ከሆነው እግዚአብሔር ጋር የተገናኘሁበትን ወሳኝ አጋጣሚ ለመተረክ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ቀደም ባሉት ጊዜያትም እግዚአብሔርን ለመተዋወቅ አንዳንድ ዕድሎች እንደ ነበሩኝ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት እጅ የማልሰጥ እስከሆን ድረስ አእምሮዬ ዝግ የነበረ መሆኑን ለማሳየት ጭምር ነው። ምናልባት እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ጊዜ እና እንደ ዕቅዱ የሆነ ሥራዎች





ስላሉት ሊሆን ይችላል። የጉምላክ ዘመቻ ጣቢያ፣ ከጣዕመ ጋር መገናኘቴ፣ እና ከእርሱ ጋር ለመገናኘት መለኮታዊት እጅ በሥራ ላይ እንደ ነበረች የምትጠቁም ትመስላለች።

ጣዕመ ለሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ልቤን አንድ ጊዜ ከከፈተው በኋላ፣ ጣዕመን የቅርብ ጓደኛዬ አደረግሁት። እንዲያውም በአዲሱ መንፈሳዊ የማዕድን ፈላጊነት ጉዞዬ ውስጥ እንደ አሠልጣኜ አየው ጀመር። በእርግጥ፣ ጉምላክ በነበርኩኝ ጊዜ እንኳን፣ ሕይወቴን ለኢየሱስ ሳልሰጥም ቢሆን ሕይወቴ በለውጥ ላይ እንደ ነበረ አንዳንድ ማስረጃዎች ታይተዋል። ስለ ክርስትና እምነት በማውቃቸው ጥቂት መሠረታዊ ነገሮች ሕይወቴን ሆነ ብዬ ወደማስተካክለው አንዳች ሁኔታ ለመጣል የምችለውን ያክል ሞክሬያለሁ። ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ እምነትን እንዲሁም ሌሎች ወሳኝ የሕይወት ጉዳዮችን በተመለከተ ተከታታይ የሆኑ የምሽት ውይይቶችን በቀረው የድንኳን ጉርብትና ቆይታችን ወቅት አደረግን።

ሁላችንም ላጤዎች ስለ ነበርን፣ እስከዚያን ጊዜ ድረስ በጣም የተጋጋለውና ተደጋግሞ የምንወያይባቸው ርእሶች ፍቅር እና የጋብቻ ጉዳዮች ነበሩ። ጣዕመ ርእሱን ከአብዛኞቻችን ይልቅ የተሻለ ስለሚያውቀው የመሪነቱን ድርሻ በሚወጣበት የምሽት ውይይት አጀንዳችን ላይ ጣዕመ እና እኔ የሃይማኖት እና የእምነት ነገሮችን ጣልቃ እናስገባለን። ከባድ ጥያቄዎችን ያነሡ የነበሩ የማይበገሩ ሳይንቲስቶች እና ተጠራጣሪዎች በመካከላችን የነበሩ ቢሆንም፣ ነገር ግን ጣዕመ በጥንቃቄ እና በብልሃት ሊመልስላቸው ይሞክራል። ይህንንም በሚያደርግባቸው በሁሉም ጊዜያት ላይ እኛን ለማጥመድ ሳይሆን፣ ነገር ግን ከእምነት ጋር በተያያዘ እንድናስብ እና የምራችንን እንድናገናዝብ በሚፈልግበት ዓላማ ውስጥ ሆኖ ጥያቄዎችን ያነሣና ኃይለኛ በሆኑ ክርክሮች እንድንያዝ ያጠምደናል። እምነታቸውን ያን ያክል አጥብቀው ያልያዙና ጨርሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን የማይሄዱ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በመካከላችን የነበሩ ሲሆን፣ እኔን ጨምሮ አንዳንዶቻችን ባልተለመደ ሁኔታ የነቃንና ስለ ክርስቲያን እምነት ወሳኝ የሆኑትን ነገሮች ለመማር የጓጓን ነበርን። ድንኳኑ ውስጥ በመካከላችን ያሉ ሌሎች በውይይቱ ውስጥ ይሳተፉ የነበሩት እንዲሁ ለጨዋታ እና ጊዜ ለማሳለፊያነት የሚሳተፉ እንደ ነበሩም አስታውሳለሁ።

ለበርካታ ምሽቶች፣ አሁን ላይ ዝርዝር ሐሳቦቻቸውን የማላስታውሳቸው

ርእሶችን ይዘን የተጋጋሉ ውይይቶችን እና ክርክሮችን እናደርጋለን። ነገር ግን፣ በእነዚያ ዘመናት ውስጥ የምሽት ምሁራዊ ውይይቶቻችንን የተቆጣጠረው አንደኛው ወሳኝ ርእስ የእምነት ጉዳይ መሆኑ በራሱ አንድ ትልቅ ነገር ነበር። ይሄ እየተካሄደ ሳለ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት ትቼው ለነበረው ለክርስትና እምነት እየጨመረ ያለ ፍላጎትና መሰጠትን ለማድረግ ምልክቶችን ማሳየት ጀመርኩኝ። ጣዕመ በልቤ ውስጥ የበለጠ ጠልቆ ሥር እየሰደደ ያለና ከሕይወቴ በቀላሉ የማይወጣን አንድ ነገርን አስቀምጧል። ከዚህ የተነሣ፣ ሥራችን ሲያልቅ ወደ ጣዕመ ቤተ ክርስቲያን ልሄድ እንደ ወሰንኩ ለጓደኞቼ ስነግራቸው፣ ከገብራት በስተቀር ሁሉም ያንኑ ፍላጎት እንጸባርቀው ነበር።

ከሁለት ወራት በኋላ ዘመቻው ተጠናቅቆ ወደ አዲስ አበባ በተመለስንበት በመጀመሪያው እሑድ ጣዕመ እና እኔ በፖስት ሬንዴቩ ካፍቴሪያ ተገናኘን። ተቀምጠን ቡና ከወሰድን በኋላ እርሱ ወደሚያመልክባት ቤተ ክርስቲያን አመራን። አይኢሲ ተብሎ በአብዛኛው ይታወቅ ወደ ነበረው ዓለም አቀፍ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ሄድን። አይኢሲ የገንዘብ ወጪው በኤስ አይ ኤም የሚሸፈንለት ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፣ ወደ 4፡00 ሰዓት ገደማ እዚያ ሄድንና ወደ ውስጥ እንድንገባ በአንድ ኢትዮጵያዊ ተስተናገድን። በማኅበረ-ምእመናኑ ውስጥ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ቢኖሩም፣ ምናልባት ወደ መቶ የሚደርሱ የውጭ ዜጎችንም አየሁ። ታዋቂ የማኅበረሰብ ሥራ ትምህርት ፕሮፌሰር የነበረውን ፕሮፌሰር ስዩምንም በዚያ አየሁት። የተለያየ ማኅበረ-ምእመናን የተገኙበት እንዲህ ያለ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ባለበት ውስጥ ተገኝቼም ስለማላውቅ፣ የመጀመሪያው ስሜቴ ግራ የተጋባሁበት ነበር። እንዲሁ ከሚወሰድ ምልከታ ብቻ ታዳሚዎቹ ተራ ሰዎች እንዳልሆኑ ማንም ሊያይ ይችላል። በስሕተት የመጣ ሰው የሆንኩ ያክል እስኪሰማኝ ድረስ፣ እንዲሁም እንግዳ መሆኔን በመጠኑ ያወቅሁ ያክል፣ አንዳች ዓይነት አስቸጋሪ ስሜት እየተሰማኝ አምልኮውን በጭንቀትና ግራ መጋባት ታደምሁ። ነገር ግን የእኔን ተስፋ አዲስ ጨረር ከሩቁ ልመለከተው ቻልኩኝ።

በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ፣ ሰባኪው ከምስባክ ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስን በጠራ እንደበተ-ርቱዕነት እና በስልታዊነት ይሰብካል። ምንም እንኳን መልእክቱን አሁን ባላስታውሰውም፣ በስብከቱ መደመም ብቻ ሳይሆን፣ ተነክቼም ጭምር እንደ ነበር ትዝ ይለኛል። የማስታውሰው አንድ ነገር





በአእምሮዬ ውስጥ ተሰራጭቶ የነበረውን "እንዴት አመለጠኝ፣ ደግሞስ እነዚህን ሁሉ ዓመታት የት ነበርኩኝ?" የሚለውን ጥያቄ እየጠየቅሁ እንደ ነበረ ነው። ለሚቀጥሉት የተወሰኑ ሳምንታት ከጣዕመ ጋር በተከታታይ ሄድኩኝና ከዚያ በኋላ ለራሴ ተተውኩኝ። ጣዕመ የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቱን ከጨረሰ በኋላ ወደ አሥመራ ሲመለስ ራሴን ችዬ ለመሄድ ወይም መሄዱን ለማቆም ባሉት ሁለት ምርጫዎች መካከል ተተውኩኝ፤ እኔም የመጀመሪያውን ወሰንኩ።

በሩቅ አውቃቸው የነበሩ፣ ስለ እምነታቸው ግን ምንም ፍንጭ ያልነበረኝን የማውቃቸውን ሰዎች ማየት ጀምሬ ስለ ነበረ በእያንዳንዱ ሳምንት አይኢሲ ተገኝቼ ለማምለክ ራሴን አሳምን ዘንድ ቀላል አልነበረም። አንዳንዶቹ ያየኋቸው ሰዎች ተራማጅ ፖለቲከኛ መሆኔን የሚያውቁ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ዘግይቶ በነበረው የሕይወት ዘይቤዬ ምክንያት ራሳቸውን ሆነ ብለው ከፖለቲካ እንደሚያገልሉት ተለዋዋጭ ሰዎች አድርገው ያዩኛል። ከናዝሬት ትምህርት ቤት የመጡ አንዳንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎቼንም በማኅበረ-ምእመናኑ ውስጥ ባስተዋልኩኝ ጊዜ የግል ሕይወቴ የእውነተኛ ክርስቲያንነትን ሥዕል የማያሳየው በችግር በመሆኑ፣ በአንዳች መልኩ ያውቁኝ የነበሩት ሰዎች ልጃገረዶችን ማጥመድን ጨምሮ ሌላ ተልዕኮ ይዤ የገባሁ ቢመስላቸውስ ብዬ ማሰብ ጀመርኩኝ። ያንን ሸክም ወደ ቤተ ክርስቲያን በሄድኩ ቍጥር ስለ ተሸከምኩት አንዳንድ ጊዜ እንደ መንገድ ዳር ጉቶ ይሆንብኝ ነበር። ፍርሃቶቼ እንዳሉ ቢሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አምልኮ በመደበኛነት በታደምሁ ቍጥር በታው የበለጠ ብርቱ መስህብነት ያለው ሆነልኝ። ኋላ ላይ የቤተሰቤ ጥሩ ጓደኛ የሆነው መጋቢ ባርከ ፋንስቶከ የእግዚአብሔርን ቃል፣ ወንጌልን በጣም አንደበተ-ርቱዕ በሆነ መንገድ ያቀርብ ስለ ነበር፣ ስብከቶቹን ፈጽሞ ላጣቸው ባለመፈለግ መታደሙን ተጋሁበት። በሰበከ ቍጥር፣ በቅርበት የሚያውቀኝ ያክል በቀጥታ ለእኔ ሕይወት የሚናገር መስሎ ይሰማኛል። በጣም ይስቡኝ ከነበሩት አንደኛው ሰው በቅርቡ ሕይወቱ ያለፈው መጋቢ ስቲቭ ስትራውስ ይባል የነበረ ሲሆን፣ መልእክቶቹ በብዙ አስደንቀውኛል። አልፎ አልፎ የሚሰብኩ ቪከ አንደርሰን የሚባል እና ስሞቻቸውን አሁን የማላስታውሳቸው ሚስዮናውያን ሆነው ከሚያገለግሉበት ደቡባዊት ኢትዮጵያ የሚመጡ መንትያ ወንድማማቾችም አገልግለዋል።

አይኢሲ እየሄድኩ ጌታን ማምለኬን ምንም ያክል ባቅማማበትም፣ በግድም

ቢሆን መሄዴን ገፋሁበት። ለመልካም ምክንያቶች፣ ደግሞም ራስን መግዛት ካለመቻል የተነሣም አምልኮዎችን ሳልገኝ የምቀርባቸው አንዳንድ ጊዜያት ነበሩ። ከጓደኞቼ ጋር ወደ ቡና ቤቶች ሄደን እጠጣና አጨስ ስለ ነበር፣ ለተወሰነ ጊዜ ከአሮጌዎቹ ልማዶቼ ጨርሶ ራሴን ማላቀቅ አልቻልኩኝም ነበር። ነገር ግን፣ ያንንም ቢሆን በድሮ ጊዜ አደርገው እንደ ነበረ ሳይሆን፣ አደርግ የነበረውን ነገር አደርግ የነበረው በአብዛኛው ከጸጸት ስሜት ጋር እንደ ነበር አልደብቅም። በሂደት ግን፣ ለመጠጣትና ለማጨስ ፍላጎት ማጣት ጀመርኩኝ። በእሑዶች ላይ የምማራቸው ትምህርቶች በሕይወቴ ሲሠሩ ይሰማኝ ጀመር። ወደ አሮጌው ልማዶቼ፣ በተለይም በመጠጣት እና በማጨስ እብደት ቀረሽ ፌሽታ ላይ ሰሞላቀቅ ከቆየሁ ወደ አይኢሲ ቤተ ክርስቲያን መሄድ የሚገባኝ እንደ ሆንኩ አድርጌ አላየውም ነበር፣ ስለዚህም ሆነ ብዬ ቤቴ እውላለሁ።

በእነዚህ ጊዜያት ወቅት፣ አንድ ዐብይ ችግር ነበረብኝ። እርሱም፣ አዜብ የምትባል ከልክ በላይ በፍቅር ያበድኩላት ጓደኛ የነበረች መሆኑ እና ከእርሷ ጋር የሚያነጋግር ነገር በገጠመኝ ቍጥር በተስፋ መቁረጥ ውስጥ እየጣለኝ የዚያ ሁኔታ መጨረሻ ወደ መጠጥና ማጨስ ያመራኝ የነበረ መሆኑ ነው። ከእኔ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን አምልኮ ዝግጅቶች እንድትመጣ አሳምኛት የተወሰኑ ጊዜያት መጥታ ታውቃለች። ነገር ግን፣ ይህ ተግባር ከኦርቶዶክስ ክርስትና ትውፊቶች አባብሎ እንደሚያሸሻት ተሰማትና አብዛኛውን ጊዜ ከመኖሪያ አካባቢዋ ብዙም ወዳልራቀው ልደታ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሄድን መረጠች። ይሄን ጊዜ፣ ብቸኝነቴን ለመርታት አንዳንድ ጓደኞቼን እና ዘመዶቼን መጋበዝ ጀመርኩኝ። የአጎቴ ልጅ ጌቱ በመደበኛነት ከእኔ ጋር መምጣት ጀመረ፣ ነገር ግን የእርሱ መምጣት በጉዟችን ውስጥ ካለው መንፈሳዊ ገጽታ ይልቅ በሌሎች ነገሮች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፣ ከጥቅሙ ይልቅ መሰናከልነቱ እንደሚያመዝን አስመሰከረ። አሥመራ ዩኒቨርስቲ አብረውኝ የሚሠሩት አቤ እና አሌክስ አልፎ አልፎ አብረውኝ ይመጡ ጀመር። አሌክስ አዲሱን መንገዴን ለመከተል በጣም ቅርብ የነበረ ቢሆንም፣ ብቅ፣ ጥፍት የሚልበት ታዳሚነቱ እንቅፋት ሆነ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ አንድ ቀን ሐረር ውስጥ ጓደኛዬ የነበረውን ዐቢይ የሚባል ሰው ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አገኘሁት። እርሱ ኋላ ላይ ለወታደራዊው መንግሥት እጁን ሰጥቶ በፓርቲው ውስጥ ትልቅ የፖለቲካ





ስፍራን ያገኘ ስመጥር የኢሕአፓ ፖለቲከኛ በመሆኑ እዚያ ስላየሁት ተደነቅሁኝ። ከአምልኮ በኋላ ተገናኘንና እያንዳንዳችን እንዴት እዚያ ልንገኝ እንደ ቻልን ተጠያይቀን፣ አንዳችን የሌላችንን ታሪክ በተወሰነ መልኩ ልንከፋፈል ተስማማን። በሚቀጥለው ጊዜ ስንገናኝ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አለህ ወይ ሲል ጠየቀኝ፣ እኔም እንደሌለኝ ነገርኩት። ከሽፋኑ በስተውስጥ "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ ቃሌ ግን አያልፍም" (ማቴዎስ 24፡35) የሚል ጥቅስ ሻጥ የተደረገበት ፍጹም አዲስ የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ ሰጠኝ።

በሕይወቴ በግሌ ከነበሩኝ መጽሐፍ ቅዱሶች የመጀመሪያው ያ ሲሆን፣ በመላው ሕይወቴ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቤ አላውቅም ነበር። አዎን፣ በቄስ አምባ ትምህርት ቤት የንባብ ትምህርቶችን እንማር በነበርን ጊዜ ከፊል የመዝሙረ ዳዊት ጽሑፎችን በግዕዝ እየደገምን አንብበን እናውቃለን። በአባቴ እግር ሥር ተቀምጬ ዳዊትን እደግም የነበረ ቢሆንም፣ ከእነዚያ ልምምዶች የትኛውንም ነገር ቀስሜ አላውቅም ነበር። በቄስ አምባም ሆነ በግሌ በቤት ውስጥ የግዕዝ ትርጉም ዳዊትን ማንበቡ አሰልቺ ልምምድ የነበረ ቢሆንም፣ የማንበብ ልማድን ለማዳበር ግን ያለምንም ጥርጥር ረድተውኛል። ግዕዝ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሕዝባዊ በዓላት ማከናወኛ ቋንቋ ቢሆንም፣ ዳዊትን በዚያ ቋንቋ እንድናነብ እና እንድንገነዘበው ይጠበቅብን የነበረ ቢሆንም፣ ለንባቡ ግን ናፍቆት አድሮብኝ አያውቅም። በልጅነቴ መጽሐፉን ማንበብ እና በቃሌ መያዝ ነበረብኝ፣ ደግሞም ጥቅሶቹን በአግባቡ በቃሌ ካልተወጣኋቸው፣ ኃይለኛ ግርፋት የመቀበል አደጋ ውስጥ እገባለሁ። ወጣትም ሆኜ ሳለሁ፣ ስሕተቶችን የመሥራቱ ምናባዊ ሥዕል እና ግርፊያ የመቀበሉ ትዝታ ዳዊት መድገምን አስደሳች ልምምድ አላደረገልኝም። ከአጎቴ ልጅ ሰለሞን ጋር ሐረር ውስጥ በ1960ዎቹ አብረን ስንኖር፣ መደርደሪያ ላይ ተቀምጦ የነበረ አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ነበረው አስታውሳለሁ። ላነበው ወይም በጕጕት ሆኜ ይዘቱን ልመረምረው መቼም ፍላጎት አድሮብኝ ስለማያውቅ፣ ከገጾቹ አንዳንዶቹን ቀድጄ ቅዱስ ላልሆኑ ተግባራት ተጠቅሜባቸዋለሁ። በማርክሲዝም አስተምህሮ ድግምት ሥር መውደቅ እንዲህ ያለ ትልቅ ጥፋትን ሊፈጥር ይችላል - እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቅዱስ መጽሐፍ ቅንጣት ታክል እንኳን በማያስጨንቅ መልኩ ለማርከስ ማለት ነው። ሐሳባዊነት ታግለው የሚያሸንፉት ነገር ካልሆነ፣ ትልቅ የሚያሳውር ነገር ሊሆን ይችላል።

የገዛ ራሴን መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ያገኘሁት ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ፣ የዐቢይን ስጦታ በጣም ዋጋ ሰጠሁት። ከዚህ የተነሣ፣ የብሉይ ኪዳኑ ክፍል ልከተለው እና ልረዳው ከባድ ቢሆንብኝም፣ ከማንም ሰው ምሪትን ሳላገኝ በራሴ ማንበብ ጀመርኩኝ። አብዛኞቹ ቅዱስ ገጽታ የተሰጣቸው ታሪኮች መጀመሪያ ላይ ለእኔ በጣም እውነታነት የሌላቸው መስለውኝ ነበር። አዲስ ኪዳን፣ በተለይም የጳውሎስ መልእክቶች ስሜት የሚሰጡኝ ሆኑ። መጽሐፍ ቅዱስን በመጠኑ በመደበኛነት ማንበብ ጀመርኩኝ፣ ነገር ግን የማርክሲዝም ሥነ-ጽሑፍን እንደማነበው እየተስገበገብኩ እና እያመዛዘንኩ አልነበረም። ነገር ግን ያኔም እንኳን በአእምሮዬ ውስጥ የሚያልፉ አንዳንድ ጥቂት መገለጦች ነበሩ።

አበረ የሚባለውን የአይኢሲ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን እና ወደ ቤተ ክርስቲያን ፊገግታ ባለው ቸርነት ያስተናግደኝ የነበረውን ሰው ለመተዋወቅ የታደልኩት በዚህ ጊዜ ነበር። አበረ የአማኑኤል ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ የነበረ ሰው ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያናቸው በአምባገነኑ የመንግሥቱ አገዛዝ ታሳልፈው ከነበረው የስደት ልምምድ የተነሣ ውስጥ ለውስጥ (በሕቡዕ/ ቤት ለቤት) በመንቀሳቀስ ላይ ነበረች። ከሞላ ጎደል ሁሉም የሚሰዮናውያን መገኛ ያላቸው የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተው ስለ ነበረ፣ በምሥጢር ሆነው በየሰዎቹ ቤቶች ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። አይኢሲ የውጭ አገር ዲፕሎማቶች እና ከአገራቸው ውጪ የሚኖሩ ሰዎች እንደ አፍሪካ ኅብረት (ያን ጊዜ አኢዩ፣ አሁን ግን ኤዩ)፣ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ፎር አፍሪካ (ኢሲኤ)፣ ያሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች የሚያመልኩባት ዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ስለ ነበረች፣ መንግሥት ሊዘጋው አልደፈረም ነበር።

## ወደ መረዳቶች መምጣት

አበረ እና በርቀት አውቀው የነበረው የቀድሞው የሕግ ትምህርት ቤት ጓደኛው፣ ሽፈራው፣ በዝግታ ጓደኞሞች መሆን ጀመርን። ጓደኛ ያደረጉኝ ምናልባት ብቸኛ እና በመጠኑ ለዚህ ቤተ ክርስቲያን ድባብ እንግዳ እንደ ሆንኩ በመገመት ሊሆን ይችላል። ከእያንዳንዱ የእሑድ አምልኮዎች በኋላ እንድናወራ በቸርችል ጎዳና ላይ ካሉት የመቀጣጠሪያ ምርጥ ካፍቴሪያዎች ወደ አንደኛው ይወስዱኝና አንዳንድ ጊዜ ለምሳ ወይም ለእራት ይጋብዙኝ ጀመር። ሽፈራው





ሲነግረኝ ከአምስት ዓመታት በላይ ለሚሆን ጊዜ ታስሮ የሚያውቅ የቀድሞ የኢሕአፓ አባል እንደ ነበረና እግዚአብሔርን ያወቀው፣ ደግሞም የተሰጠ ክርስቲያን የሆነው በእስር ቤት ውስጥ እንደ ሆነ ጠቆም አደረገኝ። እያንዳንዳችንን እግዚአብሔር እንዴት እንደ ተከታተለን፣ ወደ ሽለቆ እንዳመጣን እና በዚያም እንዳገኘን ሲታይ ነገሩ አስደናቂ ነው። በሌላ አነጋገር፣ እርሱ ከተራማጅ የኢሕአፓ ታጋይነት "ዳግም ወደ ተወለደ ክርስቲያንነት" የተለወጠው በእስር ቤት ውስጥ ነበር ማለት ነው። የሚደንቀው ነገር፣ "ዳግም ወደ ተወለደ ክርስቲያንነት" መለወጥ የሚለው ቃል ምን ማለት እንደ ሆነ የተማርኩት ኋላ ላይ ዘግይቼ መሆኑ ነው። ጣዕመ "ዳግም የተወለደ ክርስቲያን" የሚለውን ሐሳብ ጠቆም አድርጎኝ ነበር፣ ነገር ግን በጊዜው ጉልህነቱን ያን ያክል ሳልይዘው ቀረሁ። ስለዚህኛው ጠቃሚ ፍሬ ሐሳብ ከአዲሶቹ ጓደኞቼ አሁን የበለጠ መማር እየጀመርኩኝ ነው።

ከላይ እንደ ገለጽኩት፣ አበረ ያን ጊዜ በድብቅ ትንቀሳቀስ በነበረችው የአማኑኤል ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንጌላዊ ሆኖ ያገለግላል። ነገር ግን፣ በአይኢሲ ደግሞ እንደ ዲያቆን ሆኖ በሚያገለግልበት ጊዜ በመጠኑ ቁጥብ ከነበረው ሽፈራው በተለየ በጣም ተግባቢ እና ደስ የሚል ሰው ሆኖ አገኘሁት። ቀስ በቀስ ሁለቱንም ወደድኳቸው ደግሞም አመንኳቸው፣ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር መሆን ቤተኝነት እንዲሰማኝ አደረገ። ኋላ ላይ በሌሎች ጥሩ ክርስቲያን ጓደኞች ታጀብን - አሌ፣ ሚሊ፣ የእንስሳት ሐኪሙ ዜይ እና ያን ጊዜ ለዓለም አቀፉ የቀንድ ከብት ኤጀንሲ ይሠራ የነበረው ለጌ። የእምነት ጉዳዮችን በግልጽ ለመወያየት የሚፈቅዱ፣ ሲበዛ ተንከባካቢ እና ቸር የሆኑ፣ ደግሞም ለምግባቸው እንኳን ሳይቀር ተቀጣጥለው በሚጸልዩ የተሰጡ ክርስቲያኖች መካከል አዲስ የጓደኞች ክበብን ቀስ በቀስ ማዳበር ቻልኩኝ።

አንድ ጊዜ አበረ በማናቸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዝግጅት ላይ እሳተፍ እንደ ሆን ሲጠይቀኝ፣ ስለ ታሪኬ ደግሞም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ መጣሁና ራሴን የማስጠጋበት ቡድን እንደሌለኝ ፍርጥ አድርጌ ነገርኩት። ተከታታይ በሆኑት መገናኘቶቻችን የተሰጠ ክርስቲያን ለመሆን እና ክርስቶስንም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ለመከተል ጠንካራ ውሳኔ፣ ደግሞም የበረታ እርምጃ እንዳልወሰድኩኝ አስተዋለ። በእርግጥ፣ አንድ ቀን ያንን አድርጌ